አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


# ጡሩሲና የሙስሊም "ገዳም" እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ በአላት ስርአተ ክዋኔ


በ
ሰሚራ መሀመድ



2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ጡሩሲና የሙስሊም "ገዳም" እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ በአላት ስርአተ ከዋኔ

በ
ሰሚራ መሀመድ

2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ጡሩሲና የሙስሊም "ገዳም" እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ በአላት ስርአተ ከዋኔ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

አማካሪ

ዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው

በ

ሰሚራ መሀመድ

2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ጡሩሲና የሙስሊም "ገዳም" እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ በአላት ስርአተ ክዋኔ

በ

ሰሚራ መሀመድ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ባይለየኝ ጣሰው | |
| የውስጥ ፈታኝ | |
| [illegible] | |
| የውጭ ፈታኝ | |
| [illegible] | |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
UNIVERSITY

# ማውጫ


ምስጋና ____ i

አጠቃሎ ____ iii

1. መግቢያ ____ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ____ 1

1.1.1. የኦሮሚያ ዞን ገጽታ ____ 2

1.1.2. የጡሩሲና "ገዳም" አመሰራረት ____ 8

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ____ 12

1.3 የምርምር ጥያቄዎች ____ 13

1.4 የጥናቱ አላማ ____ 14

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ____ 14

1.6 የጥናቱ ወሰን ____ 16

1.7 የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ዘዴ ____ 16

1.8 የመስክ ጥናት ገጠመኝ ____ 21

2 ክለሳ ድርሳን ____ 27

2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ____ 27

2.2 የንድፈ ሀሳብ ዳራ ____ 35

3 ጡሩሲና የሙስሊም ገዳም ከገዳማዊ ህይወት ብያኔ አንፃር እና የገዳሙ መነሻ ትርክት ____ 43

3.1 ጡሩሲና የሙስሊም ገዳም ከገዳማዊ ህይወት ብያኔ አንጻር--43

3.1.1 የገዳም እና ገዳማዊነት ትርጉም ______ 43

3.1.2. የጡሩሲና "ገዳም" ከገዳማዊ ህይወት አንፃር ______ 46

3.2. የጡሩሲና "ገዳም" መነሻ ትርክት ______ 51

4. በጡሩሲና "ገዳም" የሚከበሩ ክብረ በአላት ስርአተ ክዋኔ ______ 56

4.1. የመውሊድ አከባበር ______ 56

4.1.1. የቁዜማ ዝግጅት ______ 56

4.1.2. አውደ በአል ______ 58

4.1.2.1. በወንዶች "ገዳም" የበአሉ አከባበር ______ 58

4.1.2.2. በሴቶች "ገዳም" የበአሉ አከባበር ______ 63

4.1.3. የበአል ማግስት ______ 68

4.2 የቁርአን ኸትሚያ (ሰርግ) አከባበር ______ 68

5. ማጠቃለያ እና መደምደሚያ ______ 72

5.1 ማጠቃለያ ______ 72

5.2 መደምደሚያ ______ 73

5.3 ይሁንታ ______ 75

ዋቢ ______ 76

አባሪ ______ 80

# ምስጋና

አማካሪዬ እና መምህሬ ዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው ያልገባኝን ነገር በጠየቅሁ ቁጥር ያለመታከት የማስረዳት ትእግስትህ እጅግ ይገርመኛል፡፡ በእውቀት እና በትጋት የማማከር ብቃትህ ለጥቂቶች ብቻ የሚሰጥ መሆኑን ሳስብ የአንተ ተመካሪ በመሆኔ እድለኛነቴን አስታውሳለሁ፡፡ ጥናቱን በፍጹም ንቃት አስጀምሮ እስከማስጨረስ ድረስ በሚዘልቅ ውለታ አጅበህ የሆነው ሁሉ እንዲሆን ረድተኸኛል፡፡ እናም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

መምህሬ አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ (ቴዲ) እውቀት እና ቅንነት መሳ ለመሳ የተሰጡት ሰው ጥቀሽ ብባል ከአንተ አስቀድሜ የምጠራው ሰው የለኝም፡፡ አሉኝ የምላቸውን ጥሩ ነገሮች ያገኘሁት ከአንተ ቢርቅ እንኳ በአንተ ነው፡፡ ውለታህን አስቤ አንተን ለማመስገን እንደብቴን ስከፍት የማውቃቸው ቃላት በሙሉ የውስጤን ለመግለጽ ይሰንፉብኛል፡፡ ላደረክልኝ ጥሩ ነገር አመሰግናለሁ ማለት የልቤን ባያደርስም ሌላ አማራጭ የለኝምና አመሰግናለሁ፡፡

አባቴ መ/ር መሀመድ ሰይድ እና እናቴ ወ/ሮ ፋጡማ እንድሪስ ልጅን አስተምሮ ከምንምነት ወደ አንዳችነት ለማምጣት የሚታለፈውን ንብርብር አሳር ለማስረዳት እናንተ ሁለት ዋኖቼ ማሳያ ናችሁ፡፡ እናቴ ጡሩሲና ስመላለስ በብዙ ሀሳብ እና ጭንቀት አብረሽን ነበርሽ፡፡ መረጃ ሰጭዎቼን በጓደኝነት ማቅረብ እችል ዘንድ ይገዙ የሄድኪቸው አልባሳት የእንቺ ገጸ በረከት ነበሩ፡፡ ከምንም ለሚጠልቀው ደግነትሽ ለዘላለም አመሰግንሻለሁ፡፡ አባቴ ያ ሁሉ መውጣት መውረድህ ይህን ጥናት ለመስራት ነበር፡፡ ስራ የሚበዛብህ ባተሌ ብትሆንም የጡሩሲናን መንገድ በሀሳብም በተግባርም አብረኸኝ ተጉዘሀል፡፡ በጊዜህ፣ በገንዘብህ እና በጉልበትህ ላይ ያለመሳቀቅ አዝዣለሁ፡፡ የእውነት አመሰግንሀለሁ፡፡ እህቶቼ ሰአዳ፣ ራቢያ፣ እና ኑረዲን መሀመድ ለህይወቴ መቃናት እና ለዚህ ጥናት መሳካት ሀሳባችሁ እና ገንዘባችሁ አግዞኛል፡፡ እወዳችኋለሁ፡፡

ጓደኛዬ ብርኳታይት ተክላይ ሁሌም ከጎኔ በመሆን የሰጠሽኝ ምክር እና ጭምቅ ሀሳብ እጅጉን ጠቅሞኛል፡፡ ወንድወሰን እንዱአለም በወንዶች "ገዳም" ገብቼ መረጃ መሰብሰብ አለመቻሌን ተረድተህ ከአዲስ አበባ ደሴ፣ ከደሴ ጡሩሲና በመጓዝ መረጃ በመሰብሰብ አግዘኸኛል፡፡ ሁለታችሁንም በጣሙን አመሰግናችኋለሁ፡፡

በሶስት ዙር የመስክ ቆይታዬ ያለአንዳች ማቅማማት ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል የተባበራችሁኝ አቶ አዩብ አብደላ፣ አቶ አህመድ መሀመድ፣ ሼህ መሀመድ አማን እና ጡሩሲና ገዳም የምትኖሩ ገዳማውያን ከፍ ያለ ምስጋና ይገባችኋል።

ነጻ የትምህርት እድል በመስጠት እና ለጥናቱ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የተባበረኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን፣ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍልን እና አቶ ደረጀ ገብሬን ከልብ አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ


ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በጡሩሲና ሙስሊም "ገዳም"[1] እና "በገዳሙ" የሚከወኑ በአላት ስርአተ ክዋኔ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በጥናቱ የተነሱ ሁለት ዋና የምርምር ጥያቄዎች የሙስሊም "ገዳም" በአገራችን እንዴት ሊኖር ቻለ? እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ በአላት ከሀይማኖታዊነታቸው ባለፈ ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው? የሚሉ ናቸው። ከቤተ መጻህፍት በተገኙ ስራዎች እና የጥናት ወረቀቶች ላይ ንባብ የተካሄደ ሲሆን ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይትን በመጠቀም ከመስክ መረጃ ተሰብስቧል።

የኩብረ በአላቱን እውነተኛ ገጽታ ለመረዳት አውድ ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ክዋኔን ማእከል ያደረገ አቀራረብ ተጠቅሟል። በተጨማሪም "የገዳሙን" መልከአምድራዊ አቀማመጥ፣ አመሰራረት እና ድባብ ለማሳየት ገላጭ የትንተና ስልትን በግብአትነት ወስዷል። በመጨረሻም በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙ መረጃዎች ጥናቱ ከተቀነበበበት ንድፈ ሀሳብ እና ከሚተንተንበት ስልት ጋር ተጣምረው የሚከተሉትን ውጤት አስገኝተዋል።

በእስልምና አስተምህሮት ውስጥ ያልተለመደው የሙስሊም "ገዳም" እንዴት ሊኖር ቻለ? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የእስልምና ሀይማኖት ወደ አገራችን የገባበትን ታሪክ በመውሰድ እና በወሉ ያለውን የሀይማኖቶች መቻቻል እና ተቀራርቦ የመኖር ባህል በመጥቀስ የእስልምና እና የክርስትና ሀይማኖት አብሮነት ውጤት መሆኑን አሳይቷል። ጡሩሲና የሚኖሩ ሰዎች "ገዳም" ብለው ባይጠሩትም በተለያዩ እምነቶች (በኦርቶዶክስ ክርስትና፣ በአይሁድ፣ በቡድሂዝም፣ በሂንዱይዝም፣ በብራህማኒዝም) ገዳም ያለውን ትርጉም በመውሰድ ከጡሩሲና አስተዳደራዊ መዋቅር፣ አኗኗር፣ ህይወት አንጻር በመገምገም በዚህ ጥናት ጡሩሲናን "ገዳም" ብሎ መጥራት ተችሏል።

"በገዳሙ" ውስጥ ከሚከበሩ በርካታ ክብረ በአላት መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡት መውሊድ እና የቁርአን ክትሚያ/ስርግ ስርአት ናቸው። በመውሊድ በአል ከአዲስ አበባ፣ ከጎንደር፣ ከደሴ፣ ከኮምቦልቻ፣ ከከሚሴ የሚመጡ ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች ይታደማሉ። በተመሳሳይ መልኩ የቁርአን ክትሚያ (ስርግ) ከመውሊድ የሚለየው "በገዳማውያኑ" ብቻ የሚከበር በአል በመሆኑ ነው። ሁለቱም በአላት በምርቃቶች፣ በተረኮች፣ በትእይንቶች፣ በጭፈራዎች፣ በውዝዋዜዎች እና በግጥሞች ታግዘው መከበራቸው በሀይማኖቱ እና በባህሉ መካከል ያለውን ትስስር ማሳያ ናቸው። ከበራዎቹ የታዳሚዎቹን ግላዊ እና የወል ማንነት ከመግለጽ አንጻር ከፍ ያለ ፋይዳ አላቸው።


---

[1] የጥናቱ ተተኳሪዎች የጡሩሲናን "ገዳም" ቂርአ (የቁርአን ትምህርት ቤት) "ገዳናውያኑን" ደግሞ ደረሳ በማለት ይጠሯቸዋል። በዚህ ጥናት "ገዳም" እና "ገዳማውያን" የሚሉ ቃላትን በትእምርት ጥቅስ ማስገባቴ እንደ አጥኚ የጥናቱ ተተኳሪዎች ለሚጠቀሙበት መጠሪያ ቅድሚያ መስጠቴን ለመግለጽ ነው።

# ምእራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት በጡሩሲና ሙስሊም "ገዳም" እና "በገዳሙ" በሚከበሩ በአላት ስርአተ ክዋኔ ላይ ትኩረት አድርጎ ተሰናድቷል። ጥናቱ በአምስት ምእራፎች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ምዕራፍ አንድ የጥናቱን፤ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ አላማ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብ እና የአተናተን ዘዴ፣ በሂደቱ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሄዎች እና የመስክ ጥናት ገጠመኝን አካቷል። ምዕራፍ ሁለት ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተዛማጅ የጥናት ወረቀቶች ቅኝትን እና ጥናቱን ለመተንተን የተመረጠው ክዋኔን ያማከለ ንድፈ ሀሳብን ይዟል። ምዕራፍ ሶስት በአለም አቀፍ እና በአገራችን የገዳም እና ገዳማዊ ህይወት ብያኔዎችን በመያዝ የጡሩሲናን መስጊድ "ገዳም" ብሎ መጥራት እንደሚቻል ገልጿል። ከዚሁ ጋር አያይዞ በእስልምና ሀይማኖት አስተምሮት ውስጥ "የገዳም ህይወት" ሳይኖር በአገራችን (በወሎ) አካባቢ እንዴት ሊኖር እንደቻለም አብራርቷል። ምዕራፍ አራት ከመስክ ምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅ እና ከቡድን ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ተንትኗል። በዚህም "በገዳማውያኑ" እና በአካባቢው (በሙስሊሙ) ማህበረሰብ ትልቅ ስፍራ በሚሰጠው የመውሊድ በአል እና "በገዳማውያኑ" ብቻ በሚከወነው የቁርአን ክትሚያ "(ሰርግ)" ክብረ በአላት ላይ በማተኮር ትንተና አካሂዷል። ምእራፍ አምስት የጥናቱን ማጠቃለያ እና መደምደሚያ አካቷል። በመጨረሻም ዋቢ ጽሁፎች እና ከጥናቱ ጋር የተያያዙ አባሪዎች ተቀምጠዋል።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የጡሩሲና "ገዳም" የሚገኘው በኦሮሚያ ዞን በከሚሴ ከተማ በዳዋ ጨፋ ወረዳ ነው። ስለ ጡሩሲና ከመገለጹ በፊት "ገዳሙ" የሚገኝበት ስፍራ፣ የኦሮሚያ ዞን እና በዞኑ የሚገኙ ሃይማኖታዊ እና ታሪካዊ ስፍራዎች "ለገዳሙ" ካላቸው ቅርበት አንጻር እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

### 1.1.1. የኦሮሚያ ዞን ገጽታ

የኦሮሚያ ዞን በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በ1986 ዓ.ም አጋማሽ ከተቋቋሙት ልዩ የብሄረሰብ ዞኖች አንዱ ነው፡፡ ዞኑ በ5 ወረዳዎች፣ በ2 የከተማ አስተዳደሮች፣ በ102 የገጠር ቀበሌዎች እና 21 የከተማ ቀበሌዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ ዋና ከተማው ከሚሴ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ በሚወስደዉ መንገድ በ325 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ዞኑ በምስራቅ ከአፋር፣ በምእራብ ከሰሜን ሸዋ፣ በሰሜን ከደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ከአፋር እና ከሰሜን ሸዋ ዞኖች ጋር ይዋሰናል (የኦሮሚያ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፣2003 እ.ትም፣ከሚሴ)፡፡

በዞኑ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የአርጎባ እና የአፋር ህዝቦች ይገኛሉ፡፡ በአካባቢው ሁለት የኩሽ ቋንቋዎች (ኦሮምኛ እና አፋርኛ) እና ሶስት የሴም ቋንቋ (አማርኛ፣ አርጎብኛ እና አረብኛ) ይነገራሉ፡፡ ኦሮምኛ የአፍ መፍቻ እና የስራ ቋንቋ በመሆን ያገለግላል፡፡ አማርኛ በከተሞች እና በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ በአፍ መፍቻነት እና በከፊል ሁለተኛ ቋንቋነት ይነገራል፡፡ አርጎብኛ በዳዋ ጨፋ ወረዳ ጆሮታ ቀበሌ፣ በሸንኬ ልዩ የአርጎባ መንደር እና በሌሎች ወረዳዎች በቤተሰብ ደረጃ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ አፋርኛ ደግሞ በአፋር ክልል አዋሳኝ በሆኑ የዞኑ ወረዳዎች በሁለተኛ ቋንቋነት ይነገራል፡፡ አረብኛም በዞኑ ውስጥ በሚገኙ መስጊዶች ለመግባቢያነት ያገለግላል (የኦሮሚያ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ፣2001 እ.ትም)፡፡




ምንጭ፡- የኦሮሚያ ዞን ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ

የዞኑ የሀይማኖቶች የሰላም ጽ/ቤት መረጃ እንደሚያመለክተው የእስልምና ሀይማኖት ተከታዩ ከአጠቃላይ ህዝቡ 95 በመቶ ይሸፍናል፡፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና ከፕሮቴስታንት ሀይማኖት በተሻለ በአካባቢው የእስልምና ተቋማት በስፋት መገኘታቸው በመስጊዶች የሚሰጠው ትምህርት ሚናው ከፍ ያለ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ዛውያ[1] እና ከለዋ (ጎጆ) ዋና የእስልምና ትምህርት ማእከል ሲሆኑ የትምህርት አሰጣጡ ባህላዊ በሆነ መንገድ ይከናወናል፡፡ በእምነቱ ጥልቅ እውቀት ባላቸው ሼሆች አማካይነት የአረብኛ የፊደል ገበታ፣ ቁርአንን ያለ ትርጉም መሸምደድ፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎት በመጀመሪያ ደረጃ ይሰጣል፡፡ ይህንን ደረጃ ላለፉ የቁርአን ትርጉም፣ የአረብኛ ሰዋሰው፣ ስነ—ምእላድ እና ስነ—ድምጽ፣ የኪታብ ትርጉም ለደረሱት ይሠጣል፡፡ ይህ የትምህርት አሰጣጥ ስርአት ባለው መልኩ በአንድ ማዕከል ሲሰጥ አለመቻሉ፣ የትምህርት መሳሪያ በበቂ ሁኔታ አለመሟላቱ እና ለተማሪዎች እና ለመምህራን የምግብ አቅርቦት አለመኖሩ ሂደቱን አስቸጋሪ እንዳደረገው አቶ አዩብ አብደላ[2] (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር26፣ 2004)[3] ገልጿል፡፡ የትምህርት መሳሪያ እጥረቱን ለማቃለል ከእንጨት በተጠረበ ሉህ (ጣውላ) ላይ ከጥላሸት የተሰራ መድ (ቀለም) በማዘጋጀት በመቃ (ላባ) ይጠቀማሉ፡፡ ምግባቸውን ደግሞ በሀይማኖቱ መሰረት "የተወደደ ተግባር ነው" በሚል እምነት በህብረተሰቡ በሚደረግ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ በዞኑ ውስጥ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች በመኖራቸው የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞችን በማስተባበር በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡

ከእነዚህ ስፍራዎች አንዱ የሾንኬ መንደር እና መስጊድ ነው፡፡ የሾንኬ መንደር እና መስጊድ በወረዳው ላለፉት 900 አመታት አገልግሎት ሲሰጥ የኖረ ነው፡፡ መንደሩ ከከሚሴ ከተማ በስተምስራቅ አቅጣጫ በ25 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በዳዋ ጨፋ ወረዳ ጅሮታ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ይገኛል፡፡ የመንደሩና የመስጊዱ አሰራር ከገጠሩ የአገራችን የቤቶች አሰራር የተለየ ጥንታዊ እና የስነ ህንጻ ጥበብ የሚታይበት ቅርስ ነው፡፡ የቤቶቹ አሰራር በነጫጭ ድንጋዮች የተገነባ ነው፡፡ ጣሪያው በእንጨት ርብራብ ተሰርቶ የውጭ ጣሪያው በነጭ አሸዋ እና አፈር የተደለደለ መሬት በመሆኑ ለእህል ማስጫ እና ለመናፈሻ ይጠቀሙበታል፡፡

---

[1] ዛውያ ማለት የከተማ መስጊዶች ሳይስፋፉ በገጠሩ አካባቢ ቢጋራ ለማምለክ የሚያገለግል የጸሎት ቤት ነው፡
[2] አቶ አዩብ አብደላ የሚኖረው በከሚሴ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ ነው፣ እድሜው 26 ሲሆን ከሀረማያ ዩኒቨርሲቲ በ2001 ዓ.ም ታሪክ ትምህርት ክፍል ተመርቆ በአሁኑ ሰአት የከሚሴ ከተማ የቅርስ እና የመስህብ ሀብቶች ጥናት ምዝገባ እና ቁጥጥር ኦፊሰር በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡
[3] ከዚህ በኋላ ቃለ መጠይቅን ቃ.መ በማለት የምጠቀም ይሆናል፡፡

## የሾንኬ መንደር ገጽታ



ምንጭ፡- የኦሮሚያ ዞን ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ

ለሾንኬ መንደርና መስጊድ መመስረት ምክንያቱ በአቅራቢያው የጦለህ መስጊድ መኖሩ እንደሆነ ይነገራል። በዚህ ቦታ ታዋቂ እንደነበሩ የሚነገርላቸው ጁሀር ሀይደር ቢን አሊይ የተባሉ የሀይማኖት መምህር ከጊዜ በኋላ በክብር ሼህ ሾንኬ እንደተባሉ እና ይህ የማዕረግ ስም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የአንድ ግለሰብ ስያሜ መሆኑ ቀርቶ አጠቃላይ የመንደሩ እና የመስጊዱ መጠሪያ እንደሆነ አቶ አሊ ገበየሁ ጽፈዋል። ሼህ ሾንኬ በዚህ መስጊድ ያስተምሩ በነበረበት ጊዜ ሙስሊሞች ከትራን፣ ከጅማ፣ ከደቡብ አካባቢ እና ከየመን ድረስ እየመጡ የመኖራቸው ሁኔታ መስጊዱን ጥንታዊ የእስልምና ትምህርት ማእከል እንዳደረገው ይገልጻሉ። በዚህ

መንደር የሚጠቀሰው ሌላው ጉዳይ የመንደሩ ነዋሪዎች የአርጎብኛ፣ የኦሮምኛ፣ የአማርኛ እና የአረብኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች መሆናቸው ነው (አሊ ገበየሁ፣1991)፡፡

በሁለተኛነት የሚጠቀሰው የዶዶታ መስጊድ ነው፡፡ ይህ መስጊድ በደዌ ሀረዋ ወረዳ አሊዩ ቀበሌ ዶዶታ ጎጥ ውስጥ ከከሚሴ ከተማ በስተምስራቅ አቅጣጫ ከ40 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ መስጊዱ በኮረብታ ስፍራ ላይ የተሰራ ነው፡፡ የተሰራውም በሂጅራ አቆጣጠር 1176 እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑትን አቶ ጀማል ሲራጅ ጠቅሶ አጥኚው ጽፏል፡፡ መስጊዱ በወቅቱ በአካባቢው ታዋቂ ወሊይ በነበሩት አባሲያ (የአሲያ አባት) የተሰራ ሲሆን አጽማቸው በመስጊዱ ቅጥር ግቢ ውስጥ አርፏል፡፡ ይህ መስጊድ በአካባቢው የእስልምና ሀይማኖት ለሁሉም በስፋት እንዲዳረስ የተደረገበት በመሆኑ ልዩ ቦታ እንደሚሰጠው ይነገራል (አሊ ገበየሁ፣1990)፡፡

በሶስተኛነት የሚነሳው የጆኤርቱ መስጊድ ነው፡፡ መስጊዱ በባቲ ወረዳ ጨለለቃ ቀበሌ ውስጥ ሲገኝ ከባቲ የ7 ወይም የ8 ሰአት በእግር መጓዝን ይጠይቃል፡፡ መቼ እንደተሰራ በትክክል ባይታወቅም የህንጻው ዲዛይን እና ጥበብ በመካከለኛው ዘመን እንደተሰራ ያመላክታል፡፡ የመስጊዱ መስራችም የዶዶታን መስጊድ የገነቡት አባሲያ እንደሆኑ በጆኤርቱ መስጊድ ላይ አጭር ጥናት የሰራው ፍቅሩ የተባለ ባለሙያ ጽፏል፡፡ አባሲያ የጆኤርቱ እና የዶዶታን መስጊድ ጨምሮ 99 መስጊዶች እንደገነቡ ይነገርላቸዋል፡፡ ለመስራት የተጠቀሙባቸው ድንጋዮች በዘመናዊ ማሽን ተጠርበው የተዘጋጁ እንጂ በዘመኑ በእጅ የተሰሩ እንደማይመስሉ (ፍቅሩ ደሳለኝ፣1994) ገልጿል፡፡

አራተኛው የቆምቦሮ መካነ መቃብር ቦታ ነው፡፡ ቦታው የሚገኘው በአርጡማ ፋርሲ ወረዳ በመርማ ጊሌ ቀበሌ ልዩ ስሙ ቆምቦሮ በሚባለው መንደር ነው፡፡



ምንጭ፡- የኦሮሚያ ዞን ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ

የመቃብር ቦታው 132 ስኩዌር ሜትር ስፋት አለው። ከእድሜ ብዛት መቃብሮችን መለየት የሚቻለው በአካባቢው በተተከሉት የመቃብር ድንጋዮች ብቻ ነው። በመቃብር ድንጋዮቹ ላይ የሰፈሩት ጽሁፎች በአረብኛ ቋንቋ የተጻፉ እና የሟቾቹን ማንነት እና አሟሟት የሚገልጹ ነበሩ። ጽሁፎቹ ሙሉ በሙሉ ይነበቡ በነበረበት ወቅት የሚከተለውን መረጃ ይሰጡ እንደነበር ይነገራል።

1. "በሁለተኛው ሂጅራ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ አረቦች መቃብር መሆኑን፣
2. የተቀበሩት ሰዎች ብዛት 44 እንደሆን ከእነዚህ ውስጥም ሁለቱ ሴቶች እንደነበሩ፣
3. አሟሟታቸው ለይፋት መንግስት መልእክት አድርሰው ሲመለሱ ከሌላ አካባቢ ነዋሪዎች በአጋጠማቸው ውጊያ እንደሆን የሚገልጹ ነበሩ።"

ከዚህ ሀሳብ በተቃራኒ "መካነ ቀብሩም የአረቦች ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ነው" የሚል አስተያየት አለ። (የኦሮሚያ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፣2003 እትም፣ያጠናው ባለሙያ ስም አልተጠቀሰም)።

ከላይ በተጠቀሱት መስጊዶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ሶስት መስጊዶች ይገኛሉ። የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በዞኑ ውስጥ ከሚገኙት መስጊዶች በአኗኗር ዘዴው የተለየ እና ያልተለመደው የጡሩሲና "ገዳም" ነው።

### 1.1.3. የጡሩሲና ሙስሊም "ገዳም" አመሰራረት

ጡሩሲና የሚለው ቃል ትርጉም "የሲና ተራራ" ማለት ሲሆን ትርጉሙም የሲና ተራራ በመባል ከተጠቀሰው የቁርአን፣የመጽሀፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር የሚዛመድ ነው። ይህም በመጀመሪያ የጁደይዝም እምነት አስተምህሮት እንደሆነ ወደሚነገረው ብሉይ ኪዳን እና ከድህረ ክርስቶስ በኋላ ወደመጣው ሀዲስ ኪዳን ይወስደናል። በብሉይ (ዘጸ፣20÷1.20) እግዚአብሄር ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙሴ የተገለጠበት እና አስርቱን ትእዛዛት የተቀበለበት ስፍራ መሆኑ "እግዚአብሄርም በሲና ተራራ ጫፍ ላይ ወረደ። ሙሴንም ወደ ተራራው ጫፍ ጠራው። ሙሴም ወጣ። እግዚአብሄርም እንዲህ አለው..." በሚል ተጠቅሷል። በተመሳሳይ ሁኔታ በእስልምና ሀይማኖትም የሲና ተራራ አላህ ከነቢዩ ሙሳ ጋር የተገናኘበት እና መልእክቶችን ያቀበለበት ስፍራ (ም.7፣ አልአእራፍ፣ 141-142) ነው ።

> "ሙሳም፣ ለቀጠሮአችን፣ በመጣና፣ ጌታውንም፣ ባነጋገረው፣ ጊዜ፣ ጌታዬ፣ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ፣ ወደ፣ አንተ፣ እመለከታለሁ፣ አለ፣ (አላህም) ፡- በፍጹም፣ አታየኝም፣ ግን፣ ወደ፣ ተራራው፣ ተመልከት፣ በስፍራውም፣ ቢረጋ፣ በእርግጥ፣ ታየኛለህ፣ አለው። ጌታውም፣ ለተራራው፣ በተገለጠ፣ ጊዜ፣ ንኩትኩት፣ አደረገው...። አላህም፣ አለው፣ ሙሳ፣ ሆይ፣ እኔ፣ በመልእክቶቼና፣ እና በሰዎች ላይ (1) መረጥኩህ፣ የሰጠሁንም፣ ያዝ፣ ከአመስጋኙ፣ ሁን።(ቅዱስ ቁርአን፣1961□112)

ከጥቅሱ የምንረዳው የሲና ተራራ በሁለቱም ሀይማኖቶች አስርቱ ትእዛዛት የተቀበሉበት እና ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ቦታ መሆኑን ነው። የጡሩሲና ገዳምም ይህንን ስያሜውን ሲያገኝ በዋናነት በቁርአን ላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ እንደሆነ ይነገራል። ቴዎድሮስ ገብሬ "ስም" ያሁን ማንነትን ሊገልጽ፣ ስም ያለፈ ግብርን ሊቀርጽ፣ ስም በንግርነት ነገን

ሊጠቅስ ይችላል በማለት ይገልጻሉ። ከዚሁ ሀሳብ ጋር አያይዘውም ለአንድ አካል ስም መስጠት ማለት ነገሩን ማወቅ ማለት ነው። ነገሩን ማወቅ ደግሞ በፊንታው በነገሩ ላይ መሠልጠን ማለት ነው (2001፣106) ይላሉ። ይህንን ሀሳብ ከጡሩሲና ጋር ስናዛምደው ገዳሙ ስያሜውን ያገኘበት የሲና ተራራ ሁለቱም ሀይማኖቶች በእኩል ደረጃ ከተቀበሉት ታሪክ መዛመዱ በኋላ ላይ በገዳሙ በክርስትና እምነት የተለመደውን የገዳም ህይወትን እና የእስልምና አስተምህሮት የሚያዘውን ህግ አስማምቶ ለመተግበሩ ንግር ነው ማለት ይቻላል። እግዜአብሄር (አላህ) የወደደውን ነቢይ መርጦ መልእክት ለማስተላለፍ የጠራበት ስፍራ ተራራ ነው፤ የጡሩሲና ገዳምም የሚገኘው ከሲና ተራራ ጋር አቻ ስያሜ በተሠጠው ተራራ ላይ ነው። ተራራ በአብዛኛው ሀይልን፣ ከፍታን፣ ልእልናን፣ ቅድስና ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሄር (አላህ) ህልውና መዝለቅን እና ሞትን እስከማሸነፍ የሚዘልቅ ትርጉም እንዳለው (ፈበር፣ 2007፣ 131) ገልጿል። በተመሳሳይ መልኩ ተራራ ሁሉን ለማየት እና ተቆጣጥሮ ለመግዛት (ስጋን ለማሸነፍ) የሚያስችል ስልታዊ ጠቀሜታ እንዳለው (ቴዎድሮስ፣2001፣117) ገልጸዋል። የጡሩሲና ገዳም ከስያሜው ባሻገር ተራራ ላይ መመስረቱ ገዳማውያኑ አለማዊውን (ለስጋ ማደርን) ትተው ለነፍሳቸው እንዲተጉ ብሎም በህይወታቸው ላይ ልእልና እና ቅድስና እንዲገናጸፉ በማሰብ የተደረገ ነው ማለት ይቻላል።

የጡሩሲና "ገዳም" የሚገኘው ከከሚሴ ሰሜን አቅጣጫ 16 ኪሎ ሜትር ወደ ዉስጥ ገባ ብሎ ጡሩሲና ተብሎ በሚጠራው መንደር ነው። "ገዳሙን" የመሰረቱት መሀመድ አማን[4] የሚባሉ ሼህ ናቸው። ሼሁ ጡሩሲናን ከመመስረታቸው በፊት አማን አምባ በሚባለው መስጊድ ውስጥ በደረሳነት እና በነዳሚነት አገልግለዋል። በ1963 ዓ.ም አማን አምባን ለቀው ጡሩሲና በመምጣት አንድ ጎጆ ብቻ በመስራት "ገዳሙን" አቋቋሙ። ሼሁ "ህልም እስኪታየኝ ድረስ አይሰራም"[5] በማለታቸው አሁን የሚገኘው ዋናው መስጊድ እስከ 1973 ዓ.ም ድረስ አልተሰራም ነበር። ከአስር አመት ቆይታ በኋላ የተጀመረው የዋናው መስጊድ ስራ ሶስት አመት ተከል የወሰደ ሲሆን በአካባቢው ነዋሪዎች ትብብር እንደተሰራ አቶ መሀመድ አማን[6] ይገልጻሉ (ቃ.መ፣ጥር 27/2004፣ጡሩሲና)።

---

[4] የሼህ መሀመድ አማን የህይወት ታሪክ በጥናቱ መጨረሻ በአባሪነት ተካቷል።
[5] በአለም አቀፍ ደረጃ የገዳም ህይወት ጀማሪን ገዳምን ለመመስረት መንስኤው ህልም ነው።
[6] አቶ መሀመድ አማን የሚኖሩት ቀበሌ 10 ሼክላ ተብላ በምትጠራ መንደር፣ እድሜአቸው 55፣ መተዳደሪያቸው ግብርና፣ባለትዳር እና የ3 ልጆች አባት፣ በአካባቢው ማህበረሰብ በሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ ሽማግሌ/አስታራቂ ናቸው።



"ገዳሙ" በሳርና በጭድ የተሰራ ሲሆን ስፋቱ 625 ካሬ ሜትር ነው። ከትልቅነቱ የተነሳ የውጭ ምሰሶዎች 85፤ የውስጥ ምሰሶ 40 (41 ነበር አንዱ በቅርብ ፈርሶ ነው) እና ዋናው የመሀል ምሰሶው ወደ ጎን ርዝመቱ 33 ሜትር ነው። አምስት የሚደርሱ መግቢያ በሮች አሉት።

ከዋናው መስጊድ በተጨማሪ በርካታ ክለዋዎች ተሰርተዋል። በአሁኑ ወቅት የወንዶቹ ክለዋዎች በቁጥር እስከ 170 እንደሚደርሱ ይገመታል። ሼሁ በየጊዜው እየፈረሱ እንዲሰሩ ስለሚያዙ የወንዶቹ ክለዋዎች ቁጥር በትክክል አይታወቅም (የቡድን ውይይት፣ 13/09/04፣ ጡሩሲና)።[8] በወንዶቹ "ገዳም" ከመኖሪያነት በተጨማሪ ሌሎች ግልጋሎቶችን የሚሠጡ ክለዋዎች አሉ። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሲጋ፣ የቡና፣ የእቃ እና የማር ቤት ናቸው።

---

[8] ከዚህ በኋላ የቡድን ውይይትን የቡ.ው በማለት የምጠቀም ይሆናል።

የስጋ ቤት፡- የዚህ ክፍል ዋነኛ ተግባር ከብቶች ከታረዱ በኋላ ስጋውን "ለገዳማውያኑ" ማድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የውሀ ማጠራቀሚያዎች፣ የስጋ ማስቀመጫ ገንዳዎች፣ የስጋ መቀቀያ በርሚሎች፣ ከእንጨት የተሰሩ ባለ መንታ ምሰሶዎች፣ የስጋ መክተፊያ ጣውላዎች፣ የበሰለ ስጋ ማስቀመጫ የእንጨት ገበቴዎች እና የስጋ ማማሰያ ማንኪያዎች ይገኛሉ።

የቡና ቤት፡- "ለገዳሙ" ህብረተሰብ የሚቀርበው ቡና የሚዘጋጅበት ቤት ነው። በክፍሉ የሚገኘው ረከቦት ርዝመቱ ሁለት ሜትር ሲሆን በአንድ ጊዜ 190 የሚደርሱ ስኒዎችን መደርደር ይችላል። የእንስራ መጠን ያላቸው ከብረትና ከሸክላ የሚሰሩ ባለ ሁለት ጡት ጀበናዎች፣ የእህል መውቀጫ ያህል መጠን ያላቸው የቡና መውቀጫዎች፣ የቡና ማፍያ እና የንፍሮ መቀቀያ በርሚሎች በብዛት ይገኛሉ።

የእቃ ቤት፡- ቤቱ "ለገዳሙ" አጠቃላይ ግልጋሎት የሚሰጡ እቃዎችን ይቀመጡበታል። ከእቃዎቹም ውስጥ ድቤዎች፣ ቋርአኖች፣ ሞሰቦች፣ ሳህኖች፣ ቁናዎች፣ የጥቃቅን እቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች እና ፋኖሶች ይጠቀሳሉ።

የማር ቤት፡- ይህ ቤት በጾም ጊዜ እና በተለያዩ ዝግጅቶች የማር ስጦታ የሚበረከትበት እና ማሩ እየተበጠበጠ "ለገዳማውያኑ" የሚቀርብበት ነው። ማንቆረቆሪያ፣ ብርጭቆ እና ማሩን ለመበጥበጥ የሚያገለግሉ ገንቦዎች ይቀመጡበታል።

ይህን መሰል ገጽታ ባለው "ገዳም" ውስጥ ሙስሊሞች ራሳቸውን ከአካባቢው ማህበረሰብ ሙሉ ለሙሉ አግልለው መንፈሳዊ ህይወታቸውን ይመራሉ። "በገዳሙ" ሴቶችና ወንዶች ለየብቻ ተነጥለው ከማንም ጋር አይገናኙም። "በገዳሙ" ውስጥ 111 ሴቶች እና ከ200 የሚበልጡ ወንዶች በቋሚነት የሚኖሩ ሲሆን የሴቶቹ እና የወንዶቹ መኖሪያ እና መስገጃ ቦታ ለብቻ የተከለለ ነው። "ገዳማውያኑ" በመጾም እና በመጸለይ፣ የሀይማኖቱን ትምህረት በመማር፣ እምነቱን ለማስተማር የሚረዱ ጽሁፎችን በመከተብ እና ኪታቦችን በማዘጋጀት ጊዜአቸውን እንደሚያሳልፉ ይናገራሉ (ቃ.መ፣ 01/06/04፣ አቶ መሀመድ አማን፣ ሼክላ)።

"በገዳሙ" ውስጥ የወንዶቹ ቁጥር እስከ 200 እንደሚደርስ ቢገመትም በትክክል አይታወቅም። አንዳንድ ወንዶች ለማግባት ሲያስቡ "ገዳሙን" ትተው ስለሚወጡ ነው። ማግባትን በተመለከተ ሼሁ "ጓንባ ነው" የሚሏቸውን ደረሳ መርቀው ይልካሉ። አንድ ደረሳ ካገባ በኋላ

በድጋሚ ወደ "ገዳሙ" መጥቶ እንዲኖር አይፈቀድለትም። ምክንያቱም ሚስት ካገባ ሚስቱን መንከባከብ እና ቤተሰቡን መመገብ ስላለበት ነው።

"በገዳሙ" ውስጥ የሚኖሩ ወንዶች ከሀይማኖታዊ ተግባር በተጨማሪ በቋሚነት የሚሰሯቸው ስራዎች የሉም። አልፎ አልፎ ማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀል ጫት መትከል፣ የሞተ ሰው ካለ መቅበር፣ ሰደቃ ካለ ዱአ ማድረግ እና መሰል ስራዎችን ይሰራሉ። "ገዳሙ" ውስጥ ስራ ለመስራት የሚያስችል ትርፍ ቦታ ቢኖርም ስራ እንዲሰሩ ሼሁ አይፈቅዱም። ምክንያቱም "አለማዊ ስራዎችን በስሩ ቁጥር ነፍሳቸው ወደ አለማዊው ህይወት ትወሰዳለች ስለዚህ መስራት የለባቸውም" የሚል አቋም ስላላቸው ነው። በዋናነት የምግብ ምንጫቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ሲሆን ለቁርአ በማለት ምግብ ከጠየቁ የሚመልሳቸው የለም።

ሴቶቹ "በገዳሙ" መኖር የጀመሩበት ጊዜ ባይታወቅም የ77 ድርቅ አልፎ አንድ ጊዜ አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ እንደሆነ ይናገራሉ። ከቀዳሚዎቹ ውስጥ ሰይላ ሼህ ኢብራሂም፣ መሬማ ሀሰን፣ በህያሽ አህመድ ኑር፣ ሉባባ ጦይብ እና ሳዲያ ኡመር የተባሉ አምስት ሴቶች ይገኛሉ። የጡሩሲና "ገዳም" በርካታ "ገዳማውያንን" በውስጡ አቅፎ የያዘ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደ "ገዳሙ" ለመግባት የሚመጡ ሰዎች ቁጥር በመብዛቱ ተጨማሪ ሰው ላለመቀበል እንደወሰኑ ይናገራሉ (የቡ.ው፣ 13/09/04፣ ጡሩሲና)።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

"በገዳሙ" ለመኖር የሚመጡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደመጣ ከፍ ሲል ተገልጿል። በዚህ "ገዳም" ላይ ጥናት እንዳደርግ ያነሳሱኝ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

ተወልጄ ያደኩበት ወሎ/ደሴ የእስልምና እና የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ተዋደው እና ተከባብረው የሚኖሩበት አካባቢ ነው። እኔም በዚህ ባህል ውስጥ አልፌአለሁ። የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ብሆንም ከክርስትያን ጓደኞቼ ጋር ቡሄን ጨፍሬአለሁ፣ ታቦት ሸኝቼአለሁ፣ ግንቦት ልደታን አክብሬአለሁ። ጓደኞቼም የክርስትና ሀይማኖት ተከታይ ቢሆኑም የረመዳንን ጾም ከኔ ጋር ጾመዋል፣ መስጊድ በመሄድ ቁርአን ቀርተዋል።

ለእምነቱ እና ለአካባቢው ቅርብ መሆኔ ጥናቱ ከመደረጉ በፊት "ስለገዳሙ" ጥቂት መረጃዎች እንዲኖረኝ አስችሏል። "ገዳሙን" ጎብኝተው እና "በገዳሙ" የሚከበሩ በአላትን አክብረው የሚመጡ የአካባቢያችን ሙስሊሞች ከመስጊዱ ሳይወጡ በቋሚነት የሚኖሩ ሰዎች መኖራቸውን በግርምት ሲያወሩ እሰማ ነበር። በእስልምና ሀይማኖት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች መስጊድ ሄደው ሰግደው እና ቁርአን ቀርተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ እንጅ በቋሚነት መስጊድ ውስጥ አይኖሩም። በተቃራኒው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ አማንያን እንዲህ አይነት ስርዓት እንዳላቸው አውቅ ነበር። እንዲህ አይነቱ የኑሮ ስርዓት ደግሞ ገዳማዊነት/የምንኩስና ኑሮ እንደሆነ ይታወቃል።

የፎክሎር ተማሪ መሆኔ በመስጊዱ ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ ሰዎች ካሉ እና ኑሮአቸውን በዚያ ከመሰረቱ ክርስቲያኖች ገዳም ብለው ከሚጠሩት ስርዓት ጋር ይመሳሰላል ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት መነሻ ሆኖኛል። "ገዳማዊ ህይወት" በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ የተለመደ አለመሆኑ እንዳጠናው መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል። በተጨማሪም "በገዳሙ" ዙሪያ በአካዳሚው አለም የተጠና ስራ አለመኖሩ ይበልጥ እንዳተኩርበት ምክንያት ሆኗል።

በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በክርስትና ሀይማኖት ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ ማጥናት በተወሰነ ደረጃ እየተለመደ መጥቷል። በአንጻሩ በእስልምና ሀይማኖት ተቋማት የተደረጉ ጥናቶች የሉም። ይህ ጥናት በትምህርት ክፍሉ ያለውን የእውቀት ክፍተት በከፊል ለመሙላት አስፈላጊ መሆኑን በማመኔ እንዳጠናው ሆኗል።

ከላይ በተዘረዘሩት አንኳሽ ምክንያቶች የተሰራው ይህ ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች አንስቷል።

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ በሁለት አበይት እና በአራት ዝርዝር ጥያቄዎች ላይ አተኩሯል። ቀዳሚው የሙስሊም "ገዳማዊ አኗኗር" በአገራችን እንዴት ሊኖር ቻለ? ሲሆን ተከታዩ "በገዳሙ" ውስጥ የሚከወኑ ከበራዎች ከሀይማኖታዊነታቸው በተጨማሪ ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው? የሚሉ ናቸው።

ከእነዚህ ሁለት የምርምር ጥያቄዎች የወጡ ዝርዝር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. "ገዳሙ" እንዴት እና በማን ተመሰረተ?
2. "ገዳሙ" የሚገኝበት አካባቢ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶች ምን ይመስላሉ?
3. "በገዳሙ" የሚከበሩ ክብረ በአላት ምን ምን ናቸው? እንዴት ይከበራሉ?
4. "ገዳሙ" "ለገዳማውያኑ" እና ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ ምንድን ነው? ለሚሉት ዝርዝር ጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን አልሞ ተነስቷል፡፡

## 1.4. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሙስሊም "ገዳም" እንዴት ሊኖር እንደቻለ "ከገዳሙ" አመሰራረት እና በአገራችን ካለው የሀይማኖቶች የመቻቻል ባህል አንጻር ማሳየት እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ ክበራዎች ከሀይማኖታዊነታቸው በተጨማሪ በውስጣቸው የያዟቸው ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ለይቶ ማጥናት ነው፡፡ በተያያዥም በሀይማኖቱ እና በባህሉ መካከል ያለውን ትስስር ማመላከት ነው፡፡

ከዋና አላማው የወጡ ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. "የገዳሙን" ታሪካዊ ዳራ እና አስተዳደራዊ መዋቅር በማጥናት "ገዳሙን" "ገዳም" ብሎ መጥራት እንደሚቻል ማመላከት፤
2. "ገዳሙ" የሚገኝበትን አካባቢ ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ትስስሮችን በማሳየት "የገዳሙን" አስተሳሰብ ከፍት መጣኑት መግለጽ፤
3. "በገዳሙ" ውስጥ ከሚከበሩ በአላት መካከል ሁለቱን በመለየት ፎክሎራዊ ገጽታቸውን እና ፋይዳቸውን በመግለጽ የአክባሪዎችን ማንነት ማስረዳት፤
4. "የገዳሙን" ጠቀሜታ "ከገዳማውያኑ" እና ከአካባቢው ማህበረሰብ አንጻር መግለጽ ናቸው፤

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የጥናቱ ጠቀሜታ ከአካዳሚያ፣ "ከገዳማውያኑ" እና ከአገራችን ባህል አንጻር በሶስት ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.5.1. ከአካዳሚያ አንጻር፦

"የገዳሙ" መመስረት በእስልምና አስተምህሮት ውስጥ የተለመደ ባለመሆኑ ጥናት አልተደረገበትም። ይህ ጥናት መደረጉ በአካዳሚው እውቀት ላይ አዲስ ነገር ይጨምራል። "በገዳሙ" እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ታሪክ ለመጻፍ እንዲሁም "ገዳሙን" ከኦርቶዶክስ ክርስትና ገዳማት ጋር ካለው ተመሳስሎና ልዩነት ላይ መስራት ለሚያስብ ተመራማሪ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።

### 1.5.2. ከ"ገዳማውያን" አንጻር፦

"ገዳሙ" የሚገኝበት አካባቢ ምንም ዓይነት የመሠረተ ልማት አውታር የለም። መንገዱም አመቺ አይደለም፣ የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት የለም፣ አንዳንዴም የምግብ እጥረት ስለሚያጋጥም "ገዳማውያኑ" ይቸገራሉ። ይህ ጥናት "የገዳማውያኑን" ችግር ለሚመለከተው አካል ያመላክታል።

### 1.5.3. ከአገራችን ባህል እና ታሪክ አንጻር፦

የነቢዩ መሀመድ ተከታዮች ከጠላቶቻቸው ለመሸሽግ የመረጧት አገር ኢትዮጵያ ናት። በጊዜው የነበረው የክርስትያን ንጉስ ከለላ ለማግኘት የመጡትን ስደተኞች ከለላ ሰጥቷቸዋል። በዚህም ከጠላት የመጣለትን ስጦታ "አልቀበልም" በማለት የነቢዩን ተከታዮች ህይወት ታድጓል (ስፔንሰር፣1952፣45)። በዚህ መልኩ ወደ አገራችን በገባው እስልምና እና በክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች መካከል ለዘመናት ተቀራርቦ እና ተቻችሎ የመኖር ባህል ዳብሯል። በአገራችን የሙስሊም "ገዳም" እንዴት ሊኖር እንደቻለ፣ "የገዳሙን" አመሰራረት እና አጀማመር፣ መተዳደሪያ ህግ እና ደንብ፣ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ያለውን ተዛምዶ እና ልዩነት ማጥናቱ በሁለቱ ሀይማኖቶች መካከል ያለውን ጥብቅ ትስስር ማሳያ በመሆን ያገለግላል። በተጨማሪም አንዱ ሀይማኖት በሌላው ሀይማኖት ላይ የሚያሳድረውን በጎ የሆነ የመወራረስ ባህሪን ያመላክታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየሀይማኖቶቹ መካከል እየታየ ያለው የግንኙነት መላላት እና መሻከር ሁለቱ ሀይማኖቶች ለዘመናት ጠብቀው ያቆዩአቸው የጋራ እሴቶች እየጠፉ እና እየተረሱ መሆናቸውን የሚያመላክቱ ናቸው። ይህ ጥናት እየጠፉ እና እየተረሱ ያሉ እሴቶችን ለማስታወስ እና ለንጾ ለማስቀመጥ ያገለግላል። በአገራችን እየላላ (እየሻከረ) የመጣው

የመቻቻል እና አብሮ የመኖር ባህል እንደገና ለማስቀጠል (ሀይማኖትን መሰረት አድርገው የሚሰሩ አካላት እንደ ግብአትነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ ብዬ አምናለሁ) ጡሩሲና እና መሰል ሀይማኖታዊ እሴቶች መጠናታቸው አስፈላጊ እና ጠቃሚ ነው።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

በኦሮሚያ ዞን ውስጥ ከስምንት በላይ ጥንታዊ መስጊዶች ይገኛሉ። ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ዳዋ ጨፋ ወረዳ በመባል በሚጠራው ስፍራ በታሪካዊ ቅርስነት ሰፍሮ በሚገኘው ጡሪሲና የሙስሊም "ገዳም" ላይ ነው። ጥናቱ የጡሩሲና መስጊድ "ገዳም" መሆን አለመሆኑን፣ "የገዳሙን" አመሰራረት እና "በገዳሙ" ውስጥ በሚከወኑ ክብረ በአላት በሁለቱ፣ በአመት አንዴ የነቢዩ መሀመድ ልደትን በማሰብ "በገዳማውያኑ" እና በአካባቢው ማህበረሰብ በሚከበረው የመውሊድ በአል እና በሴት "ገዳማውያን" ብቻ በሚከበረው የሰርግ ስርአት ላይ ብቻ ያተኩራል። "በገዳሙ" ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች፣ የአለባበስ እና አጊያጊያጥ ስርአቶች፣ የህክምና እና ስርአተ ቀብር ክዋኔዎች እና "የገዳማውያኑ" የግል እና የወል ትረካዎች የጥናቱ ትኩረት አይደሉም።

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ እና የአተናተን ዘዴ

ይህ ንኡስ ርእስ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች እንዴት እንደተሰበሰቡ እና መረጃዎቹ በምን መንገድ እንደተተነተኑ የሚያሳዩ ሀሳቦችን ይዟል።

### 1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ክዋኔን ማእከል ባደረገ ጥናት ተፈጥሯዊ አውድ መኖር እንዳለበት እና በመቼቱ ያየናቸውን ሁሉ መመዝገብ አስቸጋሪ ቢሆን እንኳ ልዩ እና ወሳኝ የሆኑ ክስተቶችን የግድ መሰነድ እንደሚያስፈልግ (ባውማን፣1992፣252) ያስረዳል። በመስክ ምርምር ለጥያቄዎቻችን መልስ ለማግኘት የምንጠቀምባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል የምልከታ ዘዴ፣ የቃለ መጠይቅ ዘዴ፣ የቡድን ውይይት እና የጽሁፍ መጠይቅ በዋቢነት ይጠቀሳሉ (ኮታሪ፣ 2004፣96)። በዚህ ጥናት ተተኳሪዎቹ ማንበብ እና መጻፍ ስለማይችሉ ከጽሁፍ መጠይቅ ውጭ ሌሉች ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

### 1.7.1.1. የምልከታ ዘዴ

በአውዳዊ ጥናት መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች ውስጥ ምልከታ አንዱ ነው። ጎልድስቴን (1964፣77) ምልከታ በቀጥታ የእይታ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የስሜት ህዋሳት በጋራ የሚያሳትፍ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው ይላል። በተመሳሳይ መልኩ ኮታሪ (2004፣96) በዚህ ዘዴ መረጃ የምንሰበስብ ከሆነ ምልከታውን ከመጀመራችን በፊት ምን መመልከት አለብን? እንዴት መመልከት የተሻለ ነው? ምልከታውን እንዴት መቅረጽ አለብን? ማስታወሻ አወሳሰዳችን እንዴት ቢሆን ይመረጣል? የምልከታችንን ትክክለኛነት በምን መንገድ እናረጋግጣለን? በሚሉ ጥያቄዎች ላይ አስቀድሞ መዘጋጀት አለብን ይላል። ከዚሁ ጋር አያይዞ ጎልድስቴን የምልከታችን የትኩረት ነጥብ አካላዊ አውድ፣ ማህበራዊ አውድ፣ በከዋኙ እና በተሳታፊው መካከል ያለው መስተጋብር፣ ክዋኔ፣ የሚከወንበት ጊዜ እና ሰአት፣ የስሜት ገለጻ፣ የሚከወንበትን አጋጣሚ እና ራሱ አጥኚው ሲሆኑ ይገባል ሲል ይገልጻል (1964፣91-93)። እነ ሲምስ (2005፣131) በመስክ ስራ አጥኚው የሚፈጽመውን ተግባርና ተግባቦት መነሻ አድርጎ በሰላና በነቃ መንፈስ ምልከታውን የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም በመከታተል መጀመር አለበት ይላሉ። አጥኚው ትኩረት ማድረግ የሚገባው ጥበባዊ ተግባቦት እና ጥበባዊ ገለጻ ላይ መሆን እንዳለበት አክለው ይገልጻሉ። በማስከተልም ክዋኔው የት፣ መቼ፣ ከማን ጋር፣ ለምን ተከወነ፣ ምን ይዘት አለው፣ በክዋኔው የሚስተዋሉ ቃላቶች፣ ድርጊቶች፣ ቴክስቸሮች እና አውዶች ምን ገጽታ አላቸው የሚሉትን ማየት ግድ እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

ምልከታ ሁለት አይነት ነው። የመጀመሪያው ተሳትፎአዊ ምልከታ ነው። በዚህ ዘዴ ለመጠቀም አጥኚው ለጥናት በመረጠው ማህበረሰብ ውስጥ ተወልዶ ማደግ እና የባህሉ ባለቤት ወይም ባህሉን እና ቋንቋውን አውቆ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይኖርበታል።

ሁለተኛው የምልከታ አይነት ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ሲሆን አጥኚው ስለሚያጠናው ማህበረሰብ እና ባህል እውቀት ሳይኖረው ዳር ላይ ሆኖ በመመልከት መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው (ኮታሪ፣2004፣96)። በዚህ ጥናት የገዳማውያኑ ቋንቋ እና ባህል ባለመታወቁ መረጃ የተሰበሰበው ተሳትፏዊ ባልሆነ ምልከታ ነው። "በገዳማውያኑ" እምነት ለማግኘት ሲባል ከፊል

ሊባል በሚችል ተሳትፎ ቁርአን በመቅራት፣ በመስገድ፣ ጫት በመቃም፣ ዱአ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ኮታሪ የምልከታ ስልቶችን ውስን ምልከታ (structured) እና አስቀድሞ ያልተወሰ ምልከታ (unstructured) በማለት በሁለት ከፋፍሎ አስቀምጧቸዋል። በውስን ምልከታ አጥኝው ከሚከወነው ክዋኔ "ይህንን ብቻ ነው የማየው ሌላው የኔ የጥናት አካል አይደለም" በማለት ወስኖ እና መርጦ የሚመለከትበት ነው። ይህ ዘዴ ጊዜን ከመቆጠብ አንጻር ተመራጭ ነው። በተቃራኒው ውስን ያልሆነ ምልከታ የክዋኔው ህግ እና ደንብ ለማየት የፈቀደልልን ሁሉ (ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ) የምንመለከትበት እና ያገኘናቸውን መረጃዎች ሁሉ የምንወስድበት የምልከታ ስልት ነው (2004፣96)። ለዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው አስቀድሞ ባልተወሰነ ምልከታ ነው። ለዚህ ምክንያቱ በአንድ ክዋኔ ላይ ሁሉም የፎክሎር ዘርፎች ተሰናስለው እና ተያይዘው እንደሚቀርቡና አንዱን ብቻ ነው የምመለከተው ብሎ መነጠል አስቸጋሪ በመሆኑ ነው(ሲምስ፣2005፣128)። የእነ ሲምስ ሀሳብ በክዋኔው ላይ የጥናቱ ትኩረት ያልሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ብንመለከታቸው ስለምንፈልገው ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት እንደሚያግዘን ያስገነዝባል። ለምሳሌ የዚህ ጥናት ትኩረት ተረክ ላይ ባይሆንም በክዋኔው ላይ አልፎ አልፎ የሚነገሩ ተረኮች ተሰብስበዋል። ተረኮቹ መሰብሰባቸው ክብረ በአሉ ለታዳሚያኑ የሚሰጡትን ፋይዳ ለማመላከት አስችለዋል።

ይህ ጥናት የምልከታ ዘዴን መጠቀሙ የጥናቱ ዋና አላማ የሆኑት ከበራዎች እንዴት እንደሚከበሩ፣ እነማን እንደነበሩ፣ እንዴት ተጀምረው እንዴት እንደሚጨረሱ፣ በከዋኝ እና በተሳታፊ መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል፣ በከበራው ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች ከከበራው ጋር ያላቸው ዝምድና ምን እንደሆነ፣ በአጠቃላይ "የገዳማውያኑን" እና የክብረ በአላቱን ማህበራዊ እና ባህላዊ አውድን ለመገንዘብ እና ለመረዳት ነው።

የምልከታ ዘዴ ከቃለመጠይቅ እና ከቡድን ውይይት ዘዴዎች በተሻለ ከመረጃ አቀባያችን የግል ስሜት እና አስተሳሰብ ውጭ የሆነ መረጃ እንድናገኝ ይረዳል። በተለይ የማህበረሰቡ አባል ከሆንን ክዋኔውን በሚከውኑበት ጊዜ እውነተኛውን መረጃ ሊነግሩን እና ሊያሳዩን ስለሚችሉ ትክክለኛ መረጃ እናገኛለን። ከዚህ በተጨማሪም የምናጠናውን ማህበረሰብ ባህላዊ እና ማህበራዊ አውዶችን በስፋት ለመገንዘብ እና ለመረዳት ያስችላል (ኮታሪ፣ 2004፣ 97 እና ጎልድስቲን፣ 1964፣ 78) በማለት ይገልጻሉ።

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ጠንካራ ጎኖች ያሉትን ያህል ድክመቶችም አሉበት። ከእነዚህም መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው አጥኚው በክዋኔው ውስጥ የፎቶግራፍ እና ቪዲዮ ካሜራ ይዞ ሲገኝ በከዋኞቹ ላይ ጥርጣሬን በመፍጠር ነጻ ሆነው ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ላይከውኑልን ይችላሉ የሚል ስጋት ነው። በዚህ የተነሳ የመረጃ ክፍተት ሊኖር ይችላል። በዚህ ጥናትም የቃለ መጠይቅ ዘዴ ክፍተቱን ሊሞላ ስለሚችል ተግባር ላይ ውሏል።

### 1.7.1.2. የቃለ መጠይቅ ዘዴ

ቃለ መጠይቅ በዋናነት "ጥገዳሙን"፣ አመሰራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የሴቶች እና የወንዶች ስራ ድርሻ እና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተርጎም አገልግሏል። ጎልድስቴን ሁለት አይነት የቃለ መጠይቅ ቴክኒኮች መኖራቸውን አስፍሯል። እነዚህም ቀጥተኛ ያልሆነ/ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ ቀጥተኛ /የተገደበ ቃለ መጠይቅ ናቸው።

በቀጥተኛ ያልሆነ/ያልተገደበ የቃለ መጠይቅ ቴክኒክ ወደ ዋናው ጉዳያችን በቀጥታ ገብተን መረጃ የሚሰጡንን ሰዎች አንጠይቅም። ለምናነሳቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ የሆነ ምላሽ አገኘንም አላገኘንም ሳናቋርጥ በትኩረት ማድመጥ/መመልከት ተመራጭ ይሆናል (ጎልድስቴን፣ 1964፣ 108)። ቴክኒኩ ለጠያቂው እና ለመረጃ ሰጪው ነጻነት ይሰጣል። አጥኚው በዚህ መንገድ መረጃ ሲሰበስብ አስቀድሞ ያዘጋጀው የተወሰኑ ጥያቄዎች ቢኖሩት እንኳ በመጠይቁ ወቅት የሚጨምራቸው በርካታ ጥያቄዎችን እንዲያነሳ እድል ይፈጥራል። እንዲህ መሆኑ ለአጥኚው የሚፈልገውን መረጃ ከማስገኘቱ በተጨማሪ መረጃ ሰጪዎቹ ነጻነት እንዲሰማቸው በማድረግ መልካም ግንኙነት እንዲፈጥር ያስችለዋል (ኮታሪ፣2004፣98)። ጎልድስቴን (1964፣108) ይህንን ዘዴ የሚጠቀም አጥኚ ጥልቅ እውቀት እና ብስለት ያለው መሆን አለበት በማለት ይገልጻል።

በቀጥተኛ /በተገደበ ቃለ መጠይቅ ደግሞ የመጀመሪያውን/ቴክኒክ ተጠቅመን መልካም የሆነ መግባባት ከመረጃ አቀባዮቻችን ጋር ከፈጠርን በኋላ ታስቦባቸው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን የምንጠይቅበት እና ምላሽ የምናገኝበት ነው (ጎልድስቴን፣1964፣110)። ይህ የቃለ መጠይቅ ቴክኒክ አጥኚው ካዘጋጃቸው ጥያቄዎች ውጭ ሌላ የማይጠይቅበት፣ መረጃ አቀባዩም ከሚጠየቀው ውጭ ሌላ መረጃ ለማቀበል እድል የማያገኝበት ነው (ኮታሪ፣2004፣98)።

በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋሉት ሁለቱም የቃለ መጠይቅ ቴክኒኮች ናቸው። ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር በደንብ እንድንተዋወቅ እና በጥናቱ ላይ እምነት እንዲኖራቸው አድርጌአለሁ። ስለ ማንነቴ፣ ስለ ቤተሰቤ እና ስለምሰራው ስራ በመተረክ እንዲሁም ስለ መረጃ አቀባዮቼ የህይወት ታሪክ፣ ስራ፣ አኗኗር በማድመጥ በመሀል በመሀል የምፈልገውን ጥያቄ በማንሳት መረጃ ለመሰብሰብ አስችሎኛል። የተዘለሉ እና የተቆራረጡ ሀሳቦችን ቀጥተኛ ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ሰብስቤአለሁ። በመጀመሪያው ቴክኒክ በፈጠርኩት መግባባት መረጃ አቀባዮቼ ከምጠይቃቸው ጥያቄ በተጨማሪ "እንዲህ አይነት ነገር አለ የሚጠቅምሽ ከሆነ" በማለት ጠቃሚ ነገሮችን ሊሰጡኝ ችለዋል።

ለእነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ ለማግኘት ሲባል የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። በመጀመሪያም "በገዳሙ" የስልጣን መዋቅር ውስጥ ሰፊውን ቦታ የሚሸፍኑት እና አስፈላጊነታቸው የጎላ የሆኑት ተካተዋል። ከዚህ በተጨማሪም በሀይማኖታዊ እውቀታቸው የላቁ፣ እንዲሁም ወደ "ገዳሙ" ከተቀላቀሉ ቅርብ ጊዜ የሆናቸው "ገዳማውያን" ተመርጠዋል። በመጨረሻም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለተወሰኑ "ገዳማውያን" ጥያቄዎች ማቅረብ ተችሏል። ይህም ቃለመጠይቅ ከተመረጡት መረጃ አቀባዮች የተገኘውን ሀሳብ ለማመሳከር ጠቅሟል። ጎልድስቴን መረጃ አቀባይ ለቃለ መጠይቁ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ገልጾ ስንተንትን የመረጃ አቀባዩን ማንነት በአጭሩ ማስፈር እንዳለብን ጽፏል። እነዚህም ሙሉ ስም፣ መኖሪያ አድራሻ፣ የትውልድ ቦታ እና ቀን፣ የቤተሰቡን አባል፣ የቤተሰቡን ታሪክ፣ ዘር፣ የትምህርት ሁኔታ፣ የተጓዙባቸው ስፍራዎች፣ የስራ መደብ፣ የጤና ሁኔታ፣ የተለየ ችሎታ እና ክህሎት፣ የሚከተለው ሀይማኖት፣ በሌላ ተቋም ያለው ሀላፊነት፣ አላማ እና ራእይ ናቸው (1964፣126)። ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ የመረጃን ትክክለኛነት ለመመዘን የሚያስችለን ዘዴ የቡድን ውይይት ነው።

### 1.7.1.3. የቡድን ውይይት

የቡድን ውይይት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የሰበሰብናቸውን መረጃዎች ትክክለኛነት የምንመዝንበት እና የምናረጋግጥበት ዘዴ ነው። ዘዴው ከሌሎቹ ዘዴዎች በተለየ የመረጃችንን ትርጉም እንድንገልጻ ያስችለናል።[5] የቡድን ውይይት የተመረጠበት ምክንያትም በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት ተሸፋፍነው ያለፉ፣ ግልጽነት የጎደላቸውን መረጃዎች "ገዳሙን" እና

---

[5] ፎክሎር ፊልድ ሜቶድ የሚባለውን ኮርስ ስንወስድ ከመምህራችን ዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው የተወሰደ ሀሳብ

ስርአቱን በትክክል ያውቁታል ተብለው የታመነባቸውን ሰዎች በማወያየት የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ነው።

### 1.7.2 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ገላጭ የምርምር ስልት (Descriptive Method) ተመርጧል። ይህ ዘዴ መመረጡ "የገዳሙን" መልክአምዳዊ አቀማመጥ፣ አመሰራረት፣ ድባብ እና የሚከበሩ በአላት ግልጽ እና ምስል ከሳች በሆነ ሁኔታ ለመግለጽ እንዲረዳ ነው። መረጃው በፈቀደው ልክ እና መጠን እንደ አስፈላጊነቱ ፍካሬ (Interpretation) ተካቷል።

## 1.8. የመስክ ጥናት ገጠመኝ

በዚህ ርእስ ላይ መረጃ ለማሰባሰብ ስነሳ "ገዳሙን" በስም እንጂ አይቼው ስለማላውቅ የመጀመሪያ ተግባሬ "ገዳሙን" ማየት እና የምፈልገው መረጃ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ነበር። ይህንን ታሳቢ ያደረገው የመጀመሪያ ጉዞዬ የተካሄደው እርብ ታህሳስ 20/05/04 ሲሆን የሄድኩትም ከአባቴ ጋር ነበር። የጡሪሲና "ገዳም" የሚገኘው ከአዲስ አበባ ደሴ መንገድ በሱሉልታ እና በሀርቡ መካከል ሼከላ ተብላ በምትጠራ ትንሽ መንደር ውስጥ ነው። ወደ ጡሪሲና "ገዳም" መሄድ የፈለገ ሰው ሼከላ የምትባለው መንደር ከደረሰ በኋላ ወደ "ገዳሙ" ለመድረስ የሚቀረውን 5 ኪሎ ሜትር ለማጠናቀቅ ባጃጆችን ይጠቀማል። እኛም ሰላሳ ደቂቃ ያህል የወሰደው የባጃጅ ጉዞ ጨርሰን ለመውጣት ሳይሆን ለማየት አስፈሪ ከሆነ ተራራ አጠገብ ደረስን እና ወደ "ገዳሙ" የሚወስደውን መንገድ የሚጠቁመን ሰው እስክናገኝ ድረስ ቆምን። አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉት የአካባቢው ነዋሪዎች ኦሮምኛ ብቻ ተናጋሪ ስለነበሩ አማርኛ ተናጋሪ ሰውን ለማግኘት ብዙ ደቂቃዎች ጠበቅን።

በግምት ከሀያ ደቂቃ በኋላ አማርኛ የሚናገሩ ሰው ብናገኝም ሌላ ፈታኝ ሁኔታ አጋጠመን። ይህም የወንዶቹና የሴቶቹ መግቢያ ስለሚለያይ ተራራውን ብቻየን መውጣት ነበረብኝ። አባቴ እኔን ጥሎ ለመሄድ ፈቃደኛ ባለመሆኑ እኔም ብቻዬን ለመሄድ ስላልደፈርኩ ከሴቶቹ መግቢያ ድረስ ሸኝቶኝ ሊመለስ ተስማምተን በግምት አንድ ሰአት የወሰደብንን ጉዞ አጠናቀን ከሴቶች መግቢያ ስንደርስ አባቴ ተመልሶ ወደ ወንዶች መግቢያ ሄደ። ወደ ሴቶቹ መግቢያ ስቃረብ

ወ/ሮ የሺ ፋጢማ[9] የተባሉ የአካባቢ ነዋሪ የሆኑ ሴት አገኘሁ። የሴቶቹ መግቢያ ዙሪያውን በትላልቅ ቁልቋሎች የተከበበ ሲሆን የመግቢያ በሩ ስፋትም አንድ መኪና ማስገባት የሚያስችል ነው። ይህንን በር አልፎ ለመግባት በመጀመሪያ ጫማ ማውለቅ ያስፈልጋል። መስጊዱ ንጹህ (ጡሀራ) በመሆኑ በጫማ አይረገጥም። ወ/ሮ የሺ እማወራዎች ተሰብስበው ቡና እየጠጡ ወደሚቀመጡበት ጎጆ ወሰዱኝ። ከዚያም ሁሉንም ሰላም እንድል (እንድዘይር) አደረጉ። በመቀጠልም የመጣሁበትን አላማ ለወ/ሮ የሺ ፋጢማ ሳስረዳ ሁለት ጥያቄዎችን ደጋግመው ጠይቀውኛል። የመጀመሪያው የእኔ ጥናት ለእነሱ የሚሰጠው ጥቅም ምን እንደሆነ እንድነግራቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቁርአን መቅራት አለመቅራቴን ነው። በጎጆዋ ውስጥ የተሰባሰቡት ሴቶች የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። አንዳንዶቹ ቀኑ እርብ በመሆኑ ለሶላት፣ ሌሎቹ ደግሞ "ገዳሙ" ውስጥ ልጆቻቸው በመኖራቸው ሊጠይቋቸው እና ምግብ ሊያቀብሏቸው የመጡ ናቸው። የጁምአ ሰላት እስኪደርስ ቡና እየጠጡ እና ጫት እየቃሙ ዱአ በማድረግ የተለያዩ ሀይማኖታዊ ታሪኮችን በማውራት ያሳልፋሉ። ከተሰበሰቡት ሴቶች መካከል በእድሜ የገፉ ፋጡማ[10] የሚባሉ አንድ ሴት አሉ። እርፍደው የሚመጡ ሴቶች ስኳር፣ ቡና እና ጫት ይዘው በመምጣት ለፋጡማ በመስጠት ተንበርክከው ይመረቃሉ። እኔም የቻልኩትን ሰጥቼ ተመርቄአለሁ። የጁምአ ሰላት በመድረሱ ከጎጆዋ ወጣን። በዚህ ጊዜ በተለያዩ ጎጆዎች ውስጥ ከተመው ሀይማኖታዊ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ ሴቶችን አየሁ። በግምት ሰባት አመት የሚሆናቸው ህጻናትም ነበሩ። ከአስር ደቂቃ በላይ ያልወሰደው የጁምአ ሰላት ሲጠናቀቅ ሴቶቹ ወዲያው ወደ ትምህርታቸው (ቁርአታቸው) ተመለሱ። በመጀመሪያ "ሼሁን አስፈቅጂ" በማለት እነዚህን ጎጆዎች ተዘዋውሬ እንዳይ እና ሴቶቹን እንዳናግር አልፈቀዱልኝም። በመጨረሻም ቤት ያፈራውን በማለት እንጀራ በልቼ ሴቶቹን አመስግኜ ከአንድ ወር በኋላ እንደምመጣ ነግሬአቸው ተሰናብቼ ወጣሁ። በወንዶቹ በኩል ያለውን ሁኔታ ሊመለከትልኝ የሄደው አባቴ "ገዳማውያኑ" ለሰደቃ (ጀበል ጸዲቅ እንደሚባለው) ወጥተው ስለነበር ማንንም ሳያገኝ እንደተመለሰ ነገረኝ።

---

[9] የሺ ፋጢማ ቤታቸው "ገዳሙ" አጠገብ ነው። ባለቤታቸው ከስድስት አመት በፊት መሞቱን እና በህይወት እያለ የሼሆቹ ኣዳሚ በመሆን ያገለግል እንደነበር፣ ልጆቻቸውም በደረሳነት ከገባች ከአስር አመት በላይ መሆኗን እርሳቸውም በአዳሚነት ብዙ አመት ማገልገላቸውን፣ ባለቤታቸውን ከሞተ በኋላ ግን ብዙ ጊዜአቸውን "ገዳሙ" ውስጥ እንደሚያሳልፉ ይተርካሉ። ከአዳሚነት ባሻገር የውጭ ሰው (እንግዳ) ሲመጣ በዋናነት ሀላፊነት ወስደው የሚያስተናግዱት እርሳቸው ናቸው።

[10] ፋጢማ "በገዳሙ" ውስጥ የዱበርቲዎች አለቃ በመሆን የሚያገለግሉ፣ እድሜአቸው በግምት ሰባ የሚሆን፣ አረጀም ጊዜ በፊት ትዳራቸውን በመተው ወደ "ገዳሙ" የገቡ፣ በእድሜ ብዛት ጆሮአቸውን እና አይናቸውን ያዝ የሚያደርጋቸው ናቸው።

ለሁለተኛ ጉዞ ወደ ገዳሙ ከመሄዴ በፊት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶችን አድርጌአለሁ። በቅድሚያ ከትምህርት ክፍሉ ለዞኑ ባህል እና ቱሪዝም እና ለጫፋ ወረዳ የሚሰጥ የትብብር ደብዳቤ አጻፍኩ። ጥር 25/2004 ጠዋት 4:30 ሰአት ላይ ከሚሴ ከተማ ወደሚገኘው የባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት በመሄድ እና ከዩኒቨርሲቲው ያጻፍኩትን የድጋፍ ደብዳቤ በመስጠት ሁለት ነገሮችን በማድረግ እንዲተባበሩኝ ጠየኩ። የጠየኩትም ፡-

1 በመጀመሪያው ጉዞዬ ሴቶቹ ወንዶቹን እንዳስፈቅድ እና ፈቃደኝነታቸውንም ለሴቶቹ እንዲነግሯቸው ነግረውኝ ስለነበር ለጥናት ስሄድ "በገዳሙ" ውስጥ የሚገኙ ሰዎች መረጃ እንዲሰጡኝ እንዲነግሩልኝ፤
2 ወንዶቹ ጋር መግባት ስለማልችል ወንዶቹ ጋር ገብቶ ክብረ በአሉን (መውሊዱን) ሊቀርጽልኝ የሚችል ሰው እንዲመድቡልኝ ሲሆን ወደ ወንዶቹ መኖሪያ የሚገባ ሰው ለመመደብ እና ለመንገር ቃል ገቡልኝ።

ቅዳሜ ጥር 26/05/04 ማታ አዘጋጅቼ ያስቀመጥኳቸውን እቃዎችን መፈታተሽ ጀመርኩ። ዲጂታል ካሜራ፣ መቅረጸ ድምጽ፣ ባትሪ ድንጋይ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ እስክርቢቶ፣ ስኳር፣ ቡና፣ "ለገዳማውያኑ" የምሰጣቸው አልባሳት፣ ቅያሪ ልብስ እና ጋቢ ሁሉም ነገር በቦታው እንዳለ አረጋገጥኩ። ከረፋዱ አራት ሰአት አካባቢ ወደ ከሚሴ በሚወስደው ሚኒባስ ተሳፈርኩ። ከሚሴ ለመድረስ አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀረኝ በመውረድ ወደ ጡሩሲና "ገዳም" ከሚያደርሰኝ ባጃጅ ውስጥ ከስድስት ተሳፋሪ ጋር ሰባተኛ ሆኜ ተቀላቀልኩ። የባጃጁ ሾፌር ከዚህ በፊት ወስዶኝ የነበረ በመሆኑ ሰላምታ ተለዋወጥን ማውራት ጀመርን። ከጎኔ የተሳፈሩት አምስት ሰዎች ስለ ሼሁ እና ስለ መስጊዱ ሰምተው ከአዲስ አበባ እና ከጎንደር የመጡ ናቸው። ከባጃጅ ከወረድን በኋላም የሴቶቹ መግቢያ ብቻ ሆኖ ስለሚያስፈራ በወንዶቹ መግቢያ ተሸፋፍኜ እንድሄድ ነግረውኝ አንድ ላይ ጉዟችንን አደረግን። ወንዶቹ መግቢያ ላይ ሲደርሱ መንገዱን አሳይተውኝ ሄዱ። የሴቶቹ ከወንዶቹ መግቢያ የሚርቀው በ5 ደቂቃ በመሆኑ ብዙም አስቸጋሪ አልነበረም።

ሴቶቹ "ገዳም" እንደገባሁ እሜቴን[11] ሰላም ካልኩ በሁዋላ እንግዳ መቀበያው ጋር ተቀመጥኩ። የአሱር (10 ሰአት) ሶላት ሲደርስ በህብረት ሰግደን እንደጨረስን ደረሳዎቹን (ገዳማውያኑን)

[11]እሜቴ የዘር ሀረጋቸውንና የትውልድ መንደራቸውን ለመናገር ባይፈቅዱም (ብዙ አያወሩም) በህጻንነታቸው በቤተሰብ አስገዳጅነት የወጣትነት ትዳር ጥለው "ገዳሙ" ውስጥ መኖር መጀመራቸው ይነገራል። ትክክለኛ እድሜአቸውን ባያውቁትም እርግጠኛ እንጋግሽ እንደሆኑ መገመት ችያለሁ።

ለማናገር ስሞክር በፍጥነት እንዲሄዱ ተናገሯቸው። ስጠይቃቸውም ከወንዶቹ ምንም አይነት መልእክት እንዳልደረሳቸው እና እንድሰራ እንደማይፈቅዱልኝ፣ ፎቶም እንዳላነሳ አስጠነቀቁኝ።

እሁድ ጥር 27/05/04 ጧት አንድ ሰአት አካባቢ ኔት ዎርክፍለጋ የ30 ደቂቃ መንገድ ሄድኩኝ። ከሚሴ ባህልና ቱሪዝም ለሚሰሩ ሰዎች ደውዬ ሴቶቹ እንዳልፈቀዱልኝ እና እንዲነግሩልኝ ብለምንም አልነገሩልኝም። በዚህ ጊዜ ማድረግ የምችለው በአሉን ለመታደም እንደመጡ ሰዎች የበአሉ ተሳታፊ በመሆን ለሶስት ተከታታይ ቀናት ክብረ በአሉን መታደም እና መመልከት ነበር።

ማክሠኞ ጥር 29/05/04 ከገዳሙ ወጥቼ ወደ ከሚሴ በሚወስደው ሚኒባስ ላይ ተሳፍሬ ወደ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች ሄድኩኝ። ለወንዶቹ ስላልነገሩልኝ የምፈልገውን መረጃ እንዳላገኘሁ ስናገር "ገዳም" ውስጥ ካዳሚ የሆነ አንድ ሰው ከሚሴ ድረስ ነገ እንደሚያስጠሩልኝ ቃል በመግባት ለነገ ቀጠሮ ያዙን።

እሮብ ጥር 30/05/04 በቀጠሮዬ መሰረት ወደ ከሚሴ ብሄድም የዞኑ ባህል እና ቱሪዝም መምሪያ ሰራተኞች ለማገናኘት ቃል የገቡልኝን ሰው ሊያገኙኝ አልቻሉም። በተደጋጋሚ መንገላታቴን የተመለከተው አቶ አህመድ መሀመድ[12] አባቱ አቶ መሀመድ አማን[13] የአካባቢው ሰው መሆናቸውን ነግሮኝ ወንዶቹ ጋር አባቱን ይዞ በመግባት የምፈልገውን መረጃ እንደሚጠይቅልኝ ነገረኝ።

የካቲት 01/06/04 ጧት ለስት ሰአት ላይ አቶ አህመድ እና አቶ መሀመድ ጋር ተገናኝተን ወደ ገዳሙ ገባን። ከስምንት ቀናት ደጅ ጥናት በኋላ የምፈልገውን መረጃ ከሞላ ጎደል ማግኘት ቻልኩ። የመጨረሻ ጉዞዬ የተደረገው ማክሰኞ 13/09/04 ሲሆን የተገኙት መረጃዎች ትክክለኛነት ያረጋገጥኩበት እና የተረሱ ጉዳዮችን የፈተሽኩበት ነው። በክፍለ ትምህርታችን የማስተርስ ተማሪ የሆነው ወንድወሰን አንዱአለምን ትብብር በመጠየቅ ወደ ወንዶቹ ገዳም እንዲገባልኝ አድርጌአለሁ። በወንዶቹ "ገዳም" የወንድወሰን ድርሻ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ትክክለኛነት በቡድን ውይይት ማረጋገጥ ነበር።

[12] አቶ አህመድ መሀመድ እድሜው 27፣ በታሪክ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ያለው፣ የከሚሴ ከተማ ነዋሪ እና የወረዳው ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ ነው።
[13] ቁጥር 8 ላይ የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

በተደጋጋሚ በተከናወነው የመስክ ጉዞዬ በርካታ ፈታኝ ነገሮች አጋጥመውኛል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያጋጠሙኝ ችግሮች እና ችግሮቹ የተፈቱባቸው መንገዶች ቀርበዋል፡፡

"ገዳማዊ ህይወት በእስልምና ሀይማኖት የለም" በማለት የሚቃወሙ ሰዎች ከከተማ እየመጡ ስለሚረብሿቸው በመጀመሪያው ጉዞዬ እነሱን መስያቸው መረጃ ሊሰጡኝ አልፈቀዱም ነበር፡፡ የተፈጠረባቸውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ከዞኑ የባህል እና ቱሪዝም ስራተኞች ጋር በመገናኘት ስለ ማንነቴ እንዲነግሯቸው በማድረግ ማሳመን ችያለሁ፡፡

"ገዳማውያኑ" አለማዊውን ህይወት "ንቀው" የሚኖሩ በመሆናቸው ስለአኗኗራቸው፣ ስለእምነታቸው፣ ስለራሳቸው ግልጽ የሆኑ ነገሮችን ለውጭ ሰው ለመናገር አይፈልጉም፡፡ ወደ "ገዳሙ" ስሄድ እነሱ የሚለብሷቸውን ልብሶች በመልበስ፣ የሚበሉትን በመብላት እና በሚሰሯቸው ስራዎች ላይ በመሳተፍ፣ ቁርአን በመቅራት፣ አብሬአቸው በመስገድ እና ውሀ በመቅዳት ቅርበት በመፍጠር የምፈልገውን መረጃ እንዲነግሩኝ አግባብቻለሁ፡፡ ብዙዎቹ "ገዳማውያን" የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመሆናቸው ከምፈልጋቸው ሰዎች ጋር በቀጥታ ለመግባባት ተቸግሬ ነበር፡፡ ኦሮምኛ እና አማርኛ መናገር የሚችሉ ሰዎችን በመምረጥ የቋንቋውን ችግር በከፊል መቀነስ ችያለሁ፡፡

ከአንድ ሰው ያገኘሁትን መረጃ ለማረጋገጥ ሌሎች ለመጠየቅ ስፈልግ "እኔ ነግሬሻለሁ ሌላ ምን ያደርግልሻል" በማለት እንዳይናገሩ ይከለክሉ ነበር፡፡ ይህንንም የጠየኳት ሴት አለመኖሯን በማረጋገጥ እንዲሁም ከሁለት እና ከሶስት ቀን በኋላ ሌላ ሰው በመጠየቅ የመረጃዎቹን ትክክለኛነት አረጋግጫለሁ፡፡ ሴት "ገዳማውያን" ከቅርብ ቤተሰባቸው ውጭ በእነሱ አነጋገር "ከከተማ ሰው ጋር" ተገናኝተው ባለማወቃቸው ሳናግራቸው ስፈልግ ማፈር እና መሸሽ ቢኖርም እንደ "ገዳማውያኖኑ" ቁርአን የቀራሁ መሆኔን በመንገር አንዳንዶም በመቅራት ወደ እኔ ማምጣት እና ማውራት እንዲደፍሩ ማድረግ ችያለሁ፡፡ (መቼ ትመጫለሽ በማለት ስራውን ከጨረስኩ በኋላም እንዳልቀር ቃል አስገብተውኛል)

ለቃለ መጠይቅ ስጠይቃቸው ድምጻቸው "ከገዳሙ" ከወጣ ወንዶች ይሰሙታል በማለት ለመቀረጽ ባለመፍቀዳቸው በእምቢታቸው የጸኑ "ገዳማውያን" በማስታወሻ ደብተሬ ሀሳባቸውን አስፍሬአለሁ፡፡ ፎቶ ለማንሳት ስፈልግ "እሳህ አንዴ ፎቶ አንስቶናል ስለዚህ አንነሳም" ያሉኝ ሲሆን ፎቶ ለመነሳት እሺፈረኝ ያሉትን "ገዳማውያን" የሌሎችን ፎቶ አሳጥቤ በመሥጠት እና

በማሳየት እነሱም ከተነሱልኝ ፎቶአቸውን አሳጥቤ እንደምልክላቸው በመግለጽ ለማግባባት ጥረት አድርጌአለሁ።

በአንድ ወቅት ከመገናኛ ብዙሀን የመጡ ሰዎች ምስላቸውን በቪዲዮ ቀርጸው ሄደው ከአለማዊ ዘፈን ጋር አቀናብረው ለህዝብ ማቅረባቸውን በመግለጽ ቪዲዮ ለመቀረጽ ፈቃደኛ አልሆኑም። እኔም "የገዳሙን" ማህበረሰብ በሚያስከፋ ሁኔታ የመገናኛ ብዙሀኖቹ ገዳሙን ከዘፈን ጋር አቀናብረው ማቅረባቸው ትክክል እንዳልሆነ በመግለጽ የእኔ ግን ከመገናኛ ብዙሀኖቹ በተለየ አላማ እና አቀራረብ እንደሚውል በማሳመን ለመቅረጽ ጥረት ባደርግም ብዙም አልተሳካልኝም።

ወንዶቹ ጋር ሴት ለመግባት ስለማትችል የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ብቸገርም በኋላ ላይ አቶ አህመድ እንዲገባልኝ እና የምፈልገውን መረጃ እንዲሰጠኝ አድርጌአለሁ። በመቀጠልም የጥናቱ ትኩረት "በገዳሙ" ውስጥ ያሉ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ማየት በመሆኑ በክፍለ ትምህርታችን የማስተርስ ድግሪ ተማሪ የሆነውን ወንድወሰን እንዱአለምን በማስቸገር "በገዳሙ" ተገኝቶ ለምፈልጋቸውን ጥያቄዎች ምላሽ አስገኝቶልኛል።

# ምእራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርእስ አስራ አንድ ያህል ተዛማጅ ጽሁፎች ተቃኝተዋል። በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ዲግሪ፣ በታሪክ ትምህርት ክፍል ሶስት፣ በቅድስት ስላሴ የስነ መለኮት ኮሌጅ ሶስት እና በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር የተሰሩ ሶስት ጥናቶችን አካቷል። በተጨማሪም በአገራችን እና በውጭ ዜጎች የተሰሩ ሁለት የፒኤችዲ ጥናቶችንም ይዟል።

በታሪክ ትምህርት ክፍል የተሰሩ፡ ሀብታሙ መንግስቴ በ1988 ዓ.ም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል።[14] የጥናቱ አላማ ከ1500-1974 ያለውን የመርጦ ለማሪያም ገዳም ታሪክን መቃኘት እንደሆነ ገልጿል። በዚህ መሰረትም ገዳሙ ከመመስረቱ በፊት በአካባቢው የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታ፣ ገዳሙ የተመሰረተበትን ምክንያትና ዘመን፣ የምስረታውን ሁኔታ እና በግራኝ አህመድ ወረራ ወቅት በገዳሙ የደረሰውን ጉዳት በዝርዝር አስረድቷል።

ለጥናቱ የተሰጠው ጊዜ አጭር በመሆኑ የእነዚህን ሁሉ ዘመናት ታሪክ በትክክል "አጥንቻለሁ" ማለት የመረጃውን ተአማኒነት ከገምት ውስጥ የሚጥል ነው። ጥናቱ የገዳሙን አመሰራረት ማንሳቱ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው የገዳሙን ታሪክ ጽፎ ከማስቀረት አንጻር እንጂ ፎክሎራዊ የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ለማጥናት የተሰራ አለመሆኑ ይለየዋል።

በሙቀጠል ጥጋቡ በዜ (በ2001 ዓ.ም) ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጽሁፍ ተቃኝቷል። የጥናቱ ዋና አላማ ከ1850-1994 ድረስ በገዳሙ ላይ የተከሰቱ ልዩ ልዩ ችግሮችን በዝርዝር ማሳየት ነው። በስሩ የገዳሙን አመሰራረት እና ከገዳሙ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የንግስተ ሳባን እና የንጉስ ሰለሞንን ግንኙነት ታሪክን መሰረት በማድረግ አቅርቧል።

ጥናቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት የእስራኤል እና የኢትዮጵያን ግንኙነት፣ የንግስተ ሳባ እና የሰለሞንን ግንኙነት፣ በኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም የሚደረገው መንፈሳዊ ጉዞ፣ የጉዞው ፈታኝነት በመረዳት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት በቋሚነት እንዴት መኖር እንደጀመሩ፣ የዴር ሱልጣን ገዳም አመሰራረት እና በኋላ ላይ በግብጾች የመነጠቃቸው ምስጢር ዘርዝሯል። ይህን

[14] A History of Monastery of Mertulamariame (c1500-1974) በሚል ርእስ

ተከትሎ የግብጽ እና የኢትዮጵያ መልካም ግንኙነት መቋረጥ፣ አጼ ዮሀንስ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ችግር ለመቅረፍ ያደረጉትን ሙከራ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በማንሳት ስፊ ትንተና ሰጥቶበታል። ጥናቱ በመግቢያ ውስጥ መካተት ያለባቸው የጥናቱ፤ ዳራ፣ አስፈላጊነት፣ ወሰን... ያካተተ ሲሆን ተዛማጅ ጽሁፎችንም አልዳሰሰም።

በቅድስት ስላሴ የስነ መለኮት ኮሌጅ የተሰሩ፡- መንግስቱ ከበደ (በ1999 ዓ.ም)[15] የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱን ሰርቷል። ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው የደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሰራረት እና ገዳሙ በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ያለውን ሚና ማሳየት ነው። መንግስቱ ስለ ደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሰራረት፣ ገዳሙ ከመንፈሳዊ ግልጋሎቱ ባሻገር ከቅርስ ጥበቃ እና ከልማት አኳያ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እና በግራኝ አህመድ ወረራ ወቅት በገዳሙ ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ተንትኗል። የገዳሙን አመሰራረት ማንሳቱ እና ገዳሙ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን አስተዋጽኦ መግለጹ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

ዘላለም አሰፋ (በ2001 ዓ.ም)[16] ለመጀመሪያ ዲግሪ ያቀረበው ወረቀት ተዳሷል። የጥናቱ አላማ የደብረ ጽዮን ገዳም አመሰራረት እና በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ ነገሮች ለባህል እና ቱሪዝም ያላቸውን ፋይዳ አጉልቶ ማሳየት ነው። በጥናቱ በኢትዮጵያ የገዳም ህይወት አጀማመር ምን ይመስል እንደነበር፣ ገዳሙ የሚገኝበት አከባቢ መልከአምድራዊ እና አጠቃላይ ገጽታ ምን አይነት መልክ እንዳለው እና ገዳሙ በውስጡ የያዛቸው ታሪካዊ ቅርሶች ምን እንደሆኑ አሳይቷል።

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያትና መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴው አልተጠቀሰም። የገዳሙ አመሰራረት እና ዳራ ላይ ማትኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ቢያገናኘውም ገዳማውያኑን እና በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ ከበራዎችን አለመመልከቱ ይለየዋል።

ተግባሩ አዳነ (በ2002 ዓ.ም)[17] ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። በጥናቱም የገዳሙን አመሰራረት፣ ገዳሙ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የፈጸመውን ተግባር፣ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የገዳማውያኑን የገቢ ምንጭ እና ገዳሙ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ በዝርዝር አቅርቧል።

---

[15] The Role of Debre Libanos Monastery in the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church በሚል ርእስ
[16] A Brief History and Activities of Zeway Debre Tsion Monastry በሚል ርእስ
[17] A Brief History of Dima Giorgis Monastry በሚል ርእስ

የጥናቱ አላማ የገዳሙ ቅርሶች በአግባቡ እየተጠበቁ ባለመሆናቸው የሚጠበቁበትን መንገድ ማመላከት፣ በገዳሙ እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ሁለት ገዳማውያን ታሪክ በመጻፍ ለበጎ ስራቸው እውቅና መስጠት፣ ገዳሙ በኢኮኖሚ የሚያድግበትን መንገድ ማመላከት እና በችግር ወደ ከተማ የሚፈልሱ ገዳማውያን ችግራቸውን ለመፍታት የሚያስችሉ የመፍትሄ ሀሳቦችን ማመላከት ናቸው። ጥናቱ የገዳሙን፣ አመሰራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የገዳማውያኑ የገቢ ምንጭ እና ገዳሙ ከመንፈሳዊ ህይወት አኳያ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ማየቱ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ጥናት ከእነዚህ ጉዳዮች ባለፈ ፎክሎራዊ ገጽታዎች ላይ ያተኩራል።

በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩ፡- በዚህ ስር የቀረቡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የጥናት ስራዎች ከሌሎቹ በተለየ ሰፋ ያለ ትንታኔ እና ሂስ ተሰጥቶባቸዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ትምህርት ክፍሉ መረጃን ከመሰነድ አልፎ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለማየት እድል ስለሚከፍት ነው። ጥናቶቹ ቅኝቱ እስከተደረገበት ጊዜ ገዳምን አስመልክቶ በብቸኝነት በትምህርት ክፍላችን የቀረቡ ናቸው።

ታደሰ አይችሉህም በ1999 ዓ.ም[18] የጥናት ወረቀት አቅርቧል። የጥናቱ አላማ በአንድነት ገዳም ውስጥ የሚኖሩ መነኩሳትን የየእለት ህይወት መመልከት፣ የመገልገያ እቃዎች፣ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጎቸውን ጌጣጌጦች፣ ልብሶች፣ ምግቦች፣ እረፍት፣ ግንዘት እና ጸሎተ ፍትሀት እና የገዳማቱን የአስተዳደርና የስራ መዋቅር ከትእምርቱ አንጻር በማገናዘብ መመርመር መሆኑን ገልጿል።

ጥናቱ በአምስት ምእራፎች ተከፋፍሎ ቀርቧል። በመጀመሪያው ምእራፍ የጥናቱ አላማ፣ ወሰን፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዘዴ፣ ያጋጠሙ ችግሮች...ዘርዝሯል። በሁለተኛው ምእራፍ በኢትዮጵያ የክርስትና ሀይማኖት ታሪካዊ አጀማመር፣ የገዳም እና የምንኩስና ህይወት አለም አቀፋዊ እና ኢትዮጵያዊ መነሻዎችን ጽፏል። በሶስተኛው ምእራፍ ተዛማጅ ጽሁፎችን ዳስሷል። በምእራፍ አራት እና አምስት የገዳማቱ የአስተዳደርና የስራ መዋቅር፣ የአበምኔት አመራረጥ እና የሥራ ሀላፊነት፣ የምንኩስና አቀባበል ስርአት፣ የግጭት አፈታት ዘዴ፣ የመነኮሳቱን

[18] "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የምንኩስና ስርአት እና የገዳማውያን የእለት ተእለት ህይወት ከትእምርታዊነቱ አንጻር በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተ/ሀይማኖት ገዳማት" በሚል ርእስ

የአመጋገብ ስርአትና ጊዜ፣ የስራ ክፍፍል እና አይነት አለባበስ የመነኮሳት ግንዘት እና ጸሎተ ፍትሀት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትንተና ሰጥቷል፡፡

ለጥናቱ ያነሳሳው ጉዳይ በርእስ ጉዳዩ ዙሪያ ብዙ ጥናት አለመደረጉ ነው፡፡ መረጃ የሰበሰበበት ዘዴ የመስክ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ መረጃውን ለመተንተን ገላጭ የምርምር ዘዴን እና ትእምርታዊ መስተጋብራዊ ቲዎሪን ተጠቅሟል፡፡

ታደሰ በትምህርት ክፍሉ ትኩረት ያልተደረገበትን ርእስ መምረጥ መቻሉ የጥንካሬው መጀመሪያ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ መመለስ መቻሉ፣ የገዳማውያኑን ህይወት ለማሳዬት የተጠቀመበት ዘዴ ግልጽ እና ገላጭ መሆኑ እና በተወሰነ መልኩም ቢሆን ትእምርቶችን ለይቶ ለመተርጎም መሞከሩ ሌላው የጥናቱ ጥንካሬ ነው፡፡

በመግቢያው ላይ የጥናቱ ወሰን ወንዶች እና የተወሰኑ ሴቶች ናቸው ቢልም በጥናቱ ላይ አንድም ቦታ ስለሴቶች አላነሳም፡፡ ለጥናት የመረጣቸውን ሁለት ቤተክርስትያናት አመሰራረት፣ ዳራ፣ የምርምር ጥያቄዎችን እና የጥናቱን አስፈላጊነት አላካተተም፡፡ ጥናቱ የሚቀነበብበት ምንም አይነት ንድፈ ሀሳብ የለውም፡፡ መረጃውን የሰበሰበበት ዘዴ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው ብሎ ከማለፍ ውጭ እንዴት እንደተጠቀመባቸው አልገለጸም፡፡ የመረጃውን ትክክለኛነት ለመመዘን የሚያስችለውን የቡድን ውይይት አልተጠቀመም፡፡ በሌሎች የትምህርት ክፍሎች የተሰሩ የማስተርስ እና የፒኤችዲ የጥናት ስራዎች ቢኖሩም የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝቱ ሙሉ ለሙሉ በመጀመሪያ ዲግሪ ጽሁፎች (በመጀመሪያ ዲግሪ የሚሰሩ በርካታ ጥናቶች (ሁሉንም ማለት አይደለም) መረጃን ሰብስቦ ከማስቀመጥ የዘለለ በንድፈ ሀሳብ የታገዘ ትንተና እና ትርጉም ሲሰጡ አናስተውልም) ላይ ብቻ መወሰኑ የጥናቱ ደካማ ጎኖች ናቸው፡፡

የታደሰ ጥናት የገዳማቱን የአስተዳደርና የስራ መዋቅር፣ የአበምኔት አመራረጥና የሥራ ሀላፊነት፣ የምንኩስና አቀባበል ስርአት፣ የግጭት አፈታት ዘዴ፣ የመነኮሳቱን የአመጋገብ ስርአትና ጊዜ፣ የስራ ክፍፍልና አይነት እና አለባበስ ማንሳቱ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው በገዳማቱ የሚከበሩ ክብረ በአላትን አለመመልከቱ ደግሞ የሁለቱ ጥናቶች ልዩነት ነው፡፡

ወርቁ [illegible] በ1999[13] ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ አላማ የገዳሙን አመሰራረት፣ በገዳሙ የሚከናወነው ጸበል የማጥመቅ ስርአት እና የመነኮሳቱን ድርጊቶች ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳዬት

[13] "የሴሙና ሲልቢሎ ወረዳ የጨፋ መድሀኒዓለም ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማሪያም እና ቅድስት ሰላም የሴቶች አንድነት ገዳም አመሰራረት ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርእስ

እንደሆነ አስፍሯል። ጥናቱ በአምስት ምእራፎች የተከፋፈለ ነው። በምእራፍ አንድ የጥናቱ አላማ፣ በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዘዴ እና የመረጃ አሰባሰብን ሲያመላክት በምእራፍ ሁለት ገዳማቱ የሚገኙበት አካባቢያዊ ዳራን በሰፊው ገልጿል። በምእራፍ ሶስት ከርእሱ ጋር ተዛማጅ ናቸው ያላቸውን በታሪክ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ሶስት የመጀመሪያ ዲግሪ እና አንድ የማስተርስ ጥናቶችን እና የገዳምን ምንነት አስመልክቶ የተሰሩ ቀደምት ስራዎችን ቃኝቷል። በምእራፍ አራት የገዳሙን አመሰራረት፣ የጸበልን ምንነት እና ስርአተ ክዋኔውን በማሳየት ወደ መጨረሻው ምእራፍ ተሸጋግሯል። በምእራፍ አምስት የገዳሙን መመስረት ተከትሎ የሚነገሩ ስነ ቃሎች እና ትረካዎች ፎክሎራዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል አሳይቷል።

መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅን፣ ምልከታን እና መረጃውን ለመተንተን ገላጭ የምርምር ስልትን ተጠቅሟል። በአንድ የጥናት ወረቀት ይመለሳሉ ተብለው የተቀመጡ ጥያቄዎች መመለስ መቻል አለባቸው። በዚህ ረገድ የወርቁ ጥናት ጥሩ የሚባል ነው። የገዳም ምንነት ላይ ያሠፈራቸው ጭምቅ ሀሳቦች በቂ መረጃ ይሰጣሉ።

ወርቁ የፎክሎር አጥኚ እንደመሆኑ በጥናቱ ለትርጉም የተመቹ በርካታ ትእምርቶችን አንድም ቦታ አልተረጎመም። የጥናቱ ትኩረት በገዳሙ ውስጥ የሚካሄደውን ጸበል የማጥመቅ ስርአት ማሳየት ነው ቢልም ከስርአቱ ይልቅ በገዳሙ የሚነገሩ ትረካዎች ላይ ትኩረት አድርጓል። ከጥናቱ ጋር የተገናኘ የንድፈ ሀሳብ ዳራ አላካተተም። በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በንኡስ ርእስነት ያስፈራቸው ነጥቦች ከርእሱ ጋር በቀጥታ የማይገናኙ ናቸው። ለአብነት የእማሆይ ሳህለ ማሪያም ራእይ በሚል ርእስ የቀረበውን ሀሳብ እንመለከታለን (1999፣39)። ከሌሎች ባለራእዮች በተለዩ ስም ተሰጥቶት በርእስነት የቀረበውን የእማሆይ ራእይ ሳይገልጽ በመጽሀፍ ቅዱስ በሰፈሩ የራእይ ታሪኮችና በራእይ ምንነት ላይ ብቻ ተወስኖ ያልፋል። በገዳማውያኑ የሚስተዋሉ ፎክሎራዊ ገጽታዎች በሚለው ንኡስ ርእስ በአብዛኛው የሚገልጸው ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ሳይሆን በገዳሙ እና በገዳማውያኑ ላይ የሚስተዋሉ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ ትኩረት አድርጓል።

የወርቁ ጥናት የገዳሙን አመሰራረት እና አካባቢያዊ ዳራ መግለጹ እና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በገዳማውያኑ የሚከናወኑ ስርአቶችን ፎክሎራዊ ገጽታ ለማየት መሞከሩ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በተቃራኒው የዚህ ጥናት የሙስሊም "ገዳም" እንዴት ሊኖር እንደቻለ እና 'በገዳሙ' የሚከበሩ ክብረ በአላት በሰፊው የሚዳስስ በመሆኑ ይለያል።

በሞገስ ጆንበር 2003 ዓ.ም[20] የቀረበው ጽሁፍ በጥናት ወረቀቶች ላይ የተደረገው ዳሰሳዬ ማሳረጊያ ነው። የጥናቱ አላማ በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮች እና በገዳሙ ውስጥ በሚፈጸሙ አምልኳዊ ስርአቶች የገዳማውያኑን እምነት ምን እንደሚመስል መመርመር እና እምነቱ ለገዳማውያኑ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው።

አላማውን ከግብ ለማድረስ ጥናቱን በስድስት ምእራፎች ከፋፍሎ አቅርቧል። በምእራፍ አንድ የጥናቱ፣ ዳራ፣ አላማ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ተዘርዝረዋል። በምእራፍ ሁለት ከርእሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መጻህፍት ላይ ንባብ በማካሄድ የህገረሰባዊ ልማድ፣ እምነቶች፣ ስርአቶች፣ ተረኮች ምንነት እና ጥናቱ የሚተነተንበትን ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አካቷል። በምእራፍ ሶስት የገዳም ህይወት አጀማመርን (በአለም አቀፍ፣ በኢትዮጵያ እና በዳጋ እስጢፋኖስ) አመላክቷል። በምእራፍ አራት እና አምስት በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርአቶች ላይ ትንተና አድርጎባቸዋል። የጥናቱ ማጠቃለያ በምእራፍ ስድስት ላይ አስፍሯል።

በክለሳ ድርሳኑ ስር የተለያዩ መጻህፍትን በማጣቀስ ያቀረባቸው ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶቹ በንባብ ላይ የተመሰረቱ ጭምቅ ሀሳቦች መሆናቸውን ያሳያሉ። በጥናቱ ይመለሳሉ ያላቸውን አላማዎች አንድም ሳያስቀር ማሳየት መቻሉ ጥንካሬው ነው። የጥናቱ ትኩረት በገዳሙ የሚከበሩ ትረካዎች እና ፋይዳቸው ላይ በመሆኑ ለጥናቱ የመረጠው ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አላማውን ለማሳካት አግዞታል።

ተጣጣኝ የሆኑ ጥናቶችን ሲዳስስ የአጥኚዎቹን ድክመት እና ጥንካሬ አላካተተም። ከትረካዎቹ በተጨማሪ ለጥናቱ የመረጣቸው አምልኳዊ ስርአቶች በስፋት በማተቱ (በጸሎተ ማድ የሚከናወኑ፣ በተግባር ቤት የሚከናወኑ፣ በምርጫ ስዩማን የሚከናወኑ፣ በአበምኔት ምርጫ የሚከናወኑ...) በእያንዳንዱ ስርአት ላይ ሰፊ ጥንታኔ እና ትርጎማ እንዳይሠጥ አድርጎታል። በትንተናው ወቅት "ምናልባት፣ይመስለኛል..." የሚሉ (ለምሳሌ "ምናልባትም ከተለመዱት የእንስሳት ዝርያዎች ይህች እንስሳ የተመረጠችበት ምክንያት ጭንቱን ፍጹም ቅድስና ለማላበስ ይመስለኛል (2003፣65)) የሚሉ ቃላትን በመጠቀም መረጃውን ለመተንተን እና ትእምርቶችን ለመፈከር መሞከሩ እንደ ድክመት ይጠቀሳሉ።

---

[20] "ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርአቶች" የሚል ርእስ

የሞገስ ጥናት የገዳሙን አመሰራረት እና የስርአቶችን ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየቱ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥቦች ተረኮች እና "በገዳማውያኑ" የሚከበሩ የእለት ተእለት ስርአቶች ሳይሆኑ "በገዳማውያኑ" እና በአካባቢው ማህበረሰብ የሚከበሩ ክብረ በአላት ላይ መሆኑ ለየት ያደርገዋል።

ለፒኤችዲ ማሟያ ከተሰሩ ጥናቶች መካከል ለዚህ ጥናት በቀዳሚነት የሚጠቀሰው በካፕላን[21] 1982 ዓ.ም የቀረበው ሰፊ ጥናት ነው። የጥናቱ አላማ ከ1270-1468 ዓ.ም መካከል የኖሩ ገዳማዊ ቅዱሳንን እንሳስ እና ተግባር ማሳየት ቢሆንም ከእነዚህ ጉዳዮች በዘለለ በርካታ ጉዳዮችን አንስቷል።

ጥናቱ በአምስት ንኡሳን ዘርፎች የተከፋፈለ ነው። የክርስትና ሀይማኖት ታሪካዊ ዳራ ከኤዛና ጀምሮ እስከ አምደ ጽዮን፣ በኢትዮጵያ የገዳም ህይወት አጀማመር፣ በሰለሞናውያን ስርወ መንግስት ወደ ገዳም የገቡበትን ሁኔታ፣ ቅዱሳን ሰዎች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት፣ በህይወት እያሉ የፈጸሟቸውን እና ከሞቱ በኋላ የሚነገሩላቸውን ተአምራቶች አካቶ ይዟል። ካፕላን ኢትዮጵያ የገዳም እና የገዳማዊ ህይወት እንዲሁም የቅዱሳን ታሪክ ባለቤት ብትሆንም በዚህ ዙሪያ በቂ ጥናት እንዳልተደረገ ጽፏል።

በሁለተኛነት የሚጠቀሰው ስራ በሁሴን አህመድ በ2001 ዓ.ም[22] ለፒኤችዲ ማሟያ የቀረበው የጥናት ጽሁፍ ነው። የጥናቱ አላማ እስልምና እንደ ሀይማኖት የተስፋፋበትን እና የተሰራጨበትን መንገድ መግለጽ፣ የአገራችን ሙስሊሞች አኗኗር ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ ቀደምት ነጋዴዎች እና መሪዎች ለሀይማኖቱ መስፋፋት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ማመላከት፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ስለእስልምና ሀይማኖት መስፋፋት ያላቸውን እውቀት እና መረዳት ምን እንደሆነ ማጥናት እና የእስልምና ሀይማኖት ማህበረ-ባህላዊ ሚና ምን እንደሚመስል ማሳየት እንደሆነ ገልጸዋል።

ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ምእራፎቹ ለስድስት ተከፋፍለው ቀርበዋል። በመጀመሪያው ምእራፍ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የወሎን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ዳራ እንዲሁም በወሎ የኦሮሞ መስፋፋት እና መስፋፋቱ ያሳደረውን ተጽእኖ በስፋት ዳስሰዋል። በምእራፍ ሁለት የእስልምና ሀይማኖት ታሪክ በኢትዮጵያ በተለይ በወሎ ምን እንደሚመስል እና

[21] The Monastic Holy Man and the Christianization of early Solomonic Ethiopia በሚል ርእስ
[22] Islam in the Nineteenth Century Wallo, Ethiopia, Revival, Reform and Reaction በሚል ርእስ

የሀይማኖቱን አስተማሪዎች እና የጊዜው ነጋዴዎች ሚናን አሳይተዋል። በምእራፍ ሶስትም በደቡብ ወሎ የሱፊዝም ስርአት እና የእስልምና ሀይማኖት ተሀድሶን በመጥቀስ የሱፊ ቅዱስ ስፍራዎችን (ጀማ ንጉስ እና ገታ) ገጽታ አካተዋል። በምእራፍ አራት እስልምና እና የወሎ አገሬ ገዥዎች በተለይ የወረሂመናን ኢማም በመጥቀስ በሀይማኖቱ መስፋፋትና ማጠናከር ላይ የተወጣውን ድርሻ አብራርተዋል። በምእራፍ አምስት ከ1800-1890 ዓ.ም በደቡብ ወሎ የነበረውን የንግድ እንቅስቃሴ በምእራፍ ስድስት ደግሞ ከ1850-1890 ዓ.ም በጊዜው የነበሩ ነገስታት (ቴዎድሮስ እና ዮሀንስ) በወሎ ሙስሊሞች ላይ ያደረሱትን አስተዳደራዊ በደል አካተዋል።

ጥናቱ ትኩረቱን በእስልምና ላይ ማድረጉ እና በጥናቱ የተዳሰሱት መስጊዶች እንደ ጡሩሲና "ገዳም" ለነቢዩ መሀመድ ልደት ሰዎች ከተለያዩ ስፍራዎች ወደ ቦታው በመንዝ የሚያከብሩባቸው መሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ጥናት እንደ "ገዳም" ብቻ ትኩረት አድርጎ ክብረ በአሉ ላይ ማተኩሩ ይለየዋል። የሁሴን ጥናት በወሎ የነበረውን የሀይማኖቶች እርስ በራስ መቀራረብ በተለይ ደግሞ የኦሮሞዎች ልማዳዊ ስርአት በእስልምና እና በክርስትና ሀይማኖቶች ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ያሳየበት ክፍል ለዚህ ጥናት እንደ መረጃ ምንጭነት አገልግሏል።

በአጠቃላይ ከላይ የተቃኙት ጥናቶች (ከሁሴን ውጭ) ገዳም ላይ ማተኮራቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል። በታደሰ፣ በወርቁ፣ በሞገስ እና በካፕላን የጥናት ስራዎች የገዳም አመሰራረት፣ የገዳማውያኑ ህይወት፣ የሚነገሩ ተረኮችና ስርአቶች በዚህ ጥናት ተነስተዋል። ሁሉም የጥናት ስራዎች እንደተሰሩበት ትምህርት ክፍል አላማቸው የተለያየ ነው። በታሪክ ትምህርት ክፍል የተሰሩትን የሀብታሙን እና የጥጋቡን ስራዎች ስንመለከት አላማቸው የየገዳማቱን አመሰራረት ማስተዋወቅ እና በተሰሩበት ዘመን ያጋጠማቸውን ታሪካዊ ክስተት ማጉላት ነው። በተመሳሳይ መልኩ በቅድስት ስላሴ የስነ መለኮት ኮሌጅ የተሰሩ ስራዎች የገዳማቱን አመሰራረት ማሳየት እና ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ያበረከቱትን መንፈሳዊ ተግባር መግለጽ ላይ አተኩረዋል። በአንጻሩ በትምህርት ክፍላችን የቀረቡ የታደሰ፣ የወርቁ እና የሞገስ የጥናት ስራዎች አላማ የገዳማቱን አመሰራረት በመግለጽ በውስጣቸው የያዟቸውን ፎክሎራዊ ጉዳዮች፣ ተረኮች እና ስርአቶችን ማሳየት ነው። የአብዛኞቹ ጸሁፎች አላማ የየገዳማቱን አመሰራረት መተረክ፣ በግራኝ አህመድ ጦርነት ወቅት በሁሉም ገዳማት ላይ የደረሰውን አስከፊ ታሪካዊ ውድመት ማሳየት፣ የገዳማቱን አመሰራረት፣ የአስተዳደር ሁኔታ ከገኘው መደብ አንጻር ምን

ይመስል እንደነበር ሰንደ ማስቀመጥ እና ገዳማውያኑ ያለባቸውን መሰረታዊ ችግሮች መግለጽ ነው።

ከላይ እንደተገለጸው ከሁሴን አህመድ ውጭ የሁሉም ጥናቶች ትኩረት በኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት የተለመደው የገዳም ህይወት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በእስልምና ሀይማኖት ያልተለመደው "ገዳም" እና "ገዳማዊ ህይወት" ላይ መሆኑ የልዩነቱ መጀመሪያ ነው። በሌሎች የጥናት ስራዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች ወንዶች ሲሆኑ በዚህ ጥናት ወንድ እና ሴት 'ገዳማውያን' የጥናቱ ተተኳሪ ናቸው። በተጨማሪም የሌሎቹ ጥናት በገዳማውያኑ በየእለቱ የሚከበሩ ስርአቶች ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በአመት አንዴ የሚከበር ክብረ በአል ላይ በማተኮር በንድፈ ሀሳብ የታገዘ ፍካሬ ማድረጉ ይለየዋል።

በዚህ ዳሰሳ ስር የቀረቡት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪ ስራዎች ውስጥ የምርምር ጥያቄዎችንና የጥናቱን ጠቀሜታ አለማካተት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን አለመጥቀስ፣ ተዛማጅ ስራዎች ላይ በሚካሄድ ቅኝት ላይ ሂሳዊ ግምገማ አለመስጠት፣ ጥናቱ የሚቀነበበትን ንድፈ ሀሳብ አለማካተት እና በጥናቱ ውስጥ የሚገኙ ትእምርቶችን አለመተርጎም የተስተዋሉ ድክመቶች ናቸው።

በአጠቃላይ የተመረጡት ጥናቶች ላይ ቅኝት መደረጉ ስለ ገዳም ምንነት፣ አመሰራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚጠቅሙ ሀሳቦችን ለማግኘት አስችሏል። በተመሳሳይ መልኩ በሂሳዊ ቅኝት እና በጥልቅ ንባብ ተነቅሰው የወጡ የየጥናቶቹ ድክመቶች እና ክፍተቶች በዚህ ጥናት ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይኖር ትልቅ እገዛ አድርገዋል።

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

### 2.2.1. ክዋኔን ያማከለ ንድፈ ሀሳብ (performance-centerd-approach)

ይህ ንኡስ ርእስ ክብረ በአላትን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የሚያስችል የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ቀርቦበታል። የክዋኔ ቲወሪ የተመረጠበት ምክንያት "ክዋኔ ከሌለ ክብረ በአላት የሉም፤ ክብረ በአላት በራሳቸው ክዋኔ ናቸው" (ራፖፖርት፣1992፣250 እና ሲምስ፣2005፣138) በማለት ተመራማሪዎቹ ያስፈሯቸው ሀሳቦች ናቸው። ጥቅሱ ክብረ በአላት እንዲኖሩ የክዋኔ መኖር ግድ መሆኑን ያስረዳል። በዚህም ክብረ በአላትን ለማጥናት ክዋኔን መሰረት ያደረገ ጥናት ተመርጧል።

### 2.2.1.1. የክዋኔ ጽንሰ ሀሳብ ፡-

ክዋኔ ድርጊትንና ክስተትን አጣምሮ የሚገልጽ ተግባቦታዊ ጥበብ ነው። በሁነቱ የሚከወነው ጉዳይ ክብረበዓሉ፣ ከዋኙ፣ ተደራሲው፣ በጊዜና በቦታ ውስጥ የተግባቦቱ ቅርጽ መኖሩን ይናገራሉ። ቅርጹ የክዋኔውን ሂደት እንዲያውቅ የጋራ መግባቢያ ሆኖ ያገለግላል (ቦውማን እና ብሪግስ፣1990፣61)። በተመሳሳይ መልኩ ዲቦራ ኢኬፐቻን ክዋኔ ባህሪን ለመግለጽ የሚያገለግል ስነውበታዊ ተግባር ነው ትላለች። አቀራረቡ በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚታጀብ ነውም በማለት ታክላለች። ክዋኔው እውን እንዲሆን የከዋኙና የተደራሲው በአንድ ቦታና ጊዜ መገኘትን እንደሚጠይቅ፣ በሳቂነቱ እንዲቀጥል ድግግሞሽ ዋነኛ ገጽታው እንደሆነ ማስመሰል፣ መማር፣ ወደኋላ ተመልሶ ማስታወስ መለያዎቹ እንደሆኑም ትገልጻለች። ክዋኔ በባህልና በማህበረሰብ መካከል መካከለኛ በመሆን ማህበራዊ የሆነ ስሜትን ለመፍጠር ሲያገለግል፣ ከዋኙ ውስጣዊ ስሜቱን በመግለጽ ሌላኑቱን የሚያሳይበት አጋጣሚም ይፈጥራል (1995፣480)።

ሩት ፊኒጋን ክዋኔን ከሰው ልጅ አጠቃላይ ድርጊትና ባህል አንጻር እንደ ትዕይንታዊ፣ ከአንድ ውስን ተግባቦትና ድርጊት አንጻር ቅርጻዊ፣ መዋቅር ያለው አድርጋ ይዘታዊና ቅርጻዊ መልኩን ታስተምባለች። በማያያዝም ቃላዊ ተስተላልፎው በአንድ ጥበባዊ ስራ የታጠረ ሳይሆን ወደ ሌላ ፊጠራ የሚሸጋገር እንደሆነ እና ክዋኔው በውስን አጋጣሚ እዚያው በሚነሳ ሃሳብና በሚደረግ ተግባቦት በከዋኙ የሚመራ እንደሆነ አስፍራለች (1992፣86)።

በጥቅሉ ክዋኔን እነ ቦውማን (1992) የሚታይ ጥበባዊ ገለጻ፣ እነ ዳምቤን (1971) ተግባቦት፣ እነ ጎልድስቴን (1970) ትዕምርታዊ ድራማ ይሉታል። የተጠቀሱት አጥኚዎች ክዋኔ ውስጣዊና ውጫዊ መዋቅሮችን አካቶ የሚይዝ ጥበባዊ የሃሳብና የስሜት ማስተላለፊያ ስልት እንዲሁም የራስንም ሆነ የማህበርን ማንነት ለሌላ መግለጫ ተሳላፊ ጥበብ መሆኑን ይገልጻሉ።

### 2.2.1.2. ክዋኔን ያማከለ/አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ

ክዋኔን ያማከለ ንድፈ ሀሳብ የአሜሪካዊያን የፎክሎር እና የነገረ ሰብ ባለሙያዎች ያደረጉት እንቅስቃሴ ሲሆን የምዕራባውያንን ሜታፊዚካል አስተሳሰብ በመቃወም የተነሳ ነው። በዋነኛነት ትርጉምን አንድ ማዕከል በመፍጠር ከእርሱ አንጻር መፈከር እንዲሁም ምንጩን በግለሰብ ደረጃ

መወሰንን፣ ተጨባጭ በሚባል ቴክስት እና አውድ ላይ መመስረትን በመቃወም በቋንቋና በማህበራዊ ህይወት ላይ በማትኮር ማዕከልን ማፍረስ እና በሌላ አተያይ ትርጉምን መፈከር ላይ ትኩረት አድርጎ መነሳቱን (ቦውማን እና ብሪግስ ፣1990፣61) ይገልጻሉ።

ይህን ንድፈ ሀሳብ ለፎክሎር ባለሙያዎች በማስተዋወቅ ደረጃ መሰረት ጥሏል በመባል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ሪቻርድ ቦውማን ነው (ሲምስ፣2005፣128)። አቀራረቡ መሰረት ያደረጋቸው በርካታ እሳቤዎች ሲኖሩ ከእነዚህ መካከልም ፎክሎር ተግባራዊ የሚሆነው በተከሰተበት ጊዜ ባለው ክዋኔ ወይም ተግባቦት እንጅ በቴክስቱ ብቻ መሆን የለበትም፤ ሁሉም ተግባር/ሁነት መመዝገብ ይኖርበታል፤ ምዝገባው አድካሚ ቢሆንም ገላጭ የሆኑ መረጃዎችንም ማካል ያስፈልጋል የሚሉት ይጠቀሳሉ።

> The folklore concepts apply not to a text but to an event in time in which a tradition is performed or communicated. Hence the whole performance or communicative act must be recorded". However, recording "events" often amounted to little more than taking extra dirt from around the root wad. (ሁፎርድ፣1995፣528).

አቀራረቡ ቃላዊ ጥበብ ላይ ትርጉም ሲሰጥ ቢታይም በክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሶችና ከእነሱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲሁም ባህሪን፣ አመለካከትን እና ድርጊትን ጨምሮ ለመቃኘት ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪም መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ እና ቃላዊ ባህሪያቱንም ጥናቱ ይመለከታቸዋል። አጥኚውም የተፈጸመውን ተግባርና ተግባቦት መነሻ አድርጎ በሰላና በነቃ መንፈስ ምልከታውን የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም በመከታተል ይጀምራል። ለሁሉም እኩል እድል በመስጠት በዋነኛነት ግቡ የሆነውን ከዘወትራዊ ህይወት ውጭ የመጣውን ተጽዕኖ ለማግኘት በሚያስችለው መልኩ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። በዙሪያው ያሉ ቁሳቁሶች፣ ንግግሮች፣ ስዕሎች እና ምልክቶች ምን ግንኙነት አላቸው? በትርጉም ላይስ የሚያመጡት ለውጥ አለ? ብሎ ለማየት ያስችለዋል። ወደ ቴክስቱ/አውድ በማትኮርም ምዕራባውያን እንደ ተጨባጭና ያልተበረዙ አድርገው የሚወስዱትንና እነ ሪቻርድ ቦውማን ቴክስት የት ይጀምራል? አውዱስ መቼ ይገባል? ብለው ለሚያነሱት ጥያቄ ለሁለቱም እኩል ዕድል በመስጠት ራሳቸውን የሚገልጹበትን ሌላ ስያሜ በመስጠት ያጠኑበታል። ለቴክስት /encontextualization/፣ ለአውድ ደግሞ/contextualization/ የሚል አቻ መጠሪያ በመስጠት

ምዕራባውያን ለውጤት ትኩረት በመስጠት የሰሩበትን መንገድ በመቃወም እና በመተው ሂደቱ ላይ ትኩረት እንዲሰጥበት አድርገዋል፡፡

ባህሉን ለመተርጎምም ከዋኝ ተኮር የሆነውን አቀራረብ ብቻ ሳይሆን ተደራሲንም በማካተት ሁለቱም እንደ አንድ ትርጉም አስገኝ በመጠቀም በሂደቱ ላይ የነበረውን የሁለቱን ግንኙነት መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን ያነሳል፡፡ እነ ቦውማን ሂደቱ ተግባቦታዊ በመሆኑ አጥኚው ትርጉሙን የሚያወጣው ውጫዊውም ሆነ ማህበራዊ አውዱ በሚመራው ሳይሆን በስምምነቱ ላይ በመመስረት ይሆናል (1990፣62-70) ይላሉ፡፡

### 2.2.1.3 የፎክሎር ክዋኔ ባህርያት

በክዋኔ ላይ የተመሰረተ የአጠናን ዘዴ በዋናነት በክዋኔ ባህሪዎች እና ገጽታዎች ላይ ተመስርቶ ጥናት ያካሂዳል፡፡ በዚህ ጥናት የተመረጡት ክብረ በአላት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የክዋኔ ባህርያት ላይ በመመስረት ተቃኝተዋል፡፡ ሩት ፊኒጋን ሪቻርድ ቦውማንን ጠቅሳ እንደጻፈችው አንድ የፎክሎር ባለሙያ በአንድ ክዋኔ ላይ ትኩረት አድርጎ ምልከታ በሚያካሂድበት ጊዜ የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ገልጻለች፡፡ እነዚህም የሚከወንበት አጋጣሚ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ቴክስት፣ አውድ፣ ቅርጽ እና ሂስ ናቸው (ፊኒጋን፣1992፣91-92 እና ቦውማን፣1975፣290)፡፡ እነዚህ ጥቅል የክዋኔ ባህርያት ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

የሚከወንበት አጋጣሚ፡- አንድ የፎክሎር ዘርፍ ለመከወን ከዋኝ እና ታዳሚ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የመከወኛ ምክንያት ሊኖረው ይገባል፡፡ ሁሉም የፎክሎር አይነቶች ያለ ምንም ምክንያት አይከወኑም፡፡ የሰርግ ስርአት ለመከወን የሚጋቡ ሰዎች መኖር አለባቸው፡፡ የለቅሶ ስርአት ለመከወን የአንድ ሰው ህልፈት መኖር ግድ ነው፡፡ በተመሳሳይ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ክብረ በአላት የሚከወኑበት ምክንያት አላቸው፡፡ የመውሊድ በአል ለመከበር የነቢዩ መሀመድ የልደት ቀን መምጣት እና የሰርግ (ቁርአን ክትሚያ) በአልን ለማክበር የደረሳዎቹ ቁርአን ማኩተም ግድ ነው፡፡ የክዋኔውን አጠቃላይ ሁኔታ ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል ዋናው ክዋኔው የሚከወንበት ምክንያት ነው (ሲምስ፣2005፣139) በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከዋኝ ፡- ከዋኝ የመከወን ችሎታው እና እውቀቱን ተጠቅሞ አንድን የፎክሎር ቅርጽ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የሚያሸጋግር ድልድይ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታው በከዋኙ ላይ

ሲሆን ትኩረት የተሰጠባቸው ጉዳዮች የከዋኙ እድሜ፣ ጾታ፣ የትምህርት እና ማህበራዊ ደረጃ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ...ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ከዋኙ ብቻውን ነው የሚከውነው? ወይስ በጋራ? የሚለው ታሳቢ መደረግ እንዳለበት (ሩት ፊኔጋል፣1992፣88) ታስረዳለች። በተመሳሳይ መልኩ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ሲካሄድ የከዋኙ የአከዋወን ስልት፣ የመናገር ብቃት፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የፊት ገጽታ፣ የአካል እንቅስቃሴ፣ አለባበስ፣ ፍንገጣው...ትኩረት ተሰጥቶባቸዋል (ጎልድስቴን፣1964፣92)።

ታዳሚ፦ ታዳሚያን አንድ ክዋኔ ሲከወን የሚመለከቱ፣ የሚያደምጡ፣ የሚያስተውሉ፣ የከዋኙን ችሎታ የሚገመግሙ፣ ከዋኙን የሚያነቃቁ የከዋኙ ችሎታ ካልተዋጠላቸው እንደ አስፈላጊነቱ የከዋኙን ቦታ የሚተኩ በክዋኔው ሰፊ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው። የዚህ ጥናት ትኩረት ታዳሚው ጋር በሆነበት ጊዜ የተመለከታቸው ጉዳዮች ከዋኙን እንዴት ያበረታታሉ? ድጋፋቸውን እና ተቃውሟቸውን እንዴት ይገልጻሉ? (የከዋኙን ሚና በመንጠቅ/ክዋኔውን ትተው በመሄድ በራሳቸው ሌላ ክዋኔ በመፍጠር ወይስ ረብሻ እና ጸብ በማስነሳት) ወዘተ ናቸው (ጎልድስቴን፣1964፣92)። በወንዶቹ "ገዳም" የመውሊድ በአል ሲከበር በአሉን እንዲያደምቁ መንዙማ እንዲያንጎራጉሩ ከተፈቀደላቸው ሰዎች በቀር ድምጽ ማሰማት አይፈቀደም። አብዛኞቹ የፎክሎር ዘሮች እንደባህሪያቸው ይለያዩ እንጂ ታዳሚያን የግድ ያስፈልጉቸዋል።

ቴክስት፦ እነ ሲምስ ቴክስትን ከፎክሎር ጽንሰ ሃሳብ አንፃር ለመረዳት የቃሉን ስርወ ምንጭ ማወቅ ተገቢ እንደሆነ ይናገራሉ። "text የሚለው ቃል ምንጩ "texere" የሚለው የላቲን ቃል እንደሆነ ይገልጻሉ። ትርጉሙም "to weave" መሸመን ወይም ማድራት" ማለት ነው (2005፣19)። ሥርወ ቃሉ ቴክስት ከጽሁፋዊ እሳቤው ባሻገር ቁሳዊ ነገሮችን እንደሚያመላክት ይጠቁማል። ከዚህ አንፃር እነ ሲምስ "ቴክስት የሚለው ቃል ቃላትን፣ ቁሶችን፣ ሀሳብን እና ባህርይን የሚጠቁም ነው (2005፣19) በማለት ያስረዳሉ። በተጨማሪ ክዋኔ፣ ቃላዊ ትርክቶች እና ሀይማኖታዊ ክብረ በዓላትም ቴክስት መሆናቸውን ይገልጻሉ። በዚህ ጥናትም በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው ቴክስቶች "በገዳማውያኑ" የሚከበሩ ክብረ በአላት ሲሆኑ ጥናቱ እግረ መንገዱንም ቢሆን "ገዳማውያኑ" የሚጠቀሙባቸው ቁሶች፣ አልባሳት፣ ምግቦች፣ ታሪኮች፣ ድርጊቶችን ...አይቷል።

አውድ፡- አውድና ክዋኔ አንድ መሆናቸውን በመግለጽ ይህን ቃል ለማስተዋወቅም ሆነ አቋም ለመያዝ የመጀመሪያዋ ፎክሎረኛ የሆነችው ዞራ ኒያል ሀርስተን (1903—1960) እንደሆነችና በዜግነቷም አፍሪካ አሜሪካዊ መሆኗን ፊሊፕ እና ዊሲ (2004፣668) ጽፈዋል። እነ ሲምስ "the term context to mean everything that surrounds the text the setting, people, situation-anything in addition to the expressions, item, idea or objects being shared"(2005፣137). በማለት አውድን ይገልጹታል። ከጥቅሱ በመነሳት አውድ የምንለው አንድ ክዋኔ በሚከወንበት ወቅት ያለውን አጠቃላይ ድባብ፣ የክዋኔውን ስፍራ፣ የክዋኔውን ጊዜ፣ የመከወኛ ቁሳቁስ፣ የክዋኔውን ድባብ እና የከዋኙን እና የታዳሚውን መስተጋብር የሚይዝ ነው ማለት ይቻላል።

ባውማን እና ብሪግስ (1990፣68) አውድን ለስድስት ከፋፍለው አስቀምጠዋል። እነዚህም ትርጉማዊ አውድ (context of meaning)፣ ተቋማዊ አውድ (institutional context)፣ ተግባቦታዊ አውድ (context of communicative system)፣ ማህበራዊ መሰረት (social base)፣ ግለሰባዊ አውድ (individual context) እና የሁነት አውድ (context of situation) ናቸው። በማስከተልም ስድስቱን ነጥቦች በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ጨምቆ ማስቀመጥ እንደሚቻል ጽፈዋል።

እነዚህም ባህላዊ አውድ (cultural context) እና ማህበራዊ አውድ (social context) ናቸው። እንደ ባውማን ገለጻ ባህላዊ አውድ አንድ የፎክሎር ቅርጽ ምን ሀሳብ ይይዛል? በባህሉ ውስጥ የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? ከሌሎች የፎክሎር አይነቶች ጋር እንዴት ይዛመዳል? በሀይማኖታዊ እና መሰል ተቋማት የሚታየው የስልጣን ተዋረድ ምን ይመስላል? በማህበረሰቡ የሚስተዋለው የእርስ በርስ ግንኙነት እንዴት ይገለጻል? የሚለውን ሀሳብ ይይዛል። ማህበራዊ አውድ ደግሞ የባህሉ ባለቤቶች እነማን ናቸው? ሀይማኖታቸው ምንድን ነው? የስራ ድርሻቸው ምንድን ነው? የዘር፣ የቋንቋ፣ የጾታ ልዩነቱ በክዋኔው ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ምን ይመስላል? ባህሉ በግለሰቡ እና በማህበረሰቡ ላይ ያሳረፈው አሻራ ምንድን ነው? ማህበረሰቡ የሚገኝበት ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን ይጠቀልላል (ባውማን እና ብሪግስ፣1990፣68 እና ዳን ቤን አሞስ፣1971፣9)።

የበውግን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ሁለቱም የአውድ አይነቶች እና በስራቸው የሚያካትቷቸው ገጽታዎች በዚህ ጥናት በግብአትነት ውለዋል። በባህላዊ አውድ ስር "ገዳሙ" መቼ ተመሰረተ? እንዴት ተመሰረተ? የስልጣን ተዋረዱ ምን ይመስላል? መተዳደሪያ ህጉ ምንድን ነው? የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ቀርበዋል። "የገዳማውያኑ" የእርስ በርስ መግባባት እንዴት ተገልጿል? የወንድ እና ሴት "ገዳማውያን" ግንኙነት ምን ይመስላል? ገዳማውያኑ እንዴት ይግባባሉ? ሺሆቹን በምን መንገድ ይገልጿቸዋል? ችግራቸውን እንዴት ያስረዳሉ? እንዴት ይጸልያሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በማህበራዊ አውድ ደግሞ ማህበራዊ ደረጃቸው ምንድን ነው? ደረጃው በከዋኙው ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ምንድን ነው? መተዳደሪያቸው ምንድን ነው? የሚገኙበት ሁኔታ ምን ይመስላል? የግለሰቦቹ ሚና እና አስተሳሰብ በቡድኑ ውስጥ እንዴት ይገለጻል? እና መሰል ጉዳዮች ትኩረት ተደርጎባቸዋል።

ቅርጽ፡- አንድ ክዋኔ በማህበረሰቡ ስምምነት እና ፈቃድ የተቀመጠ የራሱ የሆነ ቅርጽ አለው። በከዋኔ ላይ ህልውናቸው የተመሰረተ የፎክሎር አይነቶች ሁሉ በሚከወኑበት ወቅት የራሳቸው ቅርጽ አላቸው። ይህም የከዋኔውን መነሻ፣ ሂደት እና ፍጻሜ የሚያመላክት ነው (ሲምስ፣2005፣95)። በምእራፍ አራት ትንተናው ቅድመ ዝግጅት፣ አውደ በአል እና የበአል ማገስት በሚል እንዲከፋፈል የሆነው በቅርጹ ነው።

አስተያየት/ ሂስ፡- አስተያየት አንድም በከዋኙ (ራሱን በራሱ) አንድም በታዳሚው የሚሰጥ፣ ድክመትን ለማሻሻል እና ጥንካሬን ይዞ ለመዝለቅ የሚያስችል ስልት ነው። ሂሱ ክዋኔው ቅርጹን ጠብቆ እንዲከናወን ትልቅ ድርሻ ያበረክታል በማለት እነ ሲምስ (2005፣167) ይገልጻሉ። በከዋኙ የሚሠጠው ሂስ ከክዋኔው አስቀድሞ የሚከናወን ሲሆን "እኔ ክዋኔ (ዳንስ፣ ዘፈን፣ ጭፈራ) ላይ ብዙም አይደለሁም" በማለት ታዳሚው ከእሱ ብዙም እንዳይጠብቅ የሚያደርግበት ስልት ነው። በዚህ ጥናት ከሴት "ገዳማውያን" መረጃ ሲሰበሰብ ለሚጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እና ለማሳየት ሲጠየቁ "እኔ አልችልም እሷ ትሻላለች" በማለት ጉዳዩን ከራስ ወደ ሌላ ይገፋሉ። ይህ ሁኔታ በኋላ ላይ ከታዳሚው ከሚሰነዘር ሂስ ለመዳን ያስችላል። በአንጻሩ በታዳሚ የሚሰጠው ግምገማ ሁለት ነገሮችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው።[23] ከዋኙ በትክክል አልከወነውም ብሎ ካሰበ ክዋኔው ሳያልቅ የከዋኙን ሚና በመንጠቅ

[23] እዚህ ላይ አንድ ከዋኝ በናጠና ልዩ ልንላቸው ይገባል ያልናቸውን ጉዳዮች ያስታውሷል።

ቅሬታቸውን ይገልጻሉ። የከዋኙ ችሎታ ጥሩ ነው ብለው ካሰቡ ደግሞ በሞራል በማበረታታት እና ሽልማቶችን በመስጠት ይሁንታቸውን ያሳያሉ።

በአጠቃላይ በክዋኔ ላይ የተመሰረተ የአጠናን ዘዴ በዋናነት በክዋኔ ባህሪዎች እና ገጽታዎች ላይ ተመስርቶ ጥናት የሚያካሂድ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ክብረ በአላት የተተነተኑት ከላይ በተዘረዘሩት የክዋኔ ባህርያት ላይ ተመስርተው ነው።

# ምእራፍ ሶስት

## 3. የጡሩሲና "ገዳም" ከገዳማዊ ህይወት አንፃር እና "የገዳሙ" መነሻ ትርክት

ይህ ክፍል በእስም አቀፍ እና በአገራችን "የገዳም" እና "ገዳማዊ" ህይወት ብያኔዎችን በማካተት የጡሩሲናን መስጊድ "ገዳም" ብሎ መጥራት መቻል አለመቻሉን ያሳያል። በእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮት "የገዳም" ህይወት ሳይኖር በአገራችን በተለይ በወሎ አካባቢ እንዴት ሊኖር ቻለ? ለሚለው ጥያቄም ምላሽ ይሰጣል።

### 3.1. የጡሩሲና "ገዳም" ከገዳማዊ ህይወት አንፃር

#### 3.1.1. የገዳም እና ገዳማዊነት ትርጉም

ስለ ገዳም ምንነት በርካታ ሰዎች ጽፈዋል። ኪዳነወልድ ክፍሌ "ገዳም (ማት፣ እብ፣ ሚቅላጥ) በቁሙ ምኔት፣ ደብር፣ የመነኮሳት ሰፈር፣ ቃላት ቤተክርስትያን፣ በደለኛ ሸሽቶ የሚጠጋበት፣ ደውሉ የሚማጠንበት ደብር፣ ምስካይ፣ ዱር፣ ጫካ፣ ወማ፣ በረሀ፣ በዳ፣ ከሀገር ከመንደር የራቀ የአራዊት ክፍል..." (1948፣302) በማለት ገልጸውታል። በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው አማርኛ መዝገበ ቃላት "ገዳም መነኮሳት ከአለማዊ ኑሮ ተገልለው በሀይማኖታዊ ስርአት እና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተክርስትያን ሲሆን አንድ ሰው ገዳም ገባ ሲባል አለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር መቀመጥ ጀመረ ማለት ነው" (1993፣507) በማለት የገዳምን ምንነት አስፍሯል።

ምንኩስና የሚለው ቃል monahos ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ብቸኛ ማለት ነው። ብህትውና የሚለው ቃል ደግሞ ተባህተውን ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው። ትርጉሙም ብቸኛ ሆነ ተለየ ተነጠለ ማለት ነው (ምክረስላሴ፣2000፣356)። ሁለቱም ትርጉሞች ከሰው ከህብረተሰቡ ተለይቶ መኖርን ያመላክታሉ።

በአጠቃላይ ጥቅሶቹ የሚያመለክቱን ምንኩስና ራሳቸውን ለፈጣሪ ለማስገዛት እና ለፈጣሪ ለማትረብ፣ ይህንን አለም ንቀው ሀብት ንብረታቸውን ትተው፣ ከዘመድ አዝማድ ተለይተው እምላካቸውን ለማገልገል በዋሻ፣ በዱር፣ በበረሀ ጎጆ ቀልሰው፣ ሳር ቅጠል ነስንሰው፣ ኢጋንንትን እና አራዊትን ሳይፈሩ በገዳም ተወስኖ የሚኖርበት ህይወት መሆኑን ነው።

የገዳም ህይወት የክርስትና ሀይማኖት ከመጀመሩ በፊት በምስራቅ እና በሩቅ ምስራቅ ባሉ አገራት ውስጥ በሚገኙ ሀይማኖቶች ነው። ከሀይማኖቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ቡድሂዝም፣ ሂንዱይዝም፣ ብራህማኒዝም እና የአይሁድ እምነት ይጠቀሳሉ (ምክረ ስላሴ፣2000፣358)። የገዳም መመስረት መሰረታዊ ምክንያቶች ከዘመነ ኔሮ እስከ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ (ከ64-320ዓ.ም) ድረስ በክርስትያኖች ላይ የመጣው ስደት፣ አማኞች በጠንካራ የወንጌል ስርጭታቸው እንዲሁም በባህላዊ እምልኮ ሳላመታዘዝ በወሰዱት አቋም እና ወንጌል ሰዎችን ወደ ገዳም ይገቡ ዘንድ አመላክቷል የሚለው አመለካከት እንደሆነ ስሜ ታደሰ(2001፣133) ጽፏል።

ካፍ (1968፣169) እንደጻፈው በ1600 ቅድመ ልደት ክርስቶስ ላይ የሂንዱይዝም እና የብራህማኒዝም እምነት ተከታዮች ከአለም ተለይተው ፈጣሪያቸውን በመለመን በጾም እና በጸሎት ተወስነው በዱር፣ በገደል እና በዋሻ ይኖሩ ነበር። በ7ኛው ምእተ አመት የቡድሂዝም መናንያን ከሰው ተለይተው ኑሯቸውን በገደል እና በጫካ ማድረጋቸውን አክሏል።

በአይሁድ እምነት የምንና እና የምንኩስና ህይወት የተለመደ ነው። በዚህም ናዝራውያን በሚል መጠሪያ ከማህበረሰቡ ተለይተው በብቸኝነት የሚኖሩ ሰዎች እንደነበሩ (ምክረ ስላሴ፣2000፣358) ይገልጻሉ። ምናኔን ከመረጡ ሰዎች ውስጥ ነቢዩ ኤልያስ፣ ነቢዩ ኢሳያስ እና መጥምቁ ዮሀንስን ይጠቅሳሉ። ከናዝራውያን በተጨማሪ "ኤሴኔስ" የተባሉ በአንድነት የሚኖሩ አይሁዳውያን በጊዜው የነበረውን የቤተክህነት እና የመንግስትን አቋም በመቃወማቸው ገዳም መስርተዋል። በዚህ ማህበር ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛምርቶች እንደነበሩ ምክረ ስላሴ አክለው ጽፈዋል። የኢሴኔስ መናንያን ማህበር ለክርስትና ሀይማኖት የምንኩስና ህይወት መንገድ ጠራጊ ነው ሲል ካፍ (1968፣66)ይገልጻል። ከሌሎቹ ሀይማኖቶች በተቃራኒ በእስልምና ሀይማኖት የገዳም ህይወት እንደሌለ ኦልሰን "There is No Monasticism in Islam"(2008,132) በማለት አስፍሯል።

በአለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚው በግል የተደረገ የምንና ኑሮ ቀዳሚ ነው። ይህንን ህይወት በመጀመር ፈር ቀዳጅ የሆኑት አባ ጳውሊ ሲሆኑ የጀመሩትም በግብጽ አገር ነው። አባ ጳውሊ በጊዜው ጨካኝ የነበረውን መንግስት ለመሸሽ በማሰብ በ22 አመታቸው የምናናን ህይወት ጀምረዋል።

በእኛ አገር የኦርቶዶክስ ክርስትና በግል የሚደረግ የገዳም ኑሮ አይነቱ "ቁሪት" ይባላል፡፡ ሰዎቹ የብቸኝነትን ህይወት የሚመርጡበት ምክንያት የሚኖሩበትን አለም በመናቃቸው እንደሆነ ምክረ ስላሴ (2000፤359-361)ያስረዳሉ፡፡

> የዚህ አለም ኑሮ የክፋት፣ የተንኮል እና የሀጢያት ኑሮ ስለሆነ ከእግዚአብሄር የሚያርቅ እንጂ ወደ እግዚአብሄር የሚያቀርብ አይደለም፡፡ ስለዚህ መንፈሳውያን ሰዎች ወደ እግዚአብሄር ቀርቦ ለመገኘት ከአለም መራቅ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት ይህንን አለም ንቀው፣ ቤት ንብረታቸውን ትተው፣ ከሰው ከዘመድ አዝማድ ተለይተው መኖርን በመፈለግ ወደ ዱር፣ ዋሻ፣ ምድረ በዳ ይሰማሩ ጀመር፡፡

ጥቅሱ ሰዎች ወደ ገዳም የሚገቡት የተቀደሰ ህይወት መኖር የሚቻለው "ተለይቶ በመውጣት ነው" በሚል እምነት እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በሁለተኛነት የሚጠቀሰው የገዳም ሕይወት በርካታ ሰዎች በአንድነት የሚኖሩበት ስርአት ነው፡፡ ስርአቱን በማስጀመር አባት አባ ጳቆሚስ ይጠቀሳሉ፡፡ በ325 ዓ.ም አንድ መልአክ በራእይ ተገልጾላቸው በላእላይ ግብጽ በአባይ ባህር አጠገብ "ታቤኒ" በሚባል ስፍራ አንድ የመነኮሳት ስፍራ መመስረታቸው እና የገዳሙን ህግ ማውጣታቸው ይነገራል (ምክረስላሴ፣2000፣369-370)፡፡ ይህ የገዳም ህይወት በእኛ አገር "የአንድነት" ገዳም በመባል ይጠራል፡፡

በአንድነት ገዳም ገዳማውያኑ በማህበር እንደ ችሎታቸው እና ፍላጎታቸው በተለያዩ አገልግሎቶች ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ገዳማውያኑ ሙሉ በሙሉ ለገዳሙ ህግ ተገዢ ሲሆኑ በገዳሙ የተቀመጠውን የአለባበስ፣ አመጋገብ፣ አሰራር…ህግ እና ደንብ እንዲያከብሩ ይገደዳሉ (ሞገስ፣2003፣37)፡፡ በአገራችን ከሚገኙ የአንድነት ገዳማት መካከል ጣና ቂርቆስ አንድነት ገዳም፣ ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያም እና ቅድስት ስሉሜ የሴቶች አንድነት ገዳም፣ ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም… ይጠቀሳሉ፡፡ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው የጡሪሲና መስጊድ ከገዳምና ከገዳማዊ ህይወት አኳያ ምን ይመስላል የሚለውን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 3.1.2. የጡሩሲና "ገዳም" ከገዳማዊ ህይወት አንፃር

የጡሪሲና "ገዳም" ሰው የማይኖርበት እና በዱር የተከበበ ቦታ ነው። ገዳማውያኑ ከሩቅ አገር፣ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው፣ ሀብት ንብረታቸውን ትተው፣ በአጠቃላይ "አለማዊ ህይወትን" ንቀው ለአምላካቸው (ለአላህ) ለመገዛት የወሰኑ ናቸው። በዚህ ምክንያት መስጊዱን "ገዳም" ወደ መስጊዱ የገቡ ሰዎችን "ገዳማውያን" ብሎ መጥራት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም የጡሪሲና "ገዳም" በአለም አቀፍ እና በአገራችን ከተለመዱት ሁለት የገዳም አይነቶች መካከል ከአንድነት ገዳም ጋር ተመሳስሎው የጠነከረ ነው። ለምሳሌ ብንጠቅስ በአንድነት ገዳም አንድ ገዳማዊ አንዴ ገዳም ከገባ በኋላ መውጣት አይፈቀድለትም፤ በገዳማውያኑ መካከል የእኔ የእነሱ የሚባል ንብረት ሳይኖር ሁሉም የተገኘው ተካፍሎ ይበላል፤ በገዳማውያኑ የሚከወኑ የጋራ እውቀቶች አሉ፤ የገዳሙ ህግ እና ደንብ እጅጉን ይከበራል፤ ገዳሙ የሚተዳደርበት አስተዳደራዊ መዋቅር እና የስራ ክፍፍል አለ፤ በገዳሙ ግለሰባዊ እና ማህበራዊ የሆኑ ችግሮች ይፈታሉ። እነዚህ እና መሰል የጋራ ስምምነቶች እና ህጎች "ቁሪት" ተብሎ ከሚታወቀው የገዳም ስርአት እንደሚለዩ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት። ከዚህ ቀጥሎ የጡሩሲና "ገዳም" አጠቃላይ ገጽታ ከአንድነት ገዳም መገለጫዎች አንጻር ቀርቧል።

#### 3.1.2.1 የመግቢያ መስፈርት

ወደ ጡሩሲና "ገዳም" ለመግባት ወንዶች የሚጠየቁት ነገር ሶላት መስገድ፣ ሚስት እና ልጆች አለመኖር እና ወደ ገዳሙ መግባት መፈለግ ብቻ ነው። በአንጻሩ በሴቶቹ በኩል መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ከሀጂ ነቢይ (ወንድ) ጋር አለመገናኘት፣ ቀለባቸውን የሚያመጣላቸው ዘመድ መኖር፣ ትዳር እና ልጅ አለመኖር፣ አንዴ ከገቡ በኋላ ቢታመሙ ወጥተው ህክምና ለማግኘት አለመፈለግ እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሞት፣ ሰርግ፣ ህመም… ቢኖርም አለመውጣት እንደሆኑ አቶ አህመድ መሀመድ (ቃ.መ፣ ጥር28፣ 2004፣ ሼክላ) ያስረዳሉ።

#### 3.1.2.2 "የገዳማውያኑ" አኗኗር

"በገዳማውያኑ" መካከል ያለው ቅርበት የእኔነት ስሜት እና አመለካከት የሌለበት መሆኑን አቶ መሀመድ አማን ይናገራሉ (ቃ.መ፣ ጥር28፣ 2004፣ ሼክላ)። በምግብ በኩል ሴቶቹ የሚመጣላቸውን ተካፍለው የሚበሉ ሲሆን ከዘመድ የሚመጣው ምግብ ሲቋረጥ ወንዶቹ ለቁርአ በማለት ለምነው ይሰጧቸዋል። በሴቶቹ እና በወንዶቹ "ገዳም" ውስጥ በርካታ ጎጆዎች

ሲኖሩ፣ ጎጆዎቹ በአንድ ደረሳ ስም አይጠሩም። "በገዳሙ" ውስጥ የሚገኙ ቁርአኖች፣ መስገጃዎች፣ ኪታቦች፣ መከተቢያዎች...ሁሉም "የገዳማውያኑ" የጋራ ንብረት ናቸው።

### 3.1.2.3. የገዳማውያኑ የጋራ እውቀቶች

የሁሉም "ገዳማውያን" የእለት ተእለት ተግባር ቁርአን መቅራት፣ ሶላት መስገድ፣ አውራድ ማውረድ፣ ዱአ ማድረግ ሲሆን በእንቅልፍ የሚያሳልፉት ሶስት ሰአት ብቻ ነው። ከዱአ በሚተርፋቸው ጊዜ የሚሰሯቸው የጋራ እውቀቶች አውራድ ማውረድ እና ኪታብ መከተብ እንደሆኑ አቶ መሀመድ አማን (ቃ.መ፣ ጥር28 ፣2004፣ ሼክላ) ይተርካሉ። ኪታብ እና አውራድ ለመከተብ እንደ መስፈርት የሚቆጠሩት ሁለት ጉዳዮች ቁርአን ማክተም እና እንዲከትቡ ከሼሁ ፈቃድ ማግኘት ናቸው። በዋናነት ኪታብ የሚከትቡት አስሮቹ ሴቶች ሲሆኑ የሚጽፉበት ወረቀት በመጠኑ እና በጥራቱ ከፍ ያለ እንደሆነ መሬማ እድሪስ[24] (ቃ.መ፣ የካቲት01፣ 2004፣ ጡሩሲና) ታስረዳለች። የሚከትቡበት ቀለም "መድ" ይባላል። መዱን ለማዘጋጀት፣ ባትሬ ድንጋይ ይቀጠቀጣል፣ ጥቁሩ ነገር ተመርጦ ይወጣል፣ ይቆላል፣ በጣም ታሽቶ ይፈጫል፣ በተፈጨ በሶስተኛ ቀን ሙጫ ይደረግበታል፣ ሙጫው እንዲሟሟ ጸሀይ ላይ ይሰጣል (አራት ቀን ይቆያል)፣ በሰባተኛ ቀኑ እየተቀነሰ በውሀ ይበጠበጣል፣ ውሀው ይጠላል። በመጨረሻም ቀለሙ በሚነክርበት ቀስም ይከትባሉ።

ኪታብ እና አውራድ የመከተብ የጋራ እውቀት የሀይማኖቱን አስተምሮዎች ሰንዶ በማስቀመጥ በኩል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ስሜ ታደሰ (2002፣137) የገዳም ኑሮ መስፋፋት በአለም ላይ ካመጣው በጎ ተጽእኖ ውስጥ "ከቅዱሳን መጻህፍት" ውጭ የሆኑ የጥንት ጽሁፎችን በመገልበጥ ከጥፋት መታደግ እና የትውልድ ቀጣይነትን አስተማማኝ ማድረግ እንደሆነ ገልጿል።

---

[24] መሬማ እድሪስ እድሜዋ 31 ሲሆን በሴቶች "የገዳም" መቆትር ውስጥ አስሩ ደረሶች ውስጥ ትካተታለች። ጠዋውን ጊዜዋን የምታሳልፈው ኪታብ በመከተብ እና አውራድ በማውረድ ሲሆን በአከታተቧ ጥሩ ከሚባሉ ደረሶች ውስጥ ትመደባለች።

### 3.1.2.4 "የገዳሙ" ህግ እና አስተዳደራዊ መዋቅር

'በገዳሙ' ውስጥ የሚከለከሉ እና የሚፈቀዱ ነገሮች "በገዳማውያኑ" እጅጉን ይከበራሉ፡፡ ከሚከለከሉት ነገሮች መካከል ወንዶች እና ሴቶች መገናኘት፣ እርስ በርስ መጣላት፣ ከተጣሉም ቂም መያዝ፣ የውጭውን አለም መናፈቅ፣ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ለመውጣት መሞከር…ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡[25]

'በገዳሙ' ውስጥ በሴቶች እና በወንዶች የሚተገበሩ አስተዳደራዊ መዋቅሮች አሉ፡፡ የሴቶቹ ገዳማዊ መዋቅር በአምስት የተከፋፈለ ነው፡፡ በቀዳሚነት የሚጠቀሱት ከአምስቱ መስራቾች አንዷ የሆኑት ሰይዳ ሼክ ኢብራሂም ናቸው፡፡ እኚህ ሴት በገዳማውያኑ "እሜቴ"[26] በመባል ይጠራሉ፡፡ የስራ ድርሻቸውም አጠቃላይ የሴቶቹን "ገዳም" መቆጣጠር፣ ማሰገድ እና ቁርአን ማስቀራት ነው፡፡ ቀደም ሲል ቁርአን ያስቀሩ ነበር፤ አሁን ግን ብዙዎቹ ደረሳዎች ቁርአን ስላከተሙ/ስለጨረሱ እርስ በራስ ስለሚቀራሩ ማስቀራት አቁመዋል፡፡ "በገዳሙ" ውስጥ ለብቻቸው ተከልሎ የተሰራ ቆርቆሮ ቤት ያላቸው ሲሆን ከወንዶቹ የሚመጣውን መልእክት በወንድማቸው አማካይነት ይቀበላሉ፡፡ እሜቴ "በገዳሙ" ስልጣን እርከን በቀዳሚነት ቢጠቀሱም "እዚህ መስጊድ ውስጥ አለቃ የለም ሁሉም ለራሱ አለቃ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከእሜቴ ቀጥሎ በሴቶቹ "ገዳም" ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ዱበርቲዎች (ዱአ አድራጊዎች) ናቸው፡፡ የዱበርቲዎች አለቃ ፋጢማ[27] ሲባሉ ብዙውን እድሜአቸውን በዚህ "ገዳም" ውስጥ ያሳለፉ ናቸው፡፡ ሌሎች ዱበርቲዎች ግን በእንግድነት "ገዳሙ" ውስጥ ከ2 እስከ 3ወር የሚቀመጡ እና ወደመጡበት የሚመለሱ ናቸው፡፡ የዱበርቲዎቹ ዋና ስራ "ገዳሙን" ለመዘየር የሚመጡ ሰዎችን እና ይዘው የሚመጡትን ነገር መቀበል፣ መመረቅ፣ ተቸግረው የሚመጡ ሰዎችን ችግር በመስማት ዱአ ማድረግ፣ "ገዳሙ" ውስጥ ለሚኖሩ እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ዱአ ማድረግ… ናቸው፡፡

---

[25]ለዚህ ጥናት 'በገዳሙ' በቆየሁበት ወቅት አሚናት የሱፍ የምትባል "በገዳሙ" ለ11 አመት የኖረች "ገዳማዊ" አግኝቼ ነበር፡፡ ከሶስት ወር በፊት እመመኝ በማለት ለህክምና በመውጣቷ ከገዳሙ እንደተባረረች አጫውታኛለች፡፡ በአሁኑ ወቅት ከደረሳዎቹ ጋር እንድትገናኝ አይፈቀድላትም፡፡
[26] በቁጥር 12 ላይ የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡
[27] ቁጥር 11 ላይ የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻን ይመልከቱ፡፡

ካዳሚዎች በሶስተኛ መዋቅር ላይ ይገኛሉ። ከካዳሚዎች ውስጥ ፈቃደኛ ሆነው ስማቸውን ከተናገሩት ውስጥ እሚናት አህመድ[28]፣ እንሻ ጧሂር አብዱ[29] እና የሺ ፋጢማ[30] ይገኛሉ። የስራ ድርሻቸው ቡና ማፍላት፣ ምግብ ማቅረብ፣ የዱበርቲዎችን ልብስ ማጠብ እና እንግዳ መቀበል ነው።

ከካዳሚዎቹ በሚቀጥለው መዋቅር ስር አስሩ ደረሶች ይገኛሉ። በግምት ከ1978 ጀምሮ "ገዳሙ" ውስጥ በቋሚነት መኖር የጀመሩት እነዚህ ደረሶች ከሌሎቹ ደረሶች በተለዬ መኖሪያ ስፍራ ተሰርቶላቸው ይኖራሉ። ለዚህ ምክንያቱ "በገዳሙ" ረጅም ጊዜ ማሳለፋቸው እና ጥልቅ እውቀት ማካበታቸው ነው። መኖሪያቸው ከዋናው የሴቶች "ገዳም" በአጥር የተለየ ሲሆን በውስጡም አራት ጎጆ ቤቶች እና ሁለት ቆርቆሮ ቤት ይገኛሉ። ቤቶቹ ለቁርአን መቅሪያነት፣ ለኪታብ መጻፊያነት እና ማስቀመጫነት[31]፣ ለመኝታነት፣ ለምግብ ቤትነት፣ ለኡዱ እና ለእስቲንጃ (የመራቢያ አካል እጥበት)፣ አውራድ ማውረጃነት ያገለግላሉ።

ደረሶቹ ከሌሎች "ገዳማውያን" የሚለዩበት ሌላው ጉዳይ ምግብ አለመስራታቸው ነው። በመሆኑም አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት ቁርአን በመቅራት፣ በመስገድ፣ አውራድ በማድረግ፣ በአረብኛ የተጻፉ አውራዶችን እና ኪታቦችን በመገልበጥ ነው።

"በገዳሙ" የስልጣን እርከን ውስጥ የመጨረሻውን ቦታ የሚይዙት በቁጥር አንድ መቶ አንድ የሚሆኑት ደረሶች ናቸው። በዚህ ስር የሚካተቱት ደረሶች "በገዳሙ" ከአስር አመት በታች የቆዩ ናቸው። እድሜአቸውም ከሰባት አመት ጀምሮ እስከ ሰላሳ ይደርሳል። የስራ ድርሻቸው እንጀራ መጋገር፣ ውሀ መቅዳት እና ግቢ ማጽዳት ናቸው። በዋናነት ስራቸው ቁርአን መቅራት፣ ኪታብ መቅራት፣ሶላት መስገድ እና እልፎ አልፎ ኪታብ መከተብ ነው። ደረሳዎቹ ሶስት ጎጆዎች እና ሁለት ቆርቆሮ ቤቶች አሏቸው። አንደኛው ቆርቆሮ ቤት ለሁሉም ሴቶች

---

[28] እሚናት መሀመድ ስለይማን ባለቤታቸው እና ወንድ ልጃቸው በተከታታይ ሲሞቱባቸው "ዱንያ(አለም) ለምኔ" ብለው የቀረቻቸውን አንዲት ልጅ (ፋጡማ አሊይ መሀመድ ትባላለች) ለደረሳነት "ገዳም" ውስጥ አስገብተው ራሳቸውን "የገዳሙ" ካዳሚ አድርገው ለመኖር የመረጡ ሴት ናቸው።
[29]እንሻ ጧሂር አብዱ ትዳር ይዘው አይናቸውን በአይናቸው ማየት ቢታደሉም ልጃቸው ግን "አንድ ለናቷ" ሆና መውለድ እንቢ አላቸው። በባህላዊ መንገድ ልጅ ለማግኘት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም።በዚህም ተስፋ የቆረጠው ባለቤታቸው (ኑሩ ሀቢብ ይባላሉ) እርሳቸውን ፈትተው ሌላ ሚስት አገባባቸው። ልጃቸውን ይዘው ከዘመድ ቢጠጉም ከመሰልቸት አልዳኑም። እናም የ12 አመት ልጃቸውን ሰአዳ ኑሩ ሀቢብን ይዘው ወደ ጡሩሲና "ገዳም" መጡ። "ገዳማውያኑ" እሳቸውን በካዳሚነት ልጃቸው በደረሳነት ተቀብለዋቸዋል። የካዳሚነት ህይወት ከበፊት ህይወታቸው ጋር እያነጻጸሩ እንዲነግሩኝ ስጠይቃቸው "አሁን ያለሁት እኮ የምድር ጀነት ላይ ነው መካ መዲና ነው ያለሁት ከዛኛው ህይወቴ ጋር አይገናኝም" ነበር መልሳቸው።
[30] በቁጥር 10 ላይ የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።
[31] ይህንን ክፍል "ገዳማውያኑ" ስርጥ በማለት ሲጠሩት ዙሪያውን በነቢዩ መሀመድ ስም እና በአላህ ስሞች እንዲሁም በተለያዩ መስጊዶች ምስል ያሸበረቀ እና በጣም የሚያምር ነው።

ቁርአን መቅሪያ እና ኪታብ መከተቢያ፣ ሌላው ቆርቆሮ ቤት ለኡዱና ለእስቲንጃ፣ አንዱ ጎጆ ቤት ለመኝታ አገልግሎት ይውላል፣ ሌላኛው ጎጆ ለማረፊያና ብቻ ሆኖ ዱአ ለማድረግ፣ የመጨረሻው ጎጆ ምግብ ማብሰያ እና የምግብ እቃ ማስቀመጫነት ያገለግላል፡፡

የወንዶቹ አስተዳደራዊ መዋቅር በአራት ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ "የገዳሙ" አስተዳዳሪ እና መስራች ሼህ መሀመድ አማን ይገኛሉ፡፡ ሀላፊነታቸው "በገዳሙ" የሚከናወኑ አጠቃላይ ጉዳዮችን መቆጣጠር፣ ወደ "ገዳሙ" መግባት የሚፈልጉ ሰዎች ሲመጡ ዉሳኔ መስጠት፣ ወደ "ለገዳሙ" የሚሰጡ የእርዳታ ገንዘብ እና ምግቦችን በመቀበል ለሚመለከታቸው እንዲከፋፈሉ ትእዛዝ መስጠት፣ ከበአላት ውጭ የሚመጡ እንግዶች ካሉ መዘየር እና ማስተናገድ እንዲሁም "ለገዳማውያኑ" እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ሰላም ዱአ ማድረግ ናቸው፡፡

በሁለተኛው መዋቅር "በገዳሙ" ውስጥ ረጅም እድሜን ያሳለፉ ደረሳዎች ይገኛሉ፡፡ ከደረሳዎቹ መካከል ሼህ አሊይ አዋራ (የሼሆቹ ተላላኪ) እና ሼህ መሀመድ ሰይድ (የሼሁ አነጋጋሪ) ይጠቀሳሉ፡፡ የደረሳዎቹ ዋና የስራ ድርሻ ሼሁን መጠበቅ እና ማገዝ ነው፡፡ በዚህም ሼሁ ሲያገኘው ያስታምማሉ፣ ሼሁን ለመዘየር የሚመጡ እንግዶችን ያስተናግዳሉ፣ በመጨረሻም በሼሁ አማካይነት የሚተላለፉ መልእክቶችን ያደርሳሉ፡፡ "በገዳሙ" ውስጥ የሚያጋጥሙ ቀለል ያሉ ጉዳዮችን እንደ ሼሁ በመሆን የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡

ከሼሁ ጠባቂዎች በመቀጠል በሶስተኛነት የሚጠቀሱ ደረሳዎች አሉ፡፡ እነዚህ ደረሶች የየራሳቸው ሚና እና ሀላፊነት ያላቸው ሲሆኑ የስልጣን ልዩነት ግን የላቸውም፡፡ ሼህ አብዱል፣ ሼህ ያሲን ከሊል፣ ሼህ አሊይ እድሪስ፣ ሼህ አህመድ ኑሩ፣ ሼህ የሱፍ አረብ እና ሼህ አህመድ አሊይ ይጠቀሳሉ፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ "በገዳሙ" ውስጥ ውሀ በመቅዳት፣ ታላላቆችን በመታዘዝ፣ ገዳሙን በማጽዳት የሚያገለግሉ በርካታ ደረሳዎች አሉ፡፡ ኪታብ በማንበብ፣ ቁርአን በመቅራት፣ ሶላት በመስገድ እና ዱአ በማድረግ ያሳልፋሉ፡፡

#### 3.1.2.5. የጡሩሊና "ገዳም" "ለገዳማውያኑ" እና ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ

የጡሩሊናን "ገዳም" ገዳም ብሉ ለመጥራት ካስቻሉ ምክንያቶች መካከል በመጨረሻ የሚነሳው "በገዳሙ" ግለሰባዊ እና ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮች መፍትሄ ማግኘት መቻላቸው ነው፡፡ "በገዳሙ" ውስጥ የሚኖሩ "ገዳማውያን" ሲታመሙ በታላላቆቻቸው አማካይነት መፍትሄ ይፈለግላቸዋል፡፡ ጉዳዮቹ ከታላቆቹ አቅም በላይ ከሆነ ወደ ሼሁ ጋር ይደርስና እልባት ይበጅለታል፡፡ "ገዳሙ"

"ከገዳማውያኑ" በተጨማሪ ለአካባቢው ማህበረሰብ በርካታ ግልጋሎቶችን ይሰጣል፡፡ ለአብነት ከውጭ አገር "ለገዳሙ" የሚላከውን ገንዘብ በአብዛኛው ለአካባቢው ማህበረሰብ እና ለተቸገሩ ሰዎች ያደርሳሉ፡፡ በእርዳታ መልክ ሰዎች የሚልኩትን የምግብ ዱቄት ለአካባቢው ማህበረሰብ ያከፋፍላሉ፡፡ በሽምግልና አልፈቱ ያሉ ግጭቶች ወደ "ገዳሙ" ከመጡ ወዲያው መፍትሄ ያገኛሉ፡፡ በአገሩ ችግር እና ሞት ሲበረታ ወደ "ገዳሙ" በመምጣት ዱአ ያስደርጋሉ፡፡ በአካባቢው በሚከናወኑ የልማት ስራዎች ላይ ወንድ "ገዳማውያን" ይሳተፋሉ፡፡ ሰዎቹ ሲሞቱ ቁርአን በመቅራት እና ሶላት በመስገድ የቀብር ስርአታቸውን "ገዳማውያኑ" እንደሚያስፈጽሙ አቶ መሀመድ አማን (ቃ.መ፣ ጥር28 ፣2000፣ ሺከላ) ይተርካሉ፡፡

## 3.2. የጡሩሲና "ገዳም" መነሻ ትርክት

ይህ ክፍል "ገዳሙ" ከሚገኝበት ስፍራ ባህል እና ሀይማኖት አንጻር በእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮት የሌለው "የገዳም" ህይወት በአገራችን እንዴት ሊኖር እንደቻለ መነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡ በአገራችን ያለው የእስልምና እና የክርስትና ሀይማኖቶች መቻቻል እና ተከባብሮ የመኖር ባህል ረጅም ጊዜን ያስቆጠረ ነው፡፡ የሀይማኖቶቹ የመደጋገፍ የእስልምና ሀይማኖት ወደ ሀገራችን ከገባበትን ታሪክ ጋር ይገናኛል፡፡

ነቢዩ መሀመድ እስልምናን ባስፋፉበት ዘመን ሰዎቻቸው በጠላቶቻቸው (ቁረይሾች) ስቃይ እንደደረሰባቸው ሲመለከቱ ለተከታዮቻቸው መሸሸጊያነት የመረጧት አገር ኢትዮጵያ ነበረች፡፡ በጊዜው የክርስትና ሀይማኖት ተከታይ የነበሩት የኢትዮጵያ ንጉስ ከነቢዩ መሀመድ ጠላቶች የመጣላቸውን ጥቅማጥቅም ሳይቀበሉ ለስደተኞቹ ከለላ መስጠታቸውን ስፔንሰር (1952፣45) አስፍሯል፡፡[32] በዚህም በነቢዩ መሀመድ በጦርነት እንዳትፈለግ ቃል የተገባላት አገር መሆን እንደቻለችም ጆን አቤንክ (1998፣111) ጽፏል፡፡

[32] "...which made it appear that islam is a form of Christianity, and after hearing his defence the nejashi saw no reason to listen to the demands of the quraish and gave his protection to the refugees"(1952፡45).

ንጉሱ ለስደተኞቹ ከለላ መስጠቱ ለዘለቀው የክርስትና እና የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች የመተጋገዝ ባህል መሰረት ከመጣሉ በላይ ኢትዮጵያ የእስልምና ሀይማኖትን በሰላም ከተቀበሉ አገራት ቀደምት አድርጓታል። እስልምና ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ወደተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በተለይ በወሎ መስፋፋት ችሏል። ጌታቸው መኮንን (1984) በወሎ የእስልምና ሀይማኖት እንዴት እንደተስፋፋ ሲገልጹ፡-

> ወደ ምስራቅ ወሎ እስልምና ለመጀመሪያ ጊዜ የገባው በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በሸዋ የሱልጣን መንግስት ምስረታና ከአስራ ሁለተኛው እስከ አስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን የይፋት መንግስት ምስረታ መካከል ነው። በወሎ እስልምና የተስፋፋው በ16ኛው አጋማሽ ላይ ሲሆን በዚህ ዘመንም የኦሮሞ ብሄረሰብ ወደ አካባቢው የተስፋፋበት ነበር። የኦሮሞዎች ወደ ወሎ መፍለሳቸው እና በአንድ ላይ መኖራቸው ኦሮሞዎች የእስልምና ሀይማኖት እንዲቀበሉ ሲያደርጋቸው በአንጻሩ የወሎ ሙስሊሞች ከኦሮሞዎቹ ያገኟቸውን ባህላዊ ልማዶች (ዛር፣ ወዳጃ፣ ደም…) ከሀይማኖታቸው ጋር አጣምረው እንዲተገብሯቸው አጋጣሚ ፈጥሯል (1984፣45-46) ብለዋል።

ሁሴን አህመድ በወሎ የሚገኙ ሙስሊሞች የሚከውኗቸው ነገሮች ሀይማኖቱ ከሚፈቅደው በተጨማሪ ባህላዊ እምነትን ያካተተ እንደሆነና እነዚህንም ከኦሮዎች የወሰዷቸው እንደሆኑ በመግለጽ የጌታቸውን ሀሳብ ያጠናክራሉ።።

> Another crucial aspects of islam in Wallo was heavily influenced by the culture of the oromo many of the feateres of traditional belief system and practices which are recognizable in 19th century…which the contemporary muslim reformers, attempted to eradicate…were laregely of oromo origin. Although some like the zar (2001፣28-29).

ከኦሮሞዎቹ የወረሷቸው ባህላዊ ልማዶች በእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን በወሎ በሚገኙ የክርስትና ሀይማኖት ተካታዮችም ጭምር ይተገበራል።

ጌታቸው መኮንን (1986፣17-18) ወሎ እንደ መርካቶ የተለያየ እምነትና ብሄር ያላቸው ሰዎች ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚኖርበት አገር እንደሆነ፤ በወሎ በሚከበሩ ሀይማኖታዊ በአላት እና ድግሶች ሙስሊም ክርስቲያን ሳይባባሉ በአንድነት እንደሚሳተፉ፤ "ጠበል ቅመሱ" የሚሉ ለክርስትያኑ ጠላ፣ ለሙስሊሙ ቡቅሪ ማዘጋጀት የተለመደ መሆኑን ጽፈዋል። ይህንን የመቻቻል ባህል ፊታውራሪ አመዴ ለማ እንደሚከተለው አስፍረውታል።

> በወሎ በአመት በአል ጊዜ የእስላም በአል እና የክርስትያን በአል የሚባል ልዩነት የለም። በጥምቀት እና በገና የእስልምና ሀይማኖት አማኙ ወጥቶ ይጨፍራል። ለአረፋ እና ለኢድም ክርስትያኑ እንደዚያ ያደርጋል። ስለዚህ በአስተሪዮ ማሪያም በጥምቀት እና በጊዮርጊስ ንግስ ወጣቱና ጎልማሳው ሁሉ ፈረስ ይጋልባል። ቡሄ በክርስትና ሀይማኖት የሚያምኑ ሰዎች ባህል ተደርጎ ይታያል። በእኛ አገር ግን ቡሄ ሲደርስ የእስላሙም ሆኑ የክርስትያን ልጆች ሁሉም የጅራፍ ግርፊያ ይጫወታሉ (2003፣14-17) ።

ከምእመኑ በተጨማሪ የሀይማኖቱ መሪዎች በዚህ የመቻቻል ባህል ውስጥ ይሳተፋሉ። ቦጋለ ተፈሪ የወሎው ሼህ ሁሴን ጅብሪል የቅርብ የሩቁን ሲናገሩ እና ችግር ሲፈቱ ውለው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከብት ገብቶ ስለነበር ከመሸ በኋላ "እንዴት ወንዝ አቋርጠው ይሄዳሉ" በማለት ከድባበ ማሪያም ቤተክርስትያን ቅጥር ግቢ "ይደሩ" ተብሎ ቁጠማ ተጎዝጉዞላቸው፣ ስኒ ተደርድሮላቸው አድረው (2002፣133) እንደነበር ጽፈዋል።

ሁሴን አህመድ (1992፣146) "ወሎ ውስጥ የሚገኙ ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች የጋራ የሆነ ቋንቋ፣ ዘር እና የፖለቲካ ስርአት ባለቤት ከመሆናቸውም በላይ ኑሯቸውም በጉርብትና" እንደሆነ አስፍረዋል።[33] የወሎ ህዝብ የሐይማኖት መቻቻሉን ከሚገልጽባቸው መንገዶች ውስጥ "ሙስሊሙ መስጊድ ማሰራት ሲፈልግ፣ ክርስትያኑ ቤተክርስትያን ማሰራት ሲፈልግ በሁለቱም በኩል የገንዘብ፣ የጉልበት እና የሀሳብ ድጋፍ መስጠታቸው ነው" (አመዴ ለማ፣2003፣29-30)። ይህን መሰል ታሪካዊ መነሻ ያለው የሀይማኖቶች ሰላማዊ መወራረስ አገራችንን/ወሎን በተለያዩ ሀይማኖቶች መካከል ባለው የመቻቻል ባህል እንዲታወቅ አስችሎታል።

---

[33] Muslims and Christians have shared for centuries many aspects of the overall Ethiopian culture, such as belonging to a common ethnic linguistics group and to the same political system. In most areas they have lived side by side in the same localities.

በወሎ ጥንታዊ እና ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያናት የመኖራቸውን ያህል ጥንታዊ የሆኑ የእስልምና መጻህፍትና ታሪካዊ መስጊዶች ይገኛሉ። ለዘመናት ተጠብቆ የቆየው ግንኙነት በህዝቡ ላይ የጠበቀ ትስስር እና ተጽእኖ አሳድሯል። ብርሀኑ ገበየሁ[34] (1998) በወሎ የርስ በርስ ጋብቻ ምን እንደሚመስል ሲገልጹ "በወሎ ሙስሊሙ እና ክርስቲያኑ ፍጹም በሆነ መቻቻልና ሰላም የሚኖረው በጉርብትና ብቻ ሳይሆን በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ግማሽ ሙስሊም ግማሽ ክርስቲያን በመሆን ነው" (1998፣4) ይላሉ።[35] ፍጹም የሆነ መቻቻል የሚለውን የብርሀኑ ሀሳብ በግርድፉ ስንመለከተው ፍጹም የሚባል መቻቻል አለ? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ቢሆንም የመቻቻሉን መጠን እና ልክ ከፍታ ለማመላከት የተጠቀመበት ነው ማለት ይቻላል። ከሌሎቹ የአገራችን ክፍሎች በተለየ ሙስሊም ክርስቲያኑን፣ ክርስቲያኑ ሙስሊሙን ሀይማኖቱን ቀይሮም ሆነ ሳይቀይር የሚገባበት ባህል በወሎ የተለመደ ነው።

የግንኙነቱ ተጽእኖ የእስልምና ሀይማኖት ብቻ የሚመስሉን ተግባሮች በክርስትና ሀይማኖት ውስጥ እንዲኖሩ አስችሏል። ጀን አቤንክ የቅዱሳን እና የሼሆችን ህልፈት ተከትሎ ወደ መካነ መቃብራቸው የሚደረግ "ሀይማኖታዊ" ጉዞ በስፋት የተጀመረው በሙስሊሞች (በተለይ ለወሎው ሼህ ሁሴን ጅብሪል በሚደረግ ጉዞ) ሲሆን ከጊዜ በኋላ ግን ይህንን ስርአት የክርስትና እምነት ተከታዮችም መተግበር እንደጀመሩ (1998፣120) ያስረዳል። ከእስልምና ሀይማኖት ጋር በተያያዘ የሳምንቱ ቀናት የተለያዩ መጠሪያዎች አሉት። እነዚህም ሰኞ (ሰይድ)፣ ማክሰኞ (ጉራሁሴን)፣ እሮብ (አብዱዩ)፣ ሀሙስ (ከሚስ)፣ አርብ (ጁምአ)፣ ቅዳሜ (ከድር)...የሚሉ ናቸው። በእያንዳንዳቸው እለት ጫት መቃም፣ ቡና ማፍላት እና ዱአ ማድረግ በአብዛኛው በሙስሊሙ ማህበረሰብ የሚከናወኑ ናቸው። በወሎ ግን ከሙስሊሙ ባልተናነሰ ክርስቲያኖችም እለቱን እያስታወሱ ጫት ይቅማሉ፣ ቡና ያፈላሉ፣ በወሎ አድባር ይለማመናሉ።

በተመሳሳይ መልኩ የክርስትና ሀይማኖት ብቻ የሚመስሉን በእስልምና ሀይማኖትም ይተገበራሉ። ለአብነት በኦርቶዶክስ ክርስትና የደብረ ታቦርን በአል መሰረት አድርጎ የቡሄ በአል ሙልሙል ዳቦዎች እየተጋገሩ እና የቡሄ ጭፈራዎች እየተጨፈሩ ይከበራል። በወሎ ይህ በአል በሙስሊሙም በክርስቲያኑም በጅራፍ ታጅቦ እኩል የሚከበር በአል ነው።

---

[34] Islamic oral poetry in wallo a preliminary descriptive analysis በሚል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ በሰራው ጽሁፍ

[35] Not only do Christians and Muslim live next each other in perfect harmony and absolute peace even with in the same family half may be Christian and half Muslim.

ረጂም ጊዜን ያስቆጠረው የርስ በርስ ግንኙነቱ በህዝቡ ብቻ ሳይገታ በሁለቱም ሀይማኖታዊ ተቋማት ላይ አሻራውን አሳርፎ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም በምሳሌነት የሚጠቀሰው የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ጡሪሲና የሙስሊም "ገዳም" ወሎ ውስጥ መገኘቱን ለረበረ ይሏል፡፡

# ምእራፍ አራት

## 4. የጡሩሲና "ገዳም" ክብረ በአላት ስርአተ ክዋኔ

"በገዳሙ" የሚከናወኑ በርካታ ክብረ በአላት አሉ። ክብረ በአላቱ "በገዳማውያኑ" እና በአካባቢው ማህበረሰብ የሚከናወኑ ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ "በገዳማውያኑ" ብቻ የሚከበሩ ናቸው። ጥናቱ "በገዳማውያኑ" እና በሙስሊሙ ማህበረሰብ ከሚከናወኑ በአላት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠውን የመውሊድ ክብረ በአልን እና "በገዳማውያኑ" ከሚከናወኑ በአላት የቁርአን ኩትሚያን/ስርግ ብቻ ነጥሎ በመውሰድ ትንተና አካሂዷል።

### 4.1. የመውሊድ አከባበር

በእስልምና እምነት ተከታዮች የመውሊድ በአል ነቢዩ መሀመድ የተወለዱበትን ቀን ምክንያት በማድረግ በአመት አንድ ጊዜ ይከበራል። "በገዳሙ" በአሉ በአለም አቀፍ ደረጃ የነቢዩ መሀመድ የልደት በአል ከሚከበርበት ሶስት ቀን ቀደም ብሎ ይከበራል። ይህ የሆነበትን ምክንያት አቶ መሀመድ እማን[38]፥

> በአካባቢያችን የመውሊድ በአል ብዙ ቦታ ይከበራል። የጡሩሲና መስጊድ እና ገታ በአሉ በስፋት የሚከበርባቸው ቦታዎች ናቸው። የአካባቢው ሰውም በአሉን በተለያየ ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ ማክበር ስለማይችል የጡሩሲናውን ሶስት ቀን አስቀድመን፣ የገታውን የበአሉ ቀን በስምምነት ለማክበር ስላሰብን አስቀድመነዋል (ቃ.መ፣ ህዳር21፣ 2005፣ ሽነካ) በማለት ይገልጻሉ።

የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከናወኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ለማሳየት ሂደቱ የበአል ዋዜማ ዝግጅት፣ እውደ በአል እና የበአል ማግስት ዝግጅት በሚል ለሶስት ተከፋፍሎ ቀርቧል።

#### 4.1.1. የመውሊድ ዋዜማ ዝግጅት

የመውሊድ ክብረ በአልን ለማክበር ሰዎች ከአዲስአበባ፣ ከጎንደር፣ ከሀረር፣ ከደሴ፣ ከኮምቦልቻ ወደ "ገዳሙ" ይገባሉ። "ለገዳሙ" ከራቀ ስፍራ የሚመጡ ታዳሚያን ከበአሉ አንድ ሳምንት

[38] በቁጥር 7 የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

ቀደም ብለው ዝግጅታቸውን ይጀምራሉ። የጉዞ ስንቅ፣ የመጓጓዣ ገንዘብ፣ ልብስ፣ ጫማ እና ለገዳሙ የሚሰጡትን ነገር አዘጋጅተው ይጨርሳሉ። በተጨማሪም የተጣሏቸው ሰዎች ካሉ "ወደ ጥሩው ቦታ ወደ ጡሩሲና ልሄድ ነው አውፍ በሉኝ" (ይቅር በሉኝ) በማለት እርቅ ያወርዳሉ (ቃ.መ፣ አንሻ ሟሂር፣ ጥር25፣ ጡሩሲና)።

በአሉ በአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። በእድሜ በጣም የገፉ፣ መንቀሳቀስ የማይችሉ፣ በሽተኛ እና ህጻናት ካልሆኑ በበአሉ ቅድመ ዝግጅት እና በበአሉ ውስጥ ሁሉም ይሳተፋሉ። ቅድመ ዝግጅቱ የሚጀመረው ከበአሉ ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ ይጀመራል። የስራ ድርሻውም በእድሜ እና በጾታ የተከፋፈለ ነው። ወጣት ሴቶች እና ወንዶች ለበአሉ የሚሆን የማገዶ እንጨት፣ የሚጎዘጎዝ ሳር እና ቄጠማ ወደ "ገዳሙ" ያደርሳሉ፣ "ከገዳማውያኑ" ጋር በመሆን "ገዳሙን" ያጸዳሉ።

የአካባቢው አባወራዎች ከበአሉ አስራ አምስት ቀን ቀደም ብለው የማር ብር ያዋጣሉ፤ ለበአሉ የሚሆኑ ከብቶችን ያዘጋጃሉ፣ ለሚስቶቻቸው ገንዘብ ይሰጣሉ። በአሉ እየተቃረበ ሲመጣ ሴቶቹ እህል ሸምተ በማስፈጨት፣ በርበሬና ሽሮ በማዘጋጀት ስራ ይጠመዳሉ። በአሉ ሲደርስ አራት ቀን ሲቀረው "የጡሩሲና "ገዳም" የእህል ቡኮ አለ" በማለት ሁሉም ሰው ተጋግዞ ያቦካል። በበአሉ ዋዜማ እንጀራውን በህብረት ይጋግሩና ወደ "ገዳሙ" ይወስዳሉ (ቃ.መ፣መሀመድ አማን፣ህዳር 21፣2005፣ ሼክላ)።

ወንድ "ገዳማውያን" የማር ብርዝ በማዘጋጀት፣ ለበአሉ የሚሆኑ እቃዎችን በማጽዳት፣ የእንግዶችን ማረፊያ በማስተካከል፣ ውሀ በመቅዳት፣ ከበአሉ ቀደም ብለው ከሩቅ አገር የመጡ እንግዶችን በመቀበል፣ በማስተናገድ እና በበአሉ ቀን የሚሰጣቸውን ሀላፊነት በመከፋፈል እና ከወዲሁ በመሰናዳት የበአሉን መምጣት ይጠባበቃሉ።

በአንጻሩ ሴት "ገዳማውያን" በአሉን እንዲያከብሩም ሆነ ከውጭ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ ስለማይፈቀድላቸው በቅድመ ዝግጅቱ ያላቸው ተሳትፎ ምንም ነው። በአሉ ሁሉንም ሙስሊሞች የሚመለከት ሆኖ ሴት "ገዳማውያን" እንዲያከብሩ የማይፈቀድበትን ምክንያት ወ/ሮ የሺ ፋጢማ[37] ሲገልጹ "የውጭ ሰዎችን ሲያዩ ልባቸው ይሸፍታል፣ "ገዳሙን" ለመልቀቅ

[37] በቁጥር 10 የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

ይወሳወሳሉ እናም ትተው ይሄዳሉ በሚል ፍራቻ ነው" በማለት ይናገራሉ (ቃ.መ፣ ጥር26፣ 2004፣ ጡሩሲና)። የሴቶቹን አለማክበር ምክንያት ወንዶቹ ሲገልጹ "ወንዶቹ በአሉን ለማክበር ወደ "ገዳሙ" ሲመጡ የሚያወሩት ስለ ሀይማኖታቸው ብቻ ነው። ሴቶቹ ስለ ብዙ ነገር ያወራሉ ከእነሱ ጋር ከተቀላቀሉ ነገር እና ወሬ ይለምዳሉ" በሚል ፍራቻ ነው በማለት ሼህ ጀማል እንድሪስ[38] (ቃመ፣የካቲት 01፣ 2004፣ጡሩሲና) ያስረዳሉ።

ከበአሉ መምጣት ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ የተደረገው ቅድመ ዝግጅት የሚጠናቀቀው በበአሉ ዋዜማ ነው። በዋዜማው ከሩቅ ቦታ የመጡ ሰዎች ማረፊያ ቦታ ይሰጣቸዋል። "ለገዳሙ" የተሰጡ በግ፣ ግመል፣ ፍየሎች እና የተጋገረው እንጀራ በሙሉ ወደ "ገዳሙ" ይወሰዳል።

### 4.1.2. አውደ በአል

የበአሉ ክዋኔ ጠዋት[39]፣ ከሰአት[40] እና ምሽት[41] የሚካሄዱ ስርአቶች በሚል ለሶስት የተከፋፈለ ነው። በወንዶቹ እና በሴቶቹ ያለውን የበአል አከባበር ለማሳየት የወንዶች እና የሴቶች በሚል ለየብቻ ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 4.1.2.1. የበአሉ አከባበር በወንዶች "ገዳም"

##### 4.1.2.1.1 ጠዋት የሚካሄዱ ስርአቶች

የበአሉ ምግቦች እና መጠጦች በአብዛኛው በወንዶቹ የሚዘጋጁ በመሆኑ የስራ ጫናው በእነሱ ላይ ይበረታል። ሁሉም ደረሳዎች ወደ ስራቸው ይሰማራሉ። የስራ ክፍፍላቸው የሚከተለውን ይመስላል። ሼህ አብዱል ከሪም "በገዳሙ" ውስጥ የውጭ እንግዳን የሚቀበሉ በመሆናቸው በአሉን ለማክበር ጠዋት ወደ "ገዳሙ" የሚመጡ አማኞችን ቦታ ቦታቸውን ያስይዛሉ። እላቸውን ለማገዝ የሚመደቡ ሌሎች ደረሳዎች አሉ።

---

[38]ጀማል እንድሪስ እድሜአቸው 67 ሲሆን "በገዳሙ" ውስጥ በደረሳነት ይኖራሉ። "በገዳሙ" ውስጥ በደናግልነት ረጂም ጊዜን ካሳለፉ ደረሳዎች መካከል የሚጠቀሱ እና በአሁኑ ወቅት የሼሁ አማካሪ በመሆን እያገለገሉ የሚገኙ ናቸው።
[39]የሱብሂ (ሌሊት 11) ሰአት ሰላት ከተሰገደ በኋላ እስከ ዝሁር(ቀን 7) ሰአት ሰላት ድረስ ያለውን ጊዜ
[40] የዝሁር ሶላት ከተሰገደ በኋላ እስከ መቅሪብ (ምሽት 1 ሰአት) ድረስ ያለውን ጊዜ
[41] የኢሻ ሶላት (ምሽት 2 ሰአት) ከተሰገደ በኋላ ያለውን ጊዜ

1. ሼህ አብዱል ከሪም፦ የውጭ እንግዳን ይቀበላሉ፡፡ በአሉን ለማክበር ጠዋት ወደ "ገዳሙ" የሚመጡ እማኞችን በቦታ በቦታቸውን ያስይዛሉ፡፡ እሳቸውን ለማገዝ የሚመደቡ ሌሎች ደረሳዎች አሉ።
2. ሼህ አወል ኢብራሂም፦ "በገዳሙ" ውስጥ የቡና አዛዥ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በመሆኑም ጠዋት ላይ ቡና የሚያጥቡ፣ የሚቆሉ፣ የሚወቅጡ፣ የሚቀዱ ሌሎች ደረሳዎችን በስራቸው በማስማራት ለበአሉ የሚሆነውን ቡና በአዛዥነት ይቆጣጠራሉ፡፡
3. ሼህ የሱፍ አረብ፦ ለበአሉ የሚቀርበውን የማር ጠጅ በሀላፊነት ይቆጣጠራሉ፡፡ ጠዋት ላይ ሌሎች ደረሳዎችን በመያዝ ማር ይበጠብጣሉ፣ የማር እቃዎችን ያዘጋጃሉ፡፡
4. ሼህ አህመድ አሊይ፦ የስጋ ቤት ዋና ሀላፊ ሲሆኑ ከአካባቢው ማህበረሰብ የመጡ የእርድ ከብቶችን ጠዋት እያሳረዱ ለወጥ ቤት ሰራተኞች ያቀብላሉ፡፡ "በገዳሙ" ላደሩ ሰዎች ቁርስ ለማድረስ ወጥ ቤት የተመደቡት ወንዶች ስራቸውን በፍጥነት ያከናውናሉ።

ለበአሉ ቀን ቢያንስ አስር የወጥ በርሚል የሚጣድ ሲሆን እነዚህ በርሚሎች በአጠቃላይ አምስት በሬ የሚይዙ ናቸው። የአሰራሩም ሁኔታ በአምስቱ በርሚሎች ስጋው ከአጥንቱ እየተለየ ይጣድ እና ይበስላል። የበሰለውን ስጋ በቆሪ ለይቶ በማስቀመጥ መረቁ ላይ በርበሬ እና ጨው ይጨመርበታል። ከፈላ በኋላ ሁለት ወንዶች በግራ እና በቀኝ በመሆን የተቆራረሰውን እንጀራ በማስገባት ይፈተፈታል። በመጨረሻም የተከተፈውን ስጋ በእጅ በማንሳት በሚቀርብበት ሳህን ላይ ከአምስት እስከ አስር የሚደርሱ ፍሬዎች ይጨመርበታል፡፡

ምግቡ ሲደርስ ለእማኙ እንጀራ ፍትፍት እና ቡና ይቀርባል፡፡ ምግቡ የሚቀርበው በነጫጭ ኒኬል ሳህኖች ሲሆን አንድ ሰሀን ምግብ ለ2 እና ለ3 ሰዎች ብቻ ይቀርባል፡፡ ከምግብ በኋላ ቡና ለሁሉም ሰው ይዳረሳል። ከተበላና ከተጠጣ በኋላ ደረሳዎቹ እቃ በማንሳት ማጽዳት የቡናና የወጥ ቤት ሰራተኞቹ ደግሞ ለምሳ የሚሆን ምግብ ወደ ማዘጋጀት ይገባሉ፡፡ በእንጻሩ በአሉን ለማክበር የመጡ ሰዎች ጫት ይቅማሉ ።

### 4.1.2.1.2. ከሰአት የሚካሄዱ ስነ ስርአቶች

ከቁርስ በኋላ ተጀምሮ የነበረው ጫት የመቃም ስርአት የዝሁር ሶላት ሲቃረብ ይቆማል። ከቀኑ ስድስት ሰአት በኋላ ጫቱን እየተዉ ኡዱ ለማድረግ እና ለመናፈስ ይወጣሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ "ገዳሙ" የመጡ ሰዎች ካሉ አካባቢውን ይጎበኛሉ። ለዝሁር ሶላት አዛን ሲደረግ ሁሉም ወደ "ገዳሙ" በመግባት ይሰግዳሉ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ምሳ ለሁሉም ይቀርብላቸዋል። ምግብ ከተበላ እና ቡና ከተጠጣ በኋላ ጫት መቃም ይጀምራሉ። ጫት በሚቃምበት ጊዜ ከፍ ባለ ድምጽ ማውራት አይፈቀድም። በድምጻቸው ጥሩነት የተመረጡ ሁለት ደረሳዎች ብዙውን ጊዜ ሼህ አወሌ እና ሼህ አህመድ ሀሰን ይመረጣሉ።

ድቤ እየተመታላቸው ያንጎራጉራሉ እንጂ በቴፕ የሚከፈት መንዙማ አይደመጥም። በመካከል ከሀይማኖቱ ጋር የተያያዙ በተለይ የጡሩሲናውን ሼህ መሀመድ አማን[42] ሰብእና ከፍ የሚያደርጉ ታሪኮች ይወራሉ። አቶ አህመድ መሀመድ ከትረካዎቹ መካከል የሚከተሉትን ይናገራሉ (ቃ.መ፣ ጥር 27፣ ሼክላ)። ሼሁን እርሳቸው መጀን እና የሚታያቸው ነገር አለ። ድንገት የሆነ ነገር እንዲመጣ ያደርጋሉ በማለት ንግግራቸውን ይጀምራሉ።

> አንድ ቀን ደረሳዎቹን በመጥራት "ዛሬውኑ የሚታረዱ 7 ግመሎችን አምጡ" አሏቸው። ደረሳዎቹ ግራ በመጋባት ሲመለከቷቸው "አምጡ ብያለሁ አምጡ" በማለት ተናገሩ። ደረሳዎቹ ባላቸውን ብር ሲያሰባስቡ ሶስት ግመሎችን ብቻ ገዙ። በአካባቢው የሚኖር አንድ ገበሬ አንድ ግመል ይዞ ወደ መስጊዱ ሲመጣ አዩ እና ተጨማሪ ሶስት ግመሎች ከዬት እንደሚያመጧቸው ተጨነቁ። ሼሁም "ግደላችሁም ትንሽ ሶብሩ አንድ የአላህ ሰው ይዟቸው እየመጣ ነው" በማለት ተናገሩ። ይህንን ከተናገሩ ከአንድ ሰአት በኋላ አንድ የሩቅ አገር ሰው ለሼሆቹ የነየታቸውን (ሊሰጥ ያሰበውን) ሶስት ግመሎች አስከትሎ መጣ። ሼሆቹ እንዳሉትም በዛን ቀን ሰባት ግመሎች ታረዱ።

[42] በቁጥር 13 የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

ይህን የሚሰሙ ወንዶች "አጀባ ሆኖ እስኪ እርሳቸው መጀን ዘይረኝ" ይባባላሉ። ከመካከላቸው አንዱ ተነስቶ ሊመርቅም ይችላል። ሴቶቹ ይህንን መሰል ታሪክ ሲሰሙ በጣም ያለቅሳሉ። ከምርቃቱ በኋላ ሌሎችም እንዲህ በማለት የሼኩን ታሪክ ይተርካሉ።

> መንግስት አፍርሶ የመገንባት እና የመንገድ ስራ ከመጀመሩ በፊት ሼሁ መንግስት እንዲህ አይነት ስራ ስለሚጀምር ሳይቀድመን መጀመር አለብን በማለት እንዲህ ያደርጉ ነበር። በመስጊዱ ውስጥ ደስ ያላቸው ከለዋ ይሄዱና ውስጥ ያሉትን ደረሳ ያስጠራሉ። "ከለዋህ መንገድ ቦታ ላይ ስለተሰራች ካሳ ይሰጥሀል አፍርስ" በማለት እስከ መቼ ማፍረስ እንዳለበት ተናግረው ይሄዳሉ። ባሉበት ቀን ለቤት መስሪያ የሚሆን ተለዋጭ ቦታ እና ብር ይዘው ለደረሳው በመስጠት ቦታውን መንገድ ያስሩበታል፣ ያረጁ ከለዋዎችንም ወይ እንዲያድሱ አሊያም እንዲያፈርሱ ያስደርጉ ነበር። ይህ ድርጊታቸው በኋላ ላይ መንግስት ካደረገው ነገር ጋር ተገጣጠመ። እንገዲህ የአሳህን ስራ ተመልከቱ።

ይህንን እና መሰል ታሪኮችን እየሰሙ፣ እየተመራረቁ እና እየተዘያየሩ እስከ አስር ሰአት ይቆያሉ። ሁሉም ነገር ባለበት ቆሞ የአሱር ሶላት ይሰገድና ስርአቱ ይቀጥላል። ሌላኛው ተረክ በ1991 ዓ.ም የኢትዮጵያ እና ኤርትራ ጦርነት ጊዜ የተፈጸመ ታሪክ ላይ ያጠነጥናል።

> ኤርትራ አገራችንን የመውረሯ ዜና ከመሰማቱ ጥቂት ሳምንታት በፊት ሼሁ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎችን ሰበሰቡ። ሁሉም ሰው መገኘቱን ካረጋገጡ በኋላ "እኔ በደረሶቼ አማካይነት መልእክት ልኬ ሳስጠራችሁ መሳሪያ ካላችሁ ይዛችሁ ኑ ሌሎቻችሁ ደግሞ ሬዲዮ ይዛችሁ ኑ" በማለት አስናበቷቸው። ጦርነቱ ከታወጀበት እለት አንድ ቀን አስቀድመው ሰዎቹን "ነገ ወደ ጡሩሲና እንድትመጡ ሼሆቹ አዘዋል" ብለው ደረሶቻቸውን ላኩ። በማግስቱ መሳሪያ የያዙ ሰዎችን ለይተው ትንሽ ካስጠበቁ በኋላ "አሁን ተኩሱ" በማለት ካስተኮሱ በኋላ "አሁን ደግሞ ሬዲዮ ክፈቱ እንዲት አገር አገራችንን ወራለች" አሉ ሬዲዮው ሲከፈት ዜናው ተሰማ። ከዚህ በኋላ እስከ ጦርነቱ ፍጻሜ ሰዎችን እያስመጡ ያስተኩሱ ነበር። በመጨረሻ በሁለቱ አገር እርቅ ከመውረዱ አንድ ቀን አስቀድሞ "ነገ ጦርነቱ ስለሚቆም ከዚህ በኋላ ተኩስ የለም" በማለት ተናገሩ። እንዳሉትም በማግስቱ ጦርነቱ ቆመ።

ጫት፣ ሰንደል እና ስኳር አንዱ ጋር ካለቀ ከሌሎቹ ይወስዳሉ። ከመግሪብ እስከ ኢሻ ያለው ጊዜ የአካባቢው ሰዎች ወደ ቤታቸው ለመሄድ የሚዘጋጁበት፣ "በገዳሙ" የሚያድሩትም ለመናፈስና ሰውነታቸውን ለማፍታታት ወደ ውጭ የሚወጡበት እና ለኢሻ ሰላት ኡዱእ የሚያደርጉበት በአጠቃላይ ለአዳር ቂምህ ለመዘጋጀት እንደ መሸጋገሪያ የሚጠቀሙበት ነው። ከኢሻ ሶላት በኋላ ማደሪያ ቦታ እጥረት ስላለ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ወንዶች ለእንግዶቹ ቦታ በመልቀቅ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ።

### 4.1.2.1.3. ምሽት የሚካሄዱ ስነ ስርአቶች

ከሶላት በኋላ ምግብ ለሁሉም ይቀርባል። በዚህ ጊዜ ሙሉ ቀን ሲቅሙ በመዋላቸው የመብላት ፍላጎት ባይኖራቸውም "አልበላም" አይባልም። ምክንያቱም አቶ መሀመድ አማን[43] "የጡሩሲናን ምግብ በልተን የሞትን እንደሆን የፍርድ ቀን ስንነሳ ወደ ጥሩው ቦታ ጡሩሲና መጥተው ነበር ብሎ ምግቡ ራሱ ምስክርነት ይሰጣል" በማለት ሲያስረዱ ወ/ሮ የሺ ፋጢማ[44] ደግሞ "ምግቡ መድሀኒት ነው፣ ብዙ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ምግቡን ብቻ በመብላት ድነዋል፣ የሺሁንም በረካ የሚደርሰን በምግቡ አማካኝነት ነው" በማለት ምግብ አልበላም የማይባልበትን ምክንያት ይገልጻሉ (ቃ.መ፣ ጥር26-27፣ 2004፣ ሼክላ እና ጡሩሲና)። በዚህም የተነሳ ቢጠግቡም ሳይቀምሱ ቢቃኝ ብለው አይነሱም።

ምግብ ከተበላ እና ቡና ከተጠጣ በኋላ ወደ ዋናው ቂምህ የሚገባ ሲሆን በአብዛኛው ወሬ የሚያወራ ሰው አይስተዋልም። በዚህ ሰአት አብዛኛው ሰው በጫቱ የሚመረቅንበት ሰአት በመሆኑ ሁሉም የራሱን ሀሳብ የራሱን ስሜት የሚያደምጥበት ችግሩን እና ብሶቱን ከአምላኩ ጋር የሚያወራበት ነው። ከምሽት እስከ ንጋት ባለው ጊዜ ድቤ እየተመታ የአላህን ደግነት፣ ታጋሽነት፣ ታላቅነት በማንሳት እና በማወደስ ምስጋና ይቀርብበታል (ቃ.መ፣ የካቲት02፣ 2004፣ ሁሚድ አድሪስ፣ ሼክላ)።[45]

---

[43] በቁጥር 7 የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻን ይመልከቱ።
[44] በቁጥር 10 የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻን ይመልከቱ።
[45] ሁሚድ አድሪስ ነዋሪነታቸው በሼክላ ሲሆን ባለትዳር እና የአራት ልጆች አባት ናቸው። እድሜአቸው 40 ገደማ ሲሆን መተዳደሪያቸው ግብርና ነው። ከአካባቢው ሰዎች "ለገዳሙ" ቅርበት አላቸው የሚባሉ ናቸው።

## 4.1.2.2. በሴቶች "ገዳም" የመውሊድ አከባበር

### 4.1.2.2.1 ጠዋት የሚካሄዱ ስርአቶች

በሴቶች "ገዳም" የመውሊድን በአል ያለ ስራ ጫና ተረጋግተው እና አርፈው እንዲያከብሩ "የገዳሙ" ህግ ይፈቅድላቸዋል። ከበአሉ አንድ ቀን ቀደም ብለው ለኡዱ ማድረጊያ እንዳይቸገሩ ውሀ ይቀዳሉ። ሶላት ከተሰገደ በኋላ ብዙዎቹ ይተኛሉ። የማይተኙትም ዱአ ያደርጋሉ። ሶስት ሰአት አካባቢ በዱበርቲዎቹ አማካይነት ቁርስ ስለሚቀርብ ወደ ዋናው "ገዳም" እንዲሄዱ ይነገራል። የመመገቢያ ንጫጭ ኒኬል ሳህኖች ከወንዶቹ ወደ ሴቶች "ገዳም" ይመጣል። ምግብ የሚቀባበሉበት ቤት በሰንበሌጥ የተሰራ ሲሆን ምግቡን የሚቀባበሉት በአካባቢው የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ብቻ ናቸው።

ቁርስ ከተበላ እና እቃ ከተነሳ በኋላ ቡና ይቀርባል። ቡናው ከመቀዳቱ በፊት በኦሮምኛ ቋንቋ ምርቃት ይቀርባል። የምርቃቱ መልእክት "ሼሆቻችንን ከክፉ ነገር ይጠብቅልን፣ ረጅም እድሜ ያኑርልን፣ እኛንም እድሜአችንን ያርዝመው፣ ጤናችንን ይስጠን፣ ልጆቻችንን፣ ከብቶቻችንን እና ከሰባችንን (እህላችንን) ከክፉ ነገር ይጠብቅልን፣ አገራችንን ሰላም ያድርግልን፣ በዱንያም በአኼራም የምንጠያየቅ ሰው ያድርገን፣ አመት ከአመት ሳይለያየን ያገናኘን" የሚል ነው። ምግቡ ተበልቶ ቡና ተጠጥቶ ሲያበቃ በታዳሚዎቹ አማካይነት እቃዎቹ ይተጣጠባሉ። እስከ ዝሁር ሶላት ባለው ጊዜ ውሀ በመቅዳት እና አዲስ የሚመጡ ሰዎችን በመቀበል ያሳልፋሉ።

### 4.1.2.2.2. ከሰአት የሚካሄዱ ስርአቶች

የዝሁር ሶላት ከተሰገደ ምግብ ይበላና ቡና ይቀርባል። በርካታ ሰው ስለሚታደም ቡናው የሚቀርብበት ጀበና ከሙቶ ሀምሳ ስኒ በላይ የሚይዝ ነው። አጠቃላይ ስርአቱን የሚመሩት ሴት ፋጢማ ናቸው። በአሉን ለማክበር የሚመጡ ሰዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ምክንያት ያላቸው ናቸው። አንድም እንዲሞላላቸው የሚፈልጉት ነገር እንዲሟላላቸው ለመንገር አንድም የሞላላቸውን ጉዳይ ለፋጢማ[10] ተናግረው ለማመስገን ስኳር፣ ቡና፣ ሰንደል፣ ጫት፣ ተምር፣ ማጨሻ፣ ምንጣፍ፣ መጋረጃ... ይሰጣሉ። እዚህ ቦታ ላይ የሚመጡ ሰዎች በአብዛኛው በህይወታቸው አንዳች የሆነ እክል ያጋጠማቸው ናቸው። ከእነዚህ እክሎች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

---

[10] በቁጥር 11 የሰፈረውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

> አንሻ ከማል ይባላሉ። ከብዙ አመት በፊት ትዳር ይዘው ወልደው አይናቸውን በአይናቸው ለማየት ታድለዋል። ቢሆንም አንድ ያልተሟላላቸው ሀጃ (ጉዳይ) አለ። ወልደው ለመሳም ይቻሉ እንጂ የልጅ ልጅ ለማየት አልታደሉም። ምክንያቱ ደግሞ ልጃቸው ትዳር ሳትይዝ 29 አመት መሆኑ ነው። እሳቸው እንዳሉት "ልጆሽን ለልጄ" የሚል ሰው ከደጃቸው ጠፍቶ አያውቅም። የሽማግሌዎቹን ጥያቄ በደስታ ተቀብለው ከሸኙ በኋላ የሚመጡት ሽማግሌዎች "የውሀ ሽታ" እየሆኑ ይቀራሉ። በአካባቢያቸው ሴት ልጅ የምትዳረው ከ15 አመቷ ጀምሮ ነው። የልጃቸው ትዳር አለመያዝ አሳፍሯቸው ብዙ ጠንቋይ ቤቶች እየሄዱ መድሀኒት ቢሰጧቸውም እስካሁን አላገባችም። የቅርብ የሚባሉ ዘመዶቻቸው ወደ ጡሩሲና እንዲሄዱ ስለነገሯቸው ልጃቸውን ይዘው መጥተዋል። (ቃ.መ፣ጥር 27፣2004፣ጡሩሲና)

ሌሉች ታዳሚዎች ይህንን ታሪክ ሰምተው ዝም አይሉም። ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው ሰዎች ወደ "ገዳሙ" መጥተው መፍትሄ እንዳገኙ በመግለጽ የሚያውቋቸውን ታሪኮች ይተርካሉ።

> ሰአዳ ዑመር ይባላሉ። ነዋሪነታቸው "ከገዳሙ" 16 ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኘው ከሚሴ ከተማ ላይ ነው። እዚህ ቦታ የተገኙት ስለሞላላቸው ነው። ከዚህ ቀደም መጥተው ችግራቸውን ተናግረው ሄደው ዛሬ ላይ ለምስጋና እና የገየቱትን/የፈቀዱትን ሊሰጡ ታድመዋል። ከአምስት አመት በፊት 36 ግራም ወርቅ ከቤታቸው ጠፋ። በጊዜው የነበረቻቸውን ሰራተኛ በጥያቄ ቢያፋጥጧትም፣ በፖሊስ ቢያስደበድቧትም ወርቃቸውን ማግኘት አልቻሉም። ከአራት አመት በኋላ (ባለፈ አመት እዚህ ቦታ ተገኝተው ይህንን ችግራቸውን ሲናገሩ ወርቃቸውን ማግኘት ባይችሉ እንኳ የወሰደውን ሰው እንዲያሳውቃቸው ለምነው ነበር) በመጨረሻም የቅርብ የሚሏት ጓደኛቸው ቤት ተገኝቶላቸው ለማመስገን መጥተዋል። (ቃ.መ፣ ጥር25፣ 2004፣ ጡሩሲና)

ወደ "ገዳሙ" የሚመጡ አብዛኞቹ ሰዎች ወደ ቦታው ቢሄዱ የተሻለ መፍትሄ እንደሚያገኙ ሰምተው እንደመጡ ይናገራሉ። ከሌሎቹ በተለየ አሚናት ሀሰን[47] የተባሉት የበአሉ ታዳሚ ስለ "ገዳሙ" ህልም አይተው ለመጀመሪያ ጊዜ መምጣታቸውን (ቃ፣መ፣ ጥር27፣ 2004፣ ጡሩሲና) ይገልጻሉ።

"ተኝቼ ይመስለኛል ነጭ ሀር ልብስ የለበሰ ሰው ‹አንቺ አሚናት አሚናት› እያለ ይጠራኛል። እደነግጥና "አቤት" ብዩ እነሳለሁ።

"ልጅ ፍለጋ ብዙ ቦታዎች ስትንከራተቺ ሁሌም ነው የማይሽ (ጠንቋይ ጋር ትሄድ ነበር ) እውነቴን ነው?"

"አዎ እውነትዎን ነው"

"እኔ ብነግረሽ ትሰሚያለሽ?"

"አዎ እሰማዎታለሁ"።

"ጠንቋይ ቤት መሄድሽን ተይና እኔ የምልሽን በደንብ ስሚ! በባለሁለት ጡት ትልቅ ጀበና ቡና የሚጠጣበት ለመቁጠር የሚያታክት ስኒ የሚደረደርበት ከፍታ ቦታ ላይ የሚገኝ አንድ ስፍራ አለ። እዛ ሄደሽ ዱአ አድርጊ ልጅ ታገኛለሽ። ቦታው ከጠፋሽ ይህ ዘንዶ ይመራሻል" በማለት ነጭ ቆዳው የሚያብረቀርቅ ዘንዶ ሰጥቶኝ ተሰወረ። ዘንዶው ወደ እኔ እየተሳበ መጣና አጠገቤ ሲደርስ ወደ ጥቁር የሚያስፈራ ዘንዶነት ሲቀየርብኝ ባለቤቴ አይዞሽ ብሎ ገደለልኝ። ይህንን ህልም ካየሁ በኋላ አዋቂ ቤት ሄጄ ህልሙን ስነግራቸው ባለ ሁለት ጡት ጀበና ያለበት ጡሪሲና መስጊድ ነው ስላሉኝ ነው የመጣሁት ካገባሁ ሀያ አመቴ ነው እስካሁን ልጅ አላገኘሁም። የመጨረሻ ተስፋዬ ይህ ቦታ ነው በማለት ይተርካሉ።

ከሰአት በአብዛኛው የሞላላቸው ሰዎች ምስጋናቸውን የሚያቀርቡበት፣ ስጦታቸውን የሚያበረክቱበት ወቅት ነው። ሰአቱ እየመሸ ሲሄድ የአካባቢው ሴቶች ወደ ቤታቸው ሲሄዱ በአሉን ለመታደም የመጡ ሰዎች ደግሞ ለመናፈስ ይወጣሉ።

---

[47] አሚናት ሀሰን ነዋሪነታቸው ድልበር ("ከገዳሙ" የ10 ሰአት መንገድ ይርቃል) አካባቢ ሲሆን ከእህታቸው ፋጡማ ሀሰን ጋር መጥተዋል። "ህልም አይነገርም" በማለት ላለመንገር ቢያንገራግሩም ከብዙ ማግባባት በኋላ ሊነግሩኝ ችለዋል።

### 4.1.2.2.3. ምሽት የሚካሄዱ ስነ ስርአቶች

ሌቶቹ ከአረፍት እንደተመለሱ የኢሻን ሶላት በህብረት ይሰግዳሉ፡፡ ከሶላት በመቀጠል እራት ይበላል፡፡ ከምግብ በኋላ ሁሉም ሰው ወደ ዋናው "ገዳም" ይገባሉ፡፡ በአሉን ለመታደም የመጡት ሰዎች አራት ወይም አምስት በመሆን ቡድን ቡድን መስርተው ጫት ይቅማሉ፡፡ ቡድን የሚመሰርቱት ተመራርጠው ሳይሆን በአጋጣሚ ነው፡፡ ይዘው የመጡትን ሰንደል፣ ስኳር፣ ጫት… አንዳቸው ለአንዳቸው ይሰጣጣሉ፡፡ በየአራት ሰው መካከል ትንንሽ ማጨሻዎች ተቀምጠው ጥሩ መአዛ ያላቸው እጣኖች ይጨሰባቸዋል፡፡ ሰዎቹ ይመራረቃሉ፡፡ አንድ ቡድን መርቆ ሲጨርስ እርስ በራስ ይዞያየራሉ፡፡ ሰላምታው ከቡድኑ ወቶ ለሌላ ቡድን ይተላለፋል፡፡ የሌላውም እንዲሁ፡፡ ቢያንስ በየሁለት ደቂቃው ከስድስት ሰው የበለጠ ሰላም ይላሉ፡፡ የሰላምታ አሰጣጡ በቀኝ እጆቻቸው በመጨባበጥ የእጅ መዳፋቸውን እያገላበጡ ሁለት ሁለት ጊዜ መሳሳም ነው፡፡ የሰላምታውን መብዛት ተከትሎ ለምን በሚል ሲጠየቁ የሺ ፋጢማ[48] "ተጨባበጥንው በሙሉ ስንሞት እንዲህ የመሰለ ጥሩ ቦታ እንደነበርን አንዳችን ለአንዳችን ምስክር እንሆናለን፤ መደጋገሙ ደግሞ እንዳንረሳሳ ያደርገናል" የሚል እምነት እንዳላቸው (ቃ.መ፣ ጥር27፣ 2004፣ጡሩሲና) ይናገራሉ፡፡

ሰአቱ እየገፋ ምርቃናው እየበረታ ሲሄድ ዋናው "ገዳም" አዲስ ትእይንት ማስተናገድ ጀመረ፡፡ "ከገዳሙ" ውጭ የተቀመጠች አንዲት ሴት በጣም እንደበረደው ሰው ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ "እህህ…እህህ…"እያለች ወደ ውስጥ ገባች፡፡ የበአሉ ታዳሚዎች "እሰይ እሰይ" በሚል ማበረታቻ እስከ መስጊዱ መሀል ምሰሶ ድረስ ሸኟት፡፡ ከመስጊዱ ምሰሶ እንደደረሰች "እስ…እስ…ቹ…ቹ…" እያለች መጨፈር ስትጀምር በለበሰችውን ነጠላ ፊቷን ሸፈነች፡፡ ጭፈራዋ ከአፍሪካ ዳንስ ጋር የሚቀራረብ ሲሆን መቀመጫዋን ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ ስታንቀሳቅስ በሁለት እጇቿ ሰው የምታቅፍ ትመስላለች፡፡ ታዳሚው ከስር "እሰይ እሰይ" እያለ አበረታታት፡፡ በግምት ከአምስት ደቂቃ በኋላ መጨፈሯን አቁማ መመረቅ ጀመረች፡፡ ተቀምጠው "እሰይ" ይሏት የነበሩት ሰዎች ተነስተው ከፊት ለፊቷ በመቆም ምርቃቷን ተቀበሏት፡፡ ስትጨርስም ወደ መጣችበት ተመለሰች፡፡

---

[48] በቁጥር 10 የቀረበውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች ሰዎችም ማድረግ ጀመሩ፡፡ ይህንን ትእይንቱን የሚመለከቱ ሌሎች ሴቶች ፊታቸው በደስታ ተሞልቶ በትኩረት እና በንቃት ይከታተላሉ፡፡ አንዳንዶቹ እስከ አስራ አምስት ደቂቃ ይወስድባቸዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ "የእነሱ ብዙ ነው የትግሬው፣ የኦሮሞው፣ ራሄሉው ሁሉም ወንድ መንፈሶች ስላለባቸው ሁሉንም ማስደሰት አለባቸው" የሚል ነው፡፡[49]

---

[49] ይህንን ትእይንት ከነገረ ወሲብ እና ከነገረ ጾታ አንጻር በብዙ መልኩ ልንፈክረው እንችላለን፡፡ ለአብነት የፍካሬ ልቡናን ጥናት ይዘን ትእይንቱን ከነገረ ወሲብ አንጻር ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡ በሲግመን ፍሮይድ በሚቀነቀነው ፍካሬ ልቡናዊ አስተሳሰብ አእምሮ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው በባህልና በልማድ የተሞላው ንቁ (conscious) የአእምሮ ክፍል ነው፡፡ በተከታይነት የሚመጣው ደመነፍሳዊ ፍላጎቶች ማደሪያ የሆነው እና በሰው ልጆ አእምሮ እንደ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫት የሚመሰለው ኢ-ንቁው የአእምሮ ክፍል (unconscious) ነው (ፓሜላ፣4፣2000)፡፡

ኢ-ንቁው የአእምሮ ክፍል ውስጥ የሚስተናገዱ ፍላጎቶች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በጥላቻ እና በሞት ስሜቶች የተሞላ ክፍል ነው፡፡ ሁለተኛው በወሲባዊ ፍላጎት የተሞላው ሊቢዶ በመባል የሚታወቀው እና ከህጻንት ጀምሮ የሚጎለበተው ነው፡፡ የዚህን ወሲባዊ ፍላጎት ክፍታ ለማሳየት በተከደነ ትልቅ ሰተቴ ድስት ውስጥ በከፍተኛ ግፊት በሚፍለቀለቅና ለመገንፈል ማገኛውንም አጋጣሚ በሚጠብቅ ወጥ መስለው ያቀርቡታል፡፡ ከሁለቱ ፍላጎቶች የሚመነጩት ደስታን እና እርካታን የመሻት ስሜቶች ከፍተኛ በመሆናቸው ራስን በመጫን እና በመቆጣጠር ብቻ ሊጠፉ የሚችሉ አይደሉም (ፓሜላ፣104፣2000)፡፡ ይልቁንም ሌላ መውጫ ቀዳዳ ይፈልጋሉ፡፡ በፍላጎቶቹ አማካይነት የሚከሰቱ ግጭቶችን ለማርገብ ከሚጠቀሙባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ህልም እንደሆነ (ፍሮይድ (ዘ፣1994) ይገልጻል፡፡[50]

ከህልም በመቀጠል ሀይማኖቶች እና ሀይማኖታዊ ክብረ በአላት ለግጭቶቹ መፍትሄ ለማበጀት እንደሚያገለግሉ ፍሮይድ ያስረዳል፡፡ በዚህ በአሉ ላይ ሲያሳዩ የነበሩት እንቅስቃሴዎች በኢ-ንቁው የአእምሮ ክፍል ጫና ተደርገባቸው የነበሩ ወሲባዊ ፍላጎቶች በከፊልም ቢሆን ለመቀነስ እድል የሚያገኙበት አጋጣሚ የተፈጠሩበት ነው፡፡ በበአሉ ላይ ጭር ለፍርባቸው የሚንቀሳቀሱት ሰዎች ራሳቸውን ረስተው፣ ለመንፈሱ ተገዝተው፣ ከተገዙለት አካል እና ከነፁበት ስሜት ጨርሰው እስኪወጡ እና በእውኑ አለም በሚደረገው ወሲባዊ ግንኙነት እስኪረኩ ድረስ ያለው ሂደት ተመሳስሎው እጅግ የጠነከረ ነው፡፡ በተለይ ለትዳራቸው ታማኝ የሚባሉ ሴቶች ሁለት እና ከዚያ በላይ ወንድ መንፈስ ለፍርባቸዋል በሚል እምነት የሚያደርጉት ረዘም ያለ እንቅስቃሴ ከትዳራቸው ውጭ ከሌሎች ሰዎች ጋር ወሲብ ለመፈጸም ያላቸውን ድብቅ ፍላጎት ሊያመላክት ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትእይንቱ እየተካሄደ ባለበት ወቅት በቦታው ላይ ያለው ድባብ ሙሉ ለሙሉ እየተቀየረ በሁሉም ሰው ፊት ላይ የደስታ እና የእርካታ ስሜት መታየቱ እንዲሁም በዝምታ የተቀመጡትም ቢሆኑ የሌሎቹን እንቅስቃሴ በማየት የትእይንቱ አካል መሆናቸው ሲታይ ክብረ በአላት ለማህበረሰቡ ድብቅ ወሲባዊ ፍላጎቶች ማስተንፈሻነት እንደሚያገለግሉ ማሳያ ናቸው፡፡

ከሌሊቱ 8፡40 ላይ በትላልቅ ማንቆርቆሪያዎች በውሀ የተበጠበጠ ማር ቀረበ፡፡ ለምን እንደሚጠጣ ሲናገሩ "ደንብ" ነው ቢሉም ምርቃናውን ለማጥፋት ሲገለገሉበት ይችላሉ፡፡ ለሁሉም ሰው አንድ ሙሉ ብርጭቆ ብርዝ ይዳረሳል፡፡ ከዚህ በኋላ ግማሹ ታዳሚ ወደ አገሩ ለመሄድ መንገድ ሲጀምር ግማሹ ደግሞ በተቀመጠበት ሆኖ ያንቀላፋል፡፡

### 4.1.3 የበአል ማግስት

የመውሊድ በአል ከተከበረ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት ለበአሉ ተብለው የተጎዘጎዙ ሳሮች አይነሱም፡፡ በአድሜ የገቱ እና ከሩቅ አገር የመጡ ሰዎች እስከ ሶስት ቀን ቆይተው ይሄዳሉ፡፡ የበአሉ እለት ሰው ስለሚበዛ ሼሁን ለመዘየር ስለማይቻል ማግስቱን ጠብቀው ሼሁን ለመዘየር በማሰብ የሚቆዩት ይበዛሉ፡፡ ስለሆነም የእርድ ስርአቱ፣ ወጥ መስራቱ እንጀራ ማጋገሩ እና ቡና ማፍላቱ እስከ ሶስተኛው ቀን ድረስ ይቀጥላል፡፡ በሶስተኛው ቀን የምግብ እቃዎቹ ተጸድተው ወደ እቃ ቤቱ ይገባሉ፣ ግቢው ይጠረጋል፡፡ በአሉም በዚህ መልኩ ይጠናቀቃል፡፡

## 4.2. የቁርአን ክትሚያ (ሰርግ)

ይህ አዲስ የሚገቡ "ገዳማውያን" የእስልምና ሀይማኖት መመሪያ የሆነውን ቁርአንን ሲጨርሱ የሚከበርላቸው በአል ነው፡፡ በአሉ "ለገዳማውያኑ" እና ለሙሽራው/ለሙሽሪት የቅርብ ዘመዶች ብቻ የተፈቀደ ሲሆን ለሌላው ማህበረሰብ ግን ዝግ ነው፡፡ በዋናነት "ገዳማውያኑን" ለማበረታታት ታስቦ የሚደረግ ሲሆን ለወንዶቹም ለሴቶቹም ይደረጋል፡፡ በወንዶቹ ብዙም ትኩረት ተሰጥቶት ባይካሄድም በሴቶቹ "ገዳም" ግን በጉጉት የሚጠበቅ እና በድምቀት የሚከበር በአል ነው፡፡ ይህንን በአል ወንዶቹ የቁርአን ክትሚያ በማለት ሲጠሩት ሴቶቹ "ሰርግ" ይሉታል፡፡

የሰርጉ ቀን የሚወሰነው በሼሆቹ ሲሆን በአብዛኛው ለሰርጉ የሚመረጠው እለት ሰኞ ነው፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት ሲያስረዱ "ሰኞ ነቢያችን የተወለዱበት እለት በመሆኑ ነው" ይላሉ (ቃመ፣ ጥር26፣ 2004፣ ጡሩሲና)፡፡ የሰርጉ ቅድመ ዝግጅት የሚጀመረው ከሰርጉ አንድ ሳምንት በፊት ወደ ባለተራዋ ሙሽራ ዘመዶች "ልጃችሁ ልታገባ ነውና ኑ" የሚል መልእክት በመላክ ነው፡፡ ከዚያም ዘመዶቿ የደስ ደስ ልብስ እና የተለያዩ ስጦታዎችን ገዝተው ያመጡላታል፡፡ ሼሆቹ

ደግሞ ከሰርጉ ቀን አንድ ቀን ቀደም ብለው ነጭ ሀር ቀሚስ፣ ጉፍታ፣ ኩታ፣ ሽቶ፣ ምስኪ/እድሩስ... ለሙሽራዋ እንደሚልኩ አቶ እድሪስ ሙሄ[50] (ቃ.መ፣ ጥር 28፣ 2004፣ እድሪስ ሙሄ፣ሼክሶ) ይተርካሉ። ከዚህ በኋላም ጓደኞቿ "ገዳሙን" ያስተካክላሉ። ያጸዳሉ።

የሰርጉ ቀን ጠዋት ሙሽራዋ ከቤተ ዘመድ እና ከሼሆቹ የመጣላትን ልብስ በጓደኞቿ እርዳታ ትለባብሳለች፣ ትኳኳላለች። አምስት ሰአት ሲሆን በጓደኞቿ ታጅባ ወደ ዋናው መስጊድ እየተዘፈንላት ትገባለች። የዘፈኑ ይዘት የጋብቻን ጥሩነት የሚነግር፣ የነቢዩ መሀመድን ደግነት እና ሲጋስነት የሚያስታውስ ነው። ዋናው መስጊድ ውስጥ ከገባች በኋላ ሁሉም በተሰበሰበበት አንድ የቁርአን ምእራፍ ትቀራለች። በመቀጠልም ዝሁር ሶላት ይሰገድና ከሴሎቹ በተለየ ለሙሽራዋ ዱአ ይደረግላታል። በቤተሰቦቿ፣ በዱብርቲዎች እና በእሜቴ ትመረቃለች። የምርቃቱ ይዘት በቁርአኗ እንድትበረታ፣ እውቀቷን አላህ እንዲጨምርላት፣ የአዱንያ (አለማዊ) ሳትሆን የአሄራ ሰው እንድትሆን እና አላህ የጀነት ሰው እንዲያደርጋት ነው። ከምርቃቱ በኋላ ለሰርጉ የተዘጋጀው ምግብ ይቀርባል። ለሰርጉ የሚዘጋጀው ምግብ በአብዛኛው በሙሽራዋ ቤተሰቦች የሚሸፈን ሲሆን ቤተሰቦቿ ካልቻሉ ግን በገዳማውያኑ ይሸፈናል።[51]

ምግብ ከተበላ በኋላ ቤተሰቦቿ እና ዱብርቲዎቹ ከመስጊዱ ሲወጡ ደረሳዎቹ ግን እዛው በመትረት መዝፈን ይጀምራሉ። ከደረሳዎቹ ውስጥ በድምጿ ማማር የምትመረጠው አሚናት ሼህ ያሲን[52] የተባለችው ደረሳ እንዲህ በማለት ታስጀምራለች (ቃ.መ፣ ጥር26፣ጡሩሲና) ።

| | |
|---|---|
| ቢስሚላሂ ሪህማኒ ረሂም | ቢስሚላሂ ሪህማኒ ረሂም |
| ቢስሚላሂ ጀይ | ቢስሚላሂ አልኩኝ |
| ጎርሳን ጀባ ቀባ | ቢመክሩ ስጦታ አለው |
| ቢስሚላሂ ደበርሴ | በቢስሚላሂ አሳልፌ |
| ጎርሲኒ ጠቀማ | ምክሬን እጠቀማለሁ |
| ወረረቢ ጆርሴ | ከአምላክ ጋር ያሉ ሰዎች |
| ዋጂበል ሰፈዲፍቱ | ብለው መሬት ለቀዋል |
| ተኮምበር ባዲኒ | ከዚህ ውጭ ምንም አትፈልግ |

[50] አቶ እድሪስ ሙሄ የሚኖሩት ሼክሶ 01 ቀበሌ ውስጥ ሲሆን ባለትዳር እና የሶስት ልጆች አባት ናቸው። እድሜአቸው 38 ሲሆን መተዳደሪያቸው ግብርና ነው።
[51] የምግብ አሰራሩ በቁጥር 79 ከተጠቀሰው የግርጌ ማስታወሻ ጋር ተመሳሳይ ነው።
[52] አሚናት ሼህ ያሲን "በገዳሙ" ውስጥ ለብቻቸው ተለይተው ከሚኖሩት አስር ደረሶች ውስጥ አንዷ ስትሆን እድሜዋም በግምት 38 አካባቢ ነው። በህጻንነቷ ወደ "ገዳሙ" የገባች ሲሆን አለኝ የምትለው ዘመድ የላትም።

መርጤ ፈዱ ቀፑ
ጀማሞሪ ዱኒ…

ፈቅደው ይህንን ያሉ
ጀማው ተጠቅሟል፡፡

በማለት በኦሮምኛ ያዜማሉ። ከኦሮምኛው በመለስ ሌሎች ደረሳዎች በአማርኛ እንዲህ በማለት ይቀበሏታል።

ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም
እስቲ እንናገረው የአህመድን ሰፈር
በከዲጃ ገንጀብ ወደ ሻም አገር
እውቀቱ የበዛ አንድ አሊም ነበረ
ተወረተል እንጂልን ቀርቶ ያወቀ እጅግ ነገር
መሀመድ አሚንን እልፍ ሲል አዩት
ከከዲጃ ደጃፍ ከዛ አስጠሩዎት
መሀመድ ከአንተ ላይ የማየው ነበር ምልክት
አለው ጥኪሻህን ገልጠህ ባየሁት
እሱ እንደከጀለ አለ ገለጡለት
ሀተመን ንቡወት አዩ ተከትበበት
ያሻውን አገኘ ሙራዱ ሆንለት
ለሜቱ ከዲጃ ምስጢር ነገረዎት
አኼራ የሚላከው ይሄ ነው አለዎት
እሱን ያገባች ሴት ለካ እሳህ መረጣት
በአዱንያም በአሄራም እሳህ ጎጆ አወጣት…
(ግጥሙ አላለቀም ከዚህ በላይ ሊነግሩኝ አልፈቀዱም፡፡)

እነዚህ እና መሰል ዘፈኖችን ከዘፈኑ በኋላ ሙሽራዋ ወደ ዋናዎቹ "ገዳማውያን" ትቀላቀላለች፡፡ ወደ ዋናዎቹ "ገዳማውያን" ከተቀላቀለች በኋላም የምትሰራውን፣ የምታደርገውን እና የምትሆነውን የምታውቅ ናት ተብሎ ስለሚታመን ማንም ጫና አያደርግባትም፡፡ [53]

---

[53] ቴዎድሮስ ገብሬ (2001 ዓ.ም) ስነ ልቡናዊ ተጋዳሊ በማለት ካሰፈሩት ጥቂት ሀሳቦችን በመምዘዝ የሴት ገዳማውያንኑን የሰርግ ስርአት የዘመናዊው ተጋዳሊ ልቡናዊ ጉዞ አምሳያ አድርገን ልንፈክረው እንችላለን፡፡ እንደ

ቴዎድሮስ ገለጻ ስነ ልቡናዊ ጉዞ በውል ከምናውቀው የንቁው የአእምሮ ቀጠና ወደማናውቀው እና ወደ ጨለማው አለም የሚደረግ ጉዞ ነው፡፡ ወደ ገዳማውያኑ ስንመጣ የምንኖርበት አለም ንቁውን አእምሮ የሚወክል ሲሆን የገዳም ህይወት ግን እስልምና እና ሙስሊሞች የማያውቁት የጨለማው አለም አምሳያ ነው፡፡

በዚህ ጉዞ ተጋዳሊው ህልውናን ለመፈተን ዘብ ከቆሙ ከተስፋ መቁረጥ፣ ትላንትን፣ ትዳርን ፣ ቤተሰብን፣ ትምህርትን ከመናፈቅ እና ከአእምሮ ህውከት ጋር መተናነቅ ይጠበቅበታል (ቴዎድሮስ፣2001፣91)፡፡ ይህ ጉዞ ለገዳማውያኖቹ በገዳሙ ውስጥ በፀሎትን መኖር መቻል እና አለመቻላቸው የሚለይበት እና ብርታታቸው እና ጥንካሬያቸው የሚፈተንበት ነው፡፡ ፈተናዎቹም ከማንኛውም ወሲባዊ ፍላጎት ታቅበው፣ ያሳለፉትን ቤተሰባዊ ኑሮ ዘንግተው፣የጀመሩትን ትምህርት ትተው፣ ራእይና ተስፋቸውን ገለው ወደ ራሳቸው እንዲያዩ እና ማንነታቸውን እንዲረዱ ማስቻል ነው፡፡ ተጋዳሊው ወደ ንቁው ቀጠና በጠለቀ፣ ብዙ በተጓዘ፣ እጅግ በጠለቀ ቁጥር "በኢ-ንቃት ያሙቃቸው ልብ ሳይል የቀበራቸው ከአካባቢው ከባህሉ፣ ከሀይማኖቱ፣ ከፖለቲካው፣ ከአካዳሚው እውቀት ለተፈጥሮም ጭምር የሚቃረኑ የሚመስሉ በወፈፌነት፣ በድሁርነት፣ በመናፍቅነት የሚያስፈርጁ ግለሰባዊ እውነታዎቹ' ይገጥሙታል (ቴዎድሮስ፣2001፣92)፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ፈታኝ ጉዞዎች ወንድ "ገዳማውያን" ፈተናውን ማለፍ ተስኗቸው ወደ ትላንት ማንነታቸው ለመመለስ "ገዳሙን" ትተው ይወጣሉ፡፡[53] በአንጻሩ ሴት "ገዳማውያን" ስንመለከት እነዚህን እና መሰል ፈተናዎች ቢፈተኑም አንድም ከመመለስ ወደ ፊት መቀጠሉ የተሻለ ነው ባለው በማሰብ አንድም ንቁው የተውቱን አለም እንደገና ለመመለስ ስለሚያሣፍራቸው በጉዞው ገፍተው የጋብቻ ስርአት ከዋኙው ይፈጸምላቸውና ከራሳቸው ጋር ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ "ራሱን ያገኘ፣ ራሱን የገለጠ ሰው በውስጣዊው የጨለማ አለሙ ላይ ስለሚሰለጥን የሚሆነውን፣ የሚሰራውን የሚያውቅ ትክክለኛ ነዋሪ ይሆናል"(ቴዎድሮስ፣2001፣94)፡፡ በዚህ ምክንያት ከስርጉ በኋላ የሚሰሩትን፣ የሚያወሩትን፣ የሚያደርጉትን ያውቃሉ በሚል እስከ ማገም አይቆጣጠሩቸውም፡፡ ከዚህ ቀደም የማይፈቀድላቸው ኪታብ እና አውራድ የመጻፍ መብት ይሰጣቸዋል፡፡

# ምእራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ዞን በከሚሴ ከተማ በዳዋ ጨፋ ወረዳ በሚገኘው የጡሩሲና "ገዳም" ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነበር። የጥናቱ ዋና አላማዎች የጡሩሲና "ገዳም" ገዳም ብሎ መጥራት መቻሉን ማመላከት፣ "ገዳሙ" በአገራችን ሲኖር የቻለበትን ምክንያት ማሳየት እና "በገዳሙ" የሚከበሩ ክብረ በአላት ፎክሎራዊ ገጽታ መመርመር ነበሩ።

"የገዳሙ" ህግ እና ደንብ በፈቀደው ልክ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል። የምልከታ ዘዴን መጠቀሙ የገዳማውያኑን እና የክብረ በአላቱን ማህበራዊ እና ባህላዊ አውድ ለመገንዘብ፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት ደግሞ የገዳሙን አመሰራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የገዳማውያኑን የስራ ድርሻ እና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተርጎም እና ለማረጋገጥ አስችለዋል።

ከላይ በተገለጹት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችን ግልጽ እና ምስል ከሳች በሆነ መንገድ እንዲቀርቡ ለማድረግ የተመረጠው ገላጭ የትንተና ስልት ነበር። በማስከተልም የዚህ ጥናት አላማ የሆኑትን ክብረ በአላት ለመረዳት ክዋኔን ያማከለ ንድፈ ሀሳብን በመምረጥ እና የተለያዩ ጸሀፍት ስራዎች ላይ ንባብ በማካሄድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ሊተነተኑ ችለዋል። ትንተናው የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝቷል።

የጡሩሲና "ገዳም" ከአካባቢው ነዋሪዎች ርቆ በሚገኝ ተራራማ እና ጫካ ቦታ ላይ ይገኛል። "ገዳማውያኑም" ቤተሰቦቻቸውን፣ ዘመድ አዝማዳቸውን እና የሚኖሩበትን አካባቢ ትተው ለፈጣሪያቸው ለመገዛት የወሰኑ ናቸው። በዚህም ምክንያት የጡሩሲናን መስጊድ "ገዳም" በውስጡ የሚኖሩትን "ገዳማውያን" ብሎ መጥራት ተችሏል። የጡሩሲና "ገዳም" አገራችን በሚገኘው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት የአንድነት ገዳም ጋር ይቀራረባል። በሁለቱም ገዳማት አንድ ምእመን ገዳም ከገባ በኋላ መውጣት አይችልም፣ ገዳማቱ የሚተዳደሩባቸው ህጎች ሲኖሯቸው ህጎቹም በገዳማውያኑ ይከበራሉ፣ ገዳማቱ የሚተዳደሩበት አስተዳደራዊ መዋቅር እና የስልጣን ተዋረድ አላቸው፣ ገዳማውያኑ አብዛኛውን ጊዜአቸውን በመጾም

በመጸለይ ያሳልፋሉ፣ በገዳማውያኑ መካከል ከግለሰባዊነት ይልቅ አንድነት እና ህብረት እንዳለ ጥናቱ አመላክቷል።

በእስልምና ሀይማኖት ያልተለመደው የገዳም ህይወት በአገራችን ብሎም በወሎ የተገኘበትን ምክንያት ወሎ ሙስሊሙ እና ክርስትያኑ እርስ በራስ ተከባብሮ እና ተቻችሎ የሚኖርበት ስፍራ በመሆኑ እንደሆነ አሳይቷል። በወሎ የሙስሊሙ መገለጫዎች በኦርቶዶክስ ክርስትና፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና መገለጫ የሆኑት ደግሞ የሙስሊሙ ሆነው ሲተገበሩ ይታያል። የጡሩሲና ገዳምም ይህን መሰሉ በጎ የሆነ የመወራረስ ባህሪ የፈጠረው ተቋም ነው የሚል መነሻ ሀሳብ ሰጥቷል።

በገዳማውያኑ ከሚከበሩ ክብረ በአላት ውስጥ የመውሊድን እና የቁርአን ክትሚያን ተመልክቷል። የመውሊድ በአል በአመት አንዴ የነቢዩ መሀመድ ልደትን ለማክበር ታስቦ የሚከናውን ነው። ይህንን በአል ከተለያዩ አካባቢዎች ተጉዘው የሚመጡ ሙስሊሞች እና ጥቂት ክርስትያኖች ያከብሩታል። የቁርአን ክትሚያ/ሰርግ ደረሳዎቹ ቁርአንን ማክተም/መጨረስ ምክንያት በማድረግ "ገዳማውያኑን" ለማበረታታት በደረሳዎቹ ብቻ የሚከበር ነው።

## 5.2 መደምደሚያ

ይህ ጥናት መደረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሁለት ጉዳዮች አስገኝቷል።

### 5.2.1 በአገራችን የሙስሊም ገዳም መኖሩን አሳይቷል።

በጡሩሲና "ገዳም" የሚኖሩ "ገዳማውያን" የእስልምና ሀይማኖት ከሚያዛቸው አምስት መሰረታዊ ህጎ.ጋት መካከል አራቱን የሚፈጽሙ ሙስሊሞች ናቸው። በአላህ አንድነት እና በነቢዩ መሀመድ መልእክተኛነት የሚያምኑ፣ የሰላት ሰአታቸውን ሳያዛንፉ የሚሰግዱ፣ ረመዳንን የሚጾሙ እና ዘካ የሚያወጡ (የሚመጸውቱ) ናቸው። በአምስተኛነት የሚመጣው በህይወት ዘመን አንዴ ወደ መካ መጓዝ የሚለው ህግ በአቅም ውስንነት ምክንያት አይደለም "በገዳማውያኑ" በአብዛኛው ሙስሊም ህብረተሰብ የሚቻል ባለመሆኑ ገዳማውያኑን ሙስሊም አይደሉም ለማለት የሚያበቃ አይደለም። በክርስትና ሀይማኖት የተለመደውን እና በእስልምና ሀይማኖት ያልተፈቀደውን የገዳም ህይወት የሚመሩ በመሆናቸው ሙስሊም ተብለው መጠራት የለባቸውም የሚሉ ቢኖሩም እንኳ አንድን ሙስሊም እንደ አማኝነቱ ሊተገብራቸው

ከሚገደዱባቸው አምስት ህግጋት መካከል አብዛኛውን በመተግበራቸው ሙስሊም በዚህ ጥናት ገዳማውያኑን ሙስሊም ብሎ መጥራት ተችሏል፡፡

በጡሩሲና መስጊድ የሚስተዋለውን ገዳማዊ አኗኗር፣ ከገዳም እና ገዳማዊ ሕይወት ብያኔ እና የጋራ ባህሪ አንጻር ሲታይ በብዙ መልኩ የሚቀራረብ ነው፡፡ በዚህም መነሻ ሀሳብ ደረሳዎቹን "ገዳማውያን" መስጊዱን ደግሞ ገዳም ተብለው ተጠርተዋል፡፡ በአጠቃላይ በእስልምና አስተምህሮት ያልተፈቀደውን የገዳም ህይወት የሚተገብሩ ቢሆኑም እንኳ ሙስሊም የመሆናቸውን እውነታ እና የመስጊዱን ገዳማዊነት መካድ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የተለያዩ ጽሁፍት ስራዎችን በመጥቀስ እና በመስክ የተገኙ መረጃዎች ላይ ሰፊ ትንታኔ በመስጠት በአገራችን የሙስሊም "ገዳም" መኖሩን አረጋግጧል፡፡

### 5.2.2 በአገራችን ያለውን የሀይማኖት መቻቻል፣ መከባበር እና እርስ በራስ የመወራረስ ባህሪን ከማመላከቱም በተጨማሪ ወሎ የሀይማኖቶች መቀራረብ የሚስተዋልበት እንደሆነ ገልጿል፡፡

ኢትዮጵያ እስልምናን በሰላማዊ መንገድ የተቀበለች የመጀመሪያዋ አገር ናት፡፡ በሰላማዊ መንገድ የተጀመረው የእስልምና እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖቶች ለዘመናት ያቆዩትን መልካም ግንኙነት ለመረዳት በተለያዩ አካባቢዎች መስጊድ እና ቤተክርስትያን ጎን ለጎን መሰራታቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አንዋር መስጊድን እና ራጉኤል ቤተክርስትያንን ለዚህ አብነት ናቸው፡፡ የሁለቱ ሀይማኖቶች ቅርበት እና መተጋገዝ በሰፊው ከሚንጸባረቅባቸው የአገራችን አካባቢዎች መካከል ወሎ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ በወሎ ሙስሊም ክርስትያኑ መጋባት፣ አንዱ የሌላውን በአል ማክበር የተለመደ መሆኑን ብዙ ጸሁፍት ገልጸዋል፡፡ አብዛኞቹ በአላት በሁለቱም የእምነት ተከታዮች ይከበራሉ፡፡ በወሎ በሚከበረው የጥምቀት በአል በክርስትያኑም በሙስሊሙም ታቦቶቹ እኩል ሽኝት ይደረግላቸዋል፡፡ በአመት አንዴ የሚመጣው የሙስሊሙም የረመዳን ጾም ከአንድ ወሩ ከሶስት ቀን እስከ አምስት ቀን ሙስሊም ጎረቤቶችን እና ዘመዶችን ለማበረታታት ክርስትያኖቹ እኩል ይጾማሉ፡፡ በአሉንም ያከብራሉ፡፡ በዚህ አካባቢ የሚስተዋለው የሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች ቅርበት ከአማኞቹ በተጨማሪ በሀይማኖቱ ስርአት እና ተቋማት ላይ የመወራረስ እና የመመሳሰል ባህሪ እንዲታይ መንገድ እንደከፈተ ጥናቱ

አመላክቷል። በአገራችን የሙስሊም "ገዳም" መኖሩ በዋናነት በአገራችን/በወሎ ያለውን የሀይማኖቶች ተቻችሎ እና ተቀራርቦ የመኖር ባህልን በግልጽ የሚያሳይ ነው።

## 5.3 ይሁንታ

የሙስሊም "ገዳም" መኖሩ በአገራችን ያለውን የሀይማኖቶች ተቀራርቦ የመኖርን እውነታ በትክክል እንደሚያስረዳ ጥናቱ እንዳመለከተ ከላይ ተገልጿል። ይህ ባህል ከፎክሎር ተመራማሪዎች በተጨማሪ ታሪክን፣ ባህልን፣ ሀይማኖትን መሰረት አድርገው ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች በአገራችን/በወሎ ለጥናት የሚሆኑ በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ይጠቁማል።

ለዚህ ጥናት በማሰብ በተደረገው ንባብ የሙስሊም ገዳም መኖሩን የሚያረጋግጡ መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም። በመሆኑን ገዳሙ የመጀመሪያው የሙስሊም "ገዳም" ሊሆን ይችላል። ይህ መሆኑ ደግሞ "ገዳሙ" ላይ ትኩረት በማድረግ ለቱሪዝም የሚያገለግልበትን መንገድ ቢመቻች ለአገራችንን የገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።

# ዋቢ ጽሁፎች


ሞገስ ጀንበሩ፣ "ከዲጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርአቶች"፣ የኢትዮጲያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ለማስተርስ ዲ ግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2003።

ምክረ ስላሴ ገብረ ማሪያም፣ *የእግዚአብሄር መንግስት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተ ክርስትያን ታሪክ ሁለተኛ መጽሀፍ*፣ አዲስ አበባ፣ አርክቲክ ማተሚያ ቤት፣ 2000።

ስሜ ታደሰ፣ *የቤተ ክርስትያን ታሪክ*፣ አዲስ አበባ፣ ኢስ አይ ኤም ፕሬስ፣ 2002።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ *መጽሀፈ፣ ሰዋስው፣ ወግስ፣ ወመዝገበ፣ ቃላት፣ ሀዲስ*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ሼህ ሰይድ መሀመድ እና ሀጂ መሀመድ ሳቢ፣ *ቅዱስ ቁርአን፣* አዲስ አበባ፣ ነጃሽ አሳታሚ፣ 1961።

ቦጋለ ተፈሪ፣ *ትዝታ ሼህ ሁሴን ጅብሪል*፣ አዲስ አበባ፣ እስናቀ ማተሚያ ቤት፣ 2002።

ታደሰ አይቸሉህም፣ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የምንኩስና ስርአት እና የገዳማውያን የእለት ተእለት ህይወት ከትምህርታዊነቱ አንጻር በዝቋላ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ ተክለ ሀይማኖት ተቋማት"፣ የኢትዮጲያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1999።

ቴዎድሮስ ገብሬ፣ *ሰበን ዲሲፕሊናዊ የስነጽሑፍ ንባብ*፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማእከል፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993።

የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፣ *መጽሀፍ ቅዱስ፣* የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1980።

አባ ፊሊጶስ፣ *የምንኩስና ስርአትና ብሂል*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1961።

ወርቁ [illegible]፣ "በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ፣ የጨፋ መድኃኔአለም፣ ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማሪያም እና ቅድስት ስሉሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሰራረት ፎክሎራዊ ገጽታ"፣የኢትዮጲያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ጌታቸው መኮንን፣ *ወሎ የአገር ድባብ*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1984።

ፊታውራሪ አመዴ ለማ፣ *የሀይወት ታሪክ (ከመጋቢት 1913-2001)*፣ አዲስ አበባ፣ ማስተርስ ማተሚያ ቤት፣ 2003።

"የኦሮሚያ ዞን ገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት መምሪያ"፤ ከሚሴ፣ 2001።

"የከሚሴ ከተማ ባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት"፤ ከሚሴ፣ 2002።

"የዳዋ ጨፋ ወረዳ ገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት"፤ ከሚሴ፣ 2002።

Barties, Peter. *Folklife and Field Work: A Layman's Introduction to field Techniques.* Washington: Library of Congress,1976.

Welsh, Alexander. *Freud's Wishful Dream book.* Princeton, Newjersey: Princeton University Press, 1994.

Bauman, Richard, and Briggs L, Charles. *Poetics and Performance as Critical Perspectives on Language and Social Life* : Annual Review of Anthropology New york: vassar college, 1990.

Bauman, Richard, ed. *Folklore Cultural Performances and Popular Entertainment.* New York: oxford University Press, 1992.

Ben-Amos, Dan. *"Context in Context" Western Folklore: Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture,* 1993.

________. *"Toward A Definition of Folklore in Context: Toward New Perspectives in Folklore."* <u>TheJournal of American Folklore,</u> 1971.

Benjamin C, Ray. *African Religion: Symbol, Ritual and Community.* Newjersy: Prentice Hall, 1976.

Berhanu, Gebeyehu. "Islamic oral Poetry In Wallo: a Preliminary Descriptive Analysis." department of literature. unpublished MA Thesis. Addis Ababa University, 1998.

CR, Kothari. *Research Methodology: Methods and Techniques.* indiya: new age international limited publisher, 1985.

Dundes, Alan, and Bronner J, Simon, eds. *The Meaning of Folklore.* Logan Utah: Utah State University Press, 2007.

Ferber, A, micheel. *A Dictionary of literary symbols.* Cambridge university press, 2007.

Geertz, Clifford. *The Interpretation of Cultures: Selected Essays.* <u>A Member Of The Peneul Boob Croup</u>. New jersey: princeton university press, 1973.

Glazier, D.Stephen, and Flowerday A, Charles, eds. 2003. *Selected Readings In The Anthropology of Religion: Theoretical and Methodological essays.* London: West Port, 2003.

Habtamu, Mengste. 1988. "A History of Monastery of Mertulamariyame(C1500- 1974)." Department of history. un published Ba Thesis. Addis Ababa University, 1988.

Olson, carl. *Celibacy and religious traditions.* New York: Oxford university press, 2008.

Hufford, Mary. *Context: Keywords for the Study of Expressive Culture.* The Journal of American Folklore. Autumn: American Folklore Society, 1995: 528-549.

Hussein, Ahmed. *Islam In Nineteeth Century Wallo, Ethiopia b: Revival, Reform And Reaction.* Brill, Leinden: Boston, 2001

__________. *The Historiography of Islam In Ethiopia.* Journal of Islamic Studies, 1992.

Jon, Abbink. *An Historical-anthropological approach to Islam in Ethiopia: Issues of identity and politics.* Journal of African Cultural Studies, Volume 11, Leiden, 1998

Kapchan, A Deborah. *Performance.* The Journal of American Folklore. New York: 1995: Vol. 108, No. 430.

Kaplan, B. Steven. *The Monastic Holy Man the Christianization of Ethiopia, 1270—1468.* unpublished dissertation. Hebrew University press, 1982.

Kenneths, Goldstein, and Henderson, Hamish. *A Guide for Field Workers in Folklore.* The American Folklore Society. Pensilvaniya,1964.

Mengstu, Kebede. "The Role of Debre Libanos Monastery In The Ethiopian Orthodox Tewahdo Church." Trinity college. unpublished BA Thesis. Addis Ababa University, 1999.

Peek M. Philip, and Yankah, Kwesi, eds. *An Encyclopedia of African Folklore.* New York: Routledge, 2004.

Ruth Finnegan. *Oral Traditions and the Verbal Arts: AGuide to Research Practices.* London And New York: Routledge, 1992.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition.* Logan: Utah State University Press, 2005.

Tegbaru, Adane. "A Brief History of Dima Giorgis Monastry." Department of History. un published Ba Thesis. Addis Abeba University, 2002.

Thurschwell, Pamela. *Sigmund Freud. Essential guides for literary studies.* routledge critical thinkers. Usa and Canada: Routledge, 2000.

Tigabu, Bezie. "The Ethiopian Claim on The Monastery Deir= Es Sultan InJerusalem, 1850-1994". department of history. un published MA Thesis. Addis Ababa University, 1999.

Trimingham J, Spenser. *Islam in Ethiopia*. London and New York: Oxford University Press, 1952.

Zelalem, Assefa. "A Brief History and Activities of Zeway Debre Tsion Monastery." Trinity College. unpublished BA Thesis. Addis Ababa University, 2001.

# አባሪ 1

# የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባይ ስም | እድሜ | የት/ት ደረጃ | ሙያ | አድራሻ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ | የመረጃው አይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አዩብ አብደላ | 26 | በታሪክ ት/ት ክፍል ድግሪ | የእ/ዞን የቅርስና መስህብ ሀብቶች ጥናት፣ምዝገባ እና ቁጥጥር ሀላፊ | የከሚሴ ከተማ ነዋሪ | ጥር 25/04 | ከሚሴ | ስለ ዞኑ ታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርሶች |
| 2 | አቶ አህመድ መሀመድ | 27 | በግብርና ት/ት ክፍል ድግሪ | የወረዳው ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ | የከሚሴ ነዋሪ | ጥር 27/2004 | ከሚሴ እና ሼክላ | የገዳሙን አስተዳደራዊ መዋቅር፣የስራ ድርሻ |
| 3 | አቶ መሀመድ አማን | 55 | ምንም | ግብርና/አስታረቂ | ሼክላ | መረጃ ለመውሰድ በሄድኩባቸው ጊዜያት ሁሉ | ከሚሴ፣ ጡሩሲና እና ሼክላ | የሼሁን ታሪክ፣ተአምራት እና የመውሊድ በአል ዝግጅት |
| 4 | ወ/ሮ የሺ ፋጢማ | 59 | አልተማሩም | የገዳማውያኑ ካዳሚ | ጡሩሲና | ታህሳስ 20/04 | ጡሩሲና | ስለ ገዳሙ አጠቃላይ ህግ፣ የሴቶችን ቁጥር፣ እና ህይወት |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | አንሻ ጧሂር | 43 | አልተማሩም | የንዳግውያት ኳዳሚ | ጡሩሲና | ጥር 26-27/04 | ጡሩሲና | ስለ መውሊድ በአል አከባበር፣ በሴቶች ገዳም ስለሚደረገው ቅድመ ዝግጅት6 |
| 6 | አቶ እንድሪስ ሙሂ | 36 | ከ 8ኛ ክፍል ያቋረጡ | ግብርና | ሽነካ | ጥር 28/04 | ሽነካ | ስለ ቁርአን ከትሚያ እና የገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅር |
| 7 | አቶ ሀሚድ እንድሪስ | 40 | አልተማሩም | ግብርና | ሽነካ | የካቲት 02/04 | ሽነካ | የመውሊድ በአል አከባበር በወንዶች ገዳም ያለውን ገጽታ |
| 8 | መሪማ እንድሪስ | 28 | አልተማረችም | ደረሳ | ጡሩሲና | የካቲት 01/04 | ጡረሲና | የቀለም አሰራር እና የኪታብ እና የአውራድ አከታተብ |
| 9 | ሰአዳ መሀመድ | 19 | 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቀች | ደረሳ | ጡሩሲና | የካቲት 01/04 | ጡሩሲና | የሰርግ ስርአተ ክዋኔ |
| 10 | ሼህ ጀማል አድሪስ | 67 | አልተማሩም | ደረሳ | ጡሩሲና | የካቲት 01/04 | ጡሩሲና | ስለ ገዳሙ ህግ |

ንኡሳን መረጃ አቀባዮች

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ/ሮ እንጓ ከማል | 51 | አልተማሩም | የቤት እመቤት | ሀርቡ | ጥር 27/04 | ጡሩሲና | በእሉን ለማክበር የመጡበትን ምክንያት |
| 2 | ሰእዳ ኡመር | 37 | 12ኛን ያጠናቀቀች | የቤት እመቤት | ከሚሴ | ጥር 26/04 | ጡሩሲና | በእሉን ለማክበር የመጣችበትን ምክንያት |
| 3 | ወ/ሮ አሚናት ሀሰን | 38 | አልተማረችም | የቤት እመቤት | ድልበር | ጥር 26/04 | ጡሩሲና | በእሉን ለማክበር የመጣችበትን ምክንያት |
| 4 | ሼህ አብዱል ሀቅ | 41 | አልተማሩም | ደረሳ | ጡሩሲና | ግንቦት13/04 | ጡሩሲና | የቡድን ውይይት |
| 5 | ሼህ የሱፍ አረብ | 56 | አልተማሩም | ደረሳ | ጡሩሲና | ግንቦት 13/04 | ጡሩሲና | የቡድን ውይይት |
| 6 | ሼህ ኡካሽ | 49 | አልተማሩም | ደረሳ | ጡሩሲና | ግንቦት 13/04 | ጡሩሲና | የቡድን ውይይት |
| 7 | ወንድወሰን እንዱአለም | 29 | በክፍለ ት/ታችን የማስተርስ ተማሪ | መምህር | አዲስ አበባ | ግንቦት 13/04 | ጡሩሲና | አወያይ |

# አባሪ ሁለት

# የሼህ መሀመድ አማን የህይወት ታሪክ

## በአጭሩ

ሼህ መሀመድ አማን ከእናታቸው አሚናት ሰይድ እና ከአባታቸው አቶ አማን በ1915 ዓ.ም ገደማ ተወለዱ። በአሁኑ ወቅት እድሜአቸው ዘጠናዎቹ መጀመሪያ አካባቢ እንደሆነ ይነገራል። ሼሁ በአብዛኛው ምግብ የማይበሉ ሲሆን በቀን አንዴ አንድ ብርጭቆ ውሀ ብቻ እንደሚጠጡ ይነገርላቸዋል። ለጡሪሲና መስጊድ መመስረት ከፍተኛ ሚና የተጫወተው በአካባቢው የነበረ አንድ መስጊድ ነው። የአማን አምባ መስጊድ ይባላል። የዚህ መስጊድ መስራች ከየጁ አውራጃ ዳና ከተባለ ቦታ በ1930 ዓ/ም አካባቢ የመጡና በዚሁ ቦታ ላይ ያረፉ ሼህ መሀመድ የተባሉ ሰው ነበሩ። ሼህ መሀመድ አማን አምባ በኖሩበት ዘመን ከነበሯቸው ደረሶችና ካዳሞች መካከል በአስራ አራት አመታቸው ወደ መስጊዱ የገቡት ሼህ መሀመድ አማን አንዱ ናቸው። በ1958 ዓ.ም የአማን አምባው ሼህ ከማረፋቸው 6 አመት ቀደም ብሎ በነበራቸው የቁርአን እውቀት እና የመካደም ችሎታ ከሌሎቹ ተሽለው ስለተገኙ የሼህነት ስልጣኑን ተረክበው ነበር። አማን አምባ እያገለገሉ በነበረበት ወቅት ቤተሰብ ዘመድ አዝማድ ሳይሉ ሙሉ ጊዜአቸውን ሰውተው ይካድሙ እንደነበር ይነገርላቸዋል። የኋላ ኋላ የሼሁን ማረፍ ተከትሎ ነገሮች ለሼህ መሀመድ አማን ጥሩ አልሆኑም። የአማን አምባው ሼህ ወንድ ልጆች የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ በማንሳታቸው በመስጊዱ ውስጥ ሽኩቻ ተፈጠረ።

ነገሩ እየከረረ በመምጣቱ በአካባቢው ሽማግሌዎች እንዲታይ ተወሰነ። በውሳኔውም የአማን አምባ ሼህ ልጆች ከሌላ አካባቢ (የጁ) ተሰደው በመምጣታቸው እንግዳ ናቸውና እነሱን ማስለቀቅ ባህሉ አለመፍቀዱን በመግለጽ የዛው አካባቢ ተወላጅ የሆኑት ሼህ መሀመድ አማን መስጊዱን ለቀው ሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ ተደረገ። የሽማግሌዎችን ውሳኔ በማክበር ቦታውን የለቀቁት ሼህ መሀመድ ወደ ጡሪሲና መስጊድ ሄደው ሰፈሩ። አማን አምባ በነበሩበት ወቅት ለጉዳይ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄዱ የጡሪሲና መስጊድ የሰፈረበት ቦታ ይደርሳሉ። በዚህ ጊዜ አንድ ሼህ ሜካውን ብቻ እያዩ "ይህንን ሁሉ ከለዋ አይተሀዋል?" ይሉ ነበር። አብረዋቸው የሚሄዱ ደረሶች የተባለው ቦታ ላይ ምንም ነገር ባይታያቸውም "አዎ ይታየኛል" ይሉ ነበር "የእነማን ይመስላችኋል" ብለው ሲጠይቁ ዝም ከተባሉ ራሳቸው መልሰው "የመጪው ትውልድ" ይሉ ነበር። ሼህ መሀመድን "አዎ ይታየኛል" ከሚሉት ደረሳዎች አንዱ ነበሩ።

በ1963ዓ.ም አማን አምባን ለቀው ጡሩሲና በመምጣት አንድ ጎጆ ብቻ በመስራት ገዳሙን አቋቋሙ። ሼሁ "ራዕይ እስኪታየኝ ድረስ አይሰራም" በማለታቸው አሁን የሚገኘው ዋናው

መስጊድ እስከ 1973ዓ.ም ድረስ አልተሰራም ነበር። ከአስር አመት ቆይታ በኋላ የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር ዋናውን መስጊድ ማሰራት ችለዋል። ወደ ጡሩሲና መስጊድ የመጡት ብቻቸውን ቢሆንም ዋናውን መስጊድ ካቋቋሙ በኋላ በርካታ ተከታዮች አግኝተዋል። በአሁኑ ጊዜ በወሉ ትልቅ ክብር ከሚሰጣቸው ሼሆች መካከል አንዱ ሲሆኑ በቅተዋል።

በተከታዮቻቸው በርካታ ተአምራት እንደሰሩ የሚነገርላቸው ሼህ መሀመድ አማን እድሜአቸው ዘጠናዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የገዳሙ አስተዳዳሪ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም [illegible]

ፊርማ

የማስረከቢያ ቀን 25/10/05